አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች
የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት
አቀራረብ ፍተሻ

በ

ደረበ ሙሉ

ADDIS ABABA UNIVERSITY

ሰኔ 1999 ዓ.ም.

በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አማርኛን በማስተማር ዘዴ ትምህርት

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ደረበ ሙሉ

ሰኔ 1999 ዓ.ም

በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች
የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት
አቀራረብ ፍተሻ

በ

ደረበ ሙሉ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
ድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አቶ ዓለም እሸቱ (ረዳት ፕሮፌሰር) አማካሪ	ፊርማ
ኃ/ሩ መስቀሌ የውጭ ፈታኝ	ፊርማ
ኤፍሬም ፃዲቃ የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ

ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ ለፍፃሜ እስኪደርስ ድረስ ደክመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የጥናቱን ረቂቅ በማንበብና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ድጋፋቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለአቶ ዓለም እሸቱ (ረዳት ፕሮፌሰር) ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በትምህርት ቆይታዬ ከጎኔ ሆና የሞራል ድጋፍና የሥራ ዕገዛ በማድረግ ለጥናቱ መሳካት የበኩሏን አስተዋፅዖ ለአደረገችልኝ ባለቤቴ ወ/ሮ ሙዛይ አረፋይኔ ምስጋናዬ ይድረሳት። ከዚህ ደረጃ እንድደርስ የገንዘብ እና የምክር ድጋፋችሁ ላልተለየኝ ቤተሰቦቼ መለሰ፣ ትርፌ፣ መስፍን፣ ጊዜው፣ ሐብታም በጣም አመሰግናችኋለሁ።

እንዲሁም በሞራልና በገንዘብ ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ ጓደኞቼ ግዛቸው፣ ታዬ፣ ተመስገን፣ አመራ፣ መልካም፣ ጌታቸው፣ መርጊያው እና ሰለሞን የተከበረ ምስጋናዬን ሳቀርብላችሁ በታላቅ ደስታ ነው። የዚህን ፅሑፍ ረቂቅ በመተየብ ለተባበረችኝ ለሰብለ ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳት።

ማውጫ

ርዕስ		ገፅ
ምስጋና		i
ማውጫ		ii
የሠንጠረዥ ማውጫ		iv
አጠቃሎ		viii
ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ		1
1.1	የጥናቱ ዳራ	1
1.2	የጥናቱ ዓላማ	3
1.3	የጥናቱ ጠቀሜታ	3
1.4	የጥናቱ ክልልና ገደብ	4
ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳን		5
2.1	የቃላት ምንነት	5
2.2	ቃላትን የማስተማር አስፈላጊነት	5
2.3	ቃላትን ማስተማር	7
	2.3.1 ቃላትን ለማስተማር የሚረዱ መርሆዎች	7
	2.3.2 ቃላትን በማስተማር ሂደት ውስጥ የምናስተምረው ምንድነው?	10
	2.3.3 ቃላትን መምረጥ	14
	2.3.4 አዳዲስ ቃላትን የማቅረቢያ ስልቶች	16
	2.3.5 ቃላትን ማስታወስ	26
2.4	በቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተለዋዋጮች	30
2.5	የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት	34
ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ዘዴ		37
3.1	የናሙና አመራረጥ ሂደት	37
	3.1.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ	37

3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ 38
3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ 38
3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 38
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 38
3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ 38
3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ 39
3.3 የመረጃዎች አተናተን 40

ምዕራፍ አራት፡ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 42
4.1 የመረጃዎች ውጤት ትንተና 42
4.1.1 በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች 42
4.1.2. የቃላት ትምህርትን በአግባቡ እንዳይቀርብ
የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች 47
4.1.3. የቃላት ትምህርት ከማቅረቢያ ስልቶች አንፃር 55
4.1.4 ተማሪዎች ቃላትን እንዲያስታውሱ ከማድረግ አንፃር 76

ምዕራፍ አምስት :- ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሃሳቦች 82
5.1 ማጠቃለያ 82
5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች 83
ሙዳዬ ቃላት 85
ዋቢ ጽሑፎች 87
አባሪዎች 90

የሰንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ **ገፅ**

ሠንጠረዥ 1:– የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት ትምህርት ይዘትን በተመለከተ በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 43

ሠንጠረዥ 2:– የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅንና ንበትን ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ 43

ሠንጠረዥ 3:– የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅንና ንበትን ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ 43

ሠንጠረዥ 4:– የቃላት ትርጉም ትምህርት ይዘትን አቀራረብን በተመለከተ በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 44

ሠንጠረዥ 5:– የቃላት ትርጉምን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ 44

ሠንጠረዥ 6:– የቃላት ትርጉምን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ 45

ሠንጠረዥ 7:– የቃላት ግንባታን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 45

ሠንጠረዥ 8:– የቃላት ግንባታን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ 46

ሠንጠረዥ 9:– የቃላት ግንባታን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ 46

ሠንጠረዥ 10:– ስለቃላት ትምህርት አቀራረብ ያላቸውን አስተያየት መምህራን ምላሽ የሰጡበት ሰንጠረዥ 47

ሠንጠረዥ 11:– ስለቃላት ትምህርት የአቀራረብ ሁኔታ የተማሪዎች ምላሽ 48

ሠንጠረዥ 12:- ለቃላት ትምህርት የመማሪያ መፅሐፍን ከመጠቀም አንፃር የመምህራን ምላሽ 49

ሠንጠረዥ 13:– የመማሪያ መጽሐፍን ከመጠቀም አንፃር ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ 49

ሠንጠረዥ 14፡- ለቃላት ትምህርት የግል ማቴሪያል ከመጠቀም አንፃር መምህራን የሰጡት ምላሽ 50

ሠንጠረዥ 15:– የግል ማቴሪያልን አዘጋጅቶ ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች ምላሽ፡፡ 50

ሠንጠረዥ 16:– አጠቃላይ የመምህራንን ዳራ ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የመምህራን ምላሽ 51

ሠንጠረዥ 17:– የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ቁጥር
የሚያሳይ ሰንጠረዥ 53
ሠንጠረዥ 18:– የቃለት ትምህርት በአግባቡ እንዳይቀርብ ለሚያደርጉ ሁኔታዎች
መምህራን የሰጡት ምላሽ 53
ሠንጠረዥ 19:– የቃላትን ፍቺ በተመሳሳይና በተቃራኒ ቃላት ከማቅረብ አንፃር
በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 56
ሠንጠረዥ 20:- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ተጠቅሞ ማቅረብን በተመለከተ
የመምህራን ምላሽ 56
ሠንጠረዥ 21:– በተመሳሳይና በተቃራኒ ቃላት ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ 56
ሠንጠረዥ 22:– አብረው የሚሄዱ ቃላትን ከመጠቀም አንፃር በቪዲዮ በተደገፈ
ምልከታ የተገኘ መረጃ 57
ሠንጠረዥ 23:– አብረው የሚሄዱ ቃላትን ከመጠቀም አንፃር የመምህራን ምላሽ 57
ሠንጠረዥ 24:– አብረው የሚሄዱ ቃላትን ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች ምላሽ 58
ሠንጠረዥ 25:– ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብን በተመለከተ በቪድዮ ቀረፃ
በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 58
ሠንጠረዥ 26:– ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ 59
ሠንጠረዥ 27:– ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ 59
ሠንጠረዥ 28:– በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት
ከማቅረብ አንፃር 60
ሠንጠረዥ 29:– ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ 60
ሠንጠረዥ 30:– የቃላትን ትምህርት ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር
የተማሪዎች ምላሽ 60
ሠንጠረዥ 31:– የቃላት ሰዋስው መጠቀምን በተመለከተ በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ
የተገኘ መረጃ 61
ሠንጠረዥ 32:– የቃላት ሰዋስው መጠቀምን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ 61
ሠንጠረዥ 33:– የቃላት ሰዋስው መጠቀምን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ 62
ሠንጠረዥ 34:– የቃላት ግንባታን መጠቀምን በተመለከተ በቪዲዮ በተደገፈ
ምልከታ የተገኘ መረጃ 62
ሠንጠረዥ 35:– የቃላትን ግንባታ ከመጠቀም አንፃር የመምህራን ምላሽ 63
ሠንጠረዥ 36:– የቃላትን ግንባታ ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች ምላሽ 63
ሠንጠረዥ 37:– በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር
በማቀናጀት ስለማቅረብ የተገኘ መረጃ 64
ሠንጠረዥ 38:– ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብን በተመለከተ
ከመምህራን ምላሽ የተገኘ መረጃ 64

ሠንጠረዥ 39:– ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብን በተመለከተ
የተማሪዎች ምላሽ 64
በሠንጠረዥ40:– ቃሉን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን በተመለከተ በቪዲዮ
በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 65
በሠንጠረዥ 41:– ቃሉን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን በተመለከተ
መምህራን የሰጡት ምላሽ 65
ሠንጠረዥ 42:– ቃሉትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን በተመለከተ
ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ 66
ሠንጠረዥ 43:– ከቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ ቃላት የተለያዩ መግለጫዎችን
ከመጠቀም አንፃር የተገኘው መረጃ 67
ሠንጠረዥ 44:– ቃላትን የተለያዩ መግለጫዎችን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር
የመምህራን ምላሽ 67
ሠንጠረዥ 45:– ቃላትን የተለያዩ መግለጫዎችን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር
የተማሪዎች ምላሽ 67
ሠንጠረዥ 46:– ቃላትን አካላዊ ምላሽን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር በቪዲዮ
ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 68
ሠንጠረዥ 47:– ቃላትን አካላዊ ምላሽን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር
መምህራን ምላሽ 68
ሠንጠረዥ 48፡– ቃላትን አካላዊ ምላሽን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር
የተማዎች ምላሽ 69
ሠንጠረዥ 49:– የቃላትን ትርጉም በሌሎች ቃላት ብያኔ ከመስጠት
አንፃር በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ 70
ሠንጠረዥ 50:– የቃላትን ትርጉም በሌላ ቃል ብያኔ ከመስጠት አንፃር
የመምህራን ምላሽ 70
ሠንጠረዥ 51:– የቃላትን ትርጉም በሌላ ቃል ብያኔ ከመስጠት አንፃር
የተማሪዎች ምላሽ 70
ሠንጠረዥ 52:– ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ ከመስጠት አንፃር በምልከታ
የተገኘ መረጃ 71
ሠንጠረዥ 53:– ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ ከመስጠት አንፃር ከመምህራን
የተሰጠ ምላሽ 71
ሠንጠረዥ 54:– ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ ከመስጠት አንፃር ከተማሪዎች
የተገኘ መረጃ 72
ሠንጠረዥ 55:– ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን ከመጠቀም አንፃር
ከምልከታው የተገኘ መረጃ 72

ሠንጠረዥ 56:– ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን ከመጠቀም አንፃር
የመምህራን ምላሽ 73
ሠንጠረዥ 57:– ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን ከመጠቀም አንፃር
የተማሪዎች ምላሽ 73
ሠንጠረዥ 58፡- ቃሉን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመተርጎም አንፃር በምልከታው
የተገኘ መረጃ 74
ሠንጠረዥ 59፡- ቃሉን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመተርጎም አንፃር ከመምህራን
የተገኘ መረጃ 74
ሠንጠረዥ 60፡- ቃሉን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመተርጎም አንፃር ከተማሪዎች
የተገኘ መረጃ 74
ሠንጠረዥ 61፡- በቃላትን ትምህርት ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ ከማድረግ አንፃር
በምልከታ የተገኘው መረጃ 76
ሠንጠረዥ 62፡- በቃላትን ትምህርት ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ ከማድረግ
አንፃር የመምህራን ምላሽ 76
ሠንጠረዥ 63፡- በቃላትን ትምህርት ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ ከማድረግ
አንፃር የተማሪዎች ምላሽ 76
ሠንጠረዥ 64፡- ምስል ከሳች ቃላትን ከመጠቀም አንፃር በምልከታው የተገኘ መረጃ 77
ሠንጠረዥ 65፡- ምስል ከሳች ቃላትን ከመጠቀም አንፃር ከመምህራን የተገኘ መረጃ 77
ሠንጠረዥ 66፡- ምስል ከሳች ቃላትን ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች የተገኘ መረጃ 78
ሠንጠረዥ 67፡- ለቃላት ትርጉም ተማሪዎች የራሳቸውን ብልሃት ከመጠቀም
አንፃርበምልከታው የተገኘ መረጃ 78
ሠንጠረዥ 68፡- ለቃላት ትርጉም ተማሪዎች የራሳቸውን ብልሃት ከመጠቀም
አንፃር ከመምህራን የተገኘ ምላሽ 79
ሠንጠረዥ 69፡- ለቃላት ትርጉም ተማሪዎች የራሳቸውን ብልሃት ከመጠቀም
አንፃር ከተማሪዎች የተገኘ ምላሽ 79
ሠንጠረዥ 70፡- የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ከማስተማር አንፃር በምልከታ
የተገኘ መረጃ 80
ሠንጠረዥ 71፡- የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ከማስተማር አንፃር ከመምህራን
የተገኘ መረጃ 80
ሠንጠረዥ 72:– የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ከማስተማር አንፃር ከተማሪዎች
የተገኘ መረጃ 81

አጠቃሎ

ይህ ጥናት በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረብን ለመፈተሽ የሞከረ ነው። በዚህም ፍተሻ የቃላት ትምህርትን መምህራን በአግባቡ ያቀርባሉ? መምህራን የትምህርቱን ይዘት ለማቅረቢያነት የበለጠ የሚጠቀሙባቸው ስልቶች የትኞቹ ናቸው? መምህራን የቃላትን ትምህርት በአግባቡ እንዳያቀርቡ በሙሉም ሆነ በከፊል የማያደናቅፉ ሁኔታዎች አሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል።

ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እንዲቻል መረጃዎች ከመምህራን እና ከተማሪዎች እንዲሰበሰቡ ተደርጓል። በዚህም መሠረት በቪዲዮ የተደገፉ ምልከታ እና የፅሑፍ መጠይቆች ለመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት አገልግሎት ላይ ውለዋል። በቪዲዮ በተደገፉ የክፍል ውስጥ ምልከታ እንዲሁም ለመምህራን እና ለተማሪዎች በተበተነ የፅሑፍ መጠይቅ ስለ ትምህርቱ አቀራረብ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

መምህራን ለሁሉም የቃላት ትምህርት ይዘቶች ትኩረት ሰጥተዋል ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ለማቅረብ እና ለማለማመድ የሚረዱ ስልቶችን ከተወሰኑት በስተቀር አዘውትረው አለመጠቀማቸውን መገንዘብ ተችሏል።

መምህራን በከፍተኛ ደረጃ የተገበሯቸው የማቅረቢያ ስልቶች ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን፣ የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበትን፣ የቃላትን ግንባታ በመጠቀም፣ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት እና ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ሌላ ቃል ብያኔ በመስጠት ማቅረብ የሚሏቸውን ስልቶች ነው። ነገር ግን መምህራን ለሌሎች የማቅረቢያ ስልቶች ትኩረት አልሰጡም። እነዚህ በመምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ሲሆኑ የታዩት የማቅረቢያ ስልቶች አብረው የሚሄዱ (የሚቧደኑ) ቃላትን መጠቀም፣ በተለያዩ አውዶች ማቅረብ፣ ምንባብ በማዘጋጀት፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣ የተለያዩ መግለጫዎችን (ቁሦችን፣ ስዕሎችን)፣ አካላዊ ምላሽን በመጠቀም፣ ለቃሉ ጥልቅ ማብራሪያ፣ ለቃሉ ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት እና ለቃሉ በትግርኛ ቋንቋ አቻ ቃል በመተርጎም ማቅረብ የሚሉት ናቸው።

ሌላው ደግሞ ተማሪዎች ቃላትን እንዳይረሱ ከማድረግ አንፃር መምህራን ምስል ከሳች ቃላትን በከፍተኛ ደረጃ ሲጠቀሙ፣ ለቃለት ትርጉም ተማሪዎች ተግባራዊ ልምምድ እንዲያደርጉ፣ ለተማሪዎች የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃት እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንፃር፣ ትምህርቱን በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገሙ ከማስተማር አንፃር ሲታይ ግን በዝቅተኛ ደረጀ ላይ ይገኛል።

በመጨረሻም መምህራን ይህንን የቃላት ትምህርት በአግባቡ ለተማሪዎች ያስተላልፉ ዘንድ የሚመለከታቸው ክፍሎች ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን እንዲሰሩ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በሳምንት ከ2 ወደ 3 እንዲያድግ፣ የመምህራን የክፍለ ጊዜ ብዛት በሳምንት ከ20 እንዳይበልጥ፣ ለመምህራን የቃላት ትምህርትን በተመለከተ አጫጭር ስልጠናዎችን እንዲወስዱ ቢያደርጉ የሚሉት የመፍትሄ ሃሳቦች በጥናት አቅራቢው ተጠቁመዋል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

በማንኛውም ቋንቋ ሀሳባችንን በተገቢው መንገድ ለመሰሎቻችን ለማስተላለፍ የቃላት ዕውቀት ያስፈልገናል፡ የቋንቋውን መዋቅር ብናውቅም የቃላት ችሎታ ከሌለን ሀዘንና ደስታችን፣ ማጣትና ማግኘታችን ባጠቃላይ የተለያዩ ስሜቶቻችንን ለመግለጽ አንችልም። ለዚህም ነው Harmer (1991፣ 153) የቋንቋ መዋቅር የቋንቋውን አዕምሮ ሲገነባ ቃላት ደግሞ አስፈላጊውን የቋንቋውን ስጋና ነፍስ ይፈጥራሉ በማለት የሚናገሩት።

በቋንቋው መዋቅር የጠለቀ እውቀት ቢኖረን እንኳ ቃላትን በተፈለገው ቦታ እስካልተጠቀምን ማለትም ሀሳባችንን በትክክል የሚገልፁ ቃላትን እስካላወቅን ድረስ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ተግባቦትን ለመፍጠር ከባድ መሰናክል ይገጥመናል (Wallace፣ 1987 እና Choi፣ 1990)።

እንግዲህ ተማሪዎች በቋንቋው ለሚፈጥሩት መስተጋብር የጠራና የቀለጠፈ ተግባቦት ይኖር ዘንድ ቃላት ያላቸውን የጎላ ሚና በተለያዩ ምሁራን ከተሰጠው አስተያየት ለመገንዘብ ይቻላል። ቃላት በቋንቋ ውስጥ ሚናቸው ከፍተኛ ስለሆነ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ወቅት የእነዚህን የቃላት ይዘቶች በአግባቡ ሊማሩ ይገባል። Richards and Rodgers (1986፣ 94) በበኩላቸው ለብዙ ዓመታት ለቃላት ትምህርት ይሰጥ የነበረው ትኩረት በጣም አነስተኛ ነበር። ቃላትን የሚጠቀሙባቸው ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር ካልሆነ በስተቀር እራሳቸውን ቃላትን ለማስተማር በሥርዓት የተዘጋጀና የታወቀ ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴ አልነበረም። ቀስ በቀስ ግን ቃላትን የማስተማር አስፈላጊነት እየታመነበት መጣ በማለት ይናገራሉ።

የቃላት ትምህርት ለበርካታ ዓመታት ትኩረት ተነፍጎት ይቆይ እንጂ በአሁኑ ወቅት የራሱ የሆኑ ዓላማዎች ተነድፈውለት የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች እየተበጁለት በአግባቡ በመቅረብ ላይ ያለ የቋንቋ ዘርፍ መሆኑን ማረውና ተስፋዬ (1993፣ 3) ያስገነዝባሉ።

Cook (1991:42) ም በመቀጠል ይህ አስፈላጊ ይዘት እንዴት እንደቀረበ ሲያብራሩ ጥንታዊ የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ የቃላትን ዝርዝር መሸምደድ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን በዓረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የቃሉ አገባብ ወሳኝ በመሆኑ በምናስተምርበት ወቅት

ቃላትን ከመዋቅራዊ አውዳቸው ነጥለን ማቅረብ የለብንም፣ ምክንያቱም የቃላት ትርጉም የሚወሰነው በዓረፍተ ነገር ውስጥ ከሌሎች ቃላት ጋር ባላቸው ዝምድና ነውና ይላሉ።

ወንድወሰን (1995፣140) በሥራ ቦታውና በየገበያው ቦታ በየክልሉ ቋንቋ መጠቀም እየተስፋፋ መጥቷል። ይህ ደግሞ አማርኛን በተፈጥሯዊው መቼት የመልመድን እድል እያጠበበውና ቋንቋውን በመማር ብቻ የሚገኝ እያደረገው ይሄዳል። ስለሆነም ተማሪዎች የሚኖራቸው የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ እጅጉን በትምህርት ቤት በምናቀርብላቸው የትምህርት ይዘት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም በተራው ለትምህርቱ የምንሰጠው ትኩረት ከፍ እንዲል ይጠይቀናል።

Lado (1964:115) በሚከተለው መልኩ የወንድወሰንን ሀሳብ ያጠናክራሉ። ተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋውን መሠረታዊ ቃላት በህፃንነቱ ማወቁ የህልውና ጉዳይ ነው። እነዚህን መሠረታዊ ቃላት የሚማረውም ከቤተሰቡ ወይም ከአካባቢው ነው። ስለዚህ ትምህርት ቤት ገብቶ የሚማረው በሚያውቃቸው ቃላት እንዲዕፍ እና የበለጠ እንዲያዳብራቸው ነው። ይሁን እንጅ የሁለተኛ ቋንቋውን ቃላት ለማወቅ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋው ቃላት ሰፊ ተጋልጦ ስለማይኖረው በትምህርት ቤት ገብቶ እንዲማር ይገደዳል። በመሆኑም የሁለተኛ ቋንቋን ቃላት የማወቅ ሁኔታ በመምህሩ፣ በመማሪያ መፅሐፉ ወይም በትምህርት ቤቱ ይወሰናል ማለት ነው።

የዚህ ጥናት አቅራቢም ጥናቱን ለማቅረብ ያነሳሱት ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። አንደኛው የቃላት ትምህርት አቀራረብ ምንም እንኳ ከመማሪያ መፃህፍት አንጻር በርካታ ስራዎች ቢኖሩም ከመምህሩ አንፃር ግን አጥኚው ባደረገው ፍተሻ አንድ ጥናት ብቻ ማግኘቱ ገና ብዙ ያልተሰራበት በመሆኑ ይህንን ክፍተት ለመመላት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በክልሉ በየቦታው በአማርኛ ቋንቋ የመገልገሉ ሁኔታ እየጠበበ መምጣቱ እና ቀደም ሲል አጥኚው ይሠራበት በነበረው ትምህርት ቤት እና በአጎራባች ወረዳዎች በሚገኙ ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሁሉም ተማሪዎች ማለት ይቻላል ሀሳባቸውን የመግለጽ ችግር ማየቱ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ አጠቃላይ የቋንቋ ክሂሎችን ቢመለከትም በሌሎች ክሂሎች ላይ በርካታ ጥናቶች ስለተካሄዱ በቃላት ትምህት በኩል ያለውን ክህሎት ለመመላት ነው። ይህ ጥናትም ለመመለስ ይዟቸው የተነሳው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. የቃላት ትምህርት ይዘቶችን መምህራን ያቀርባሉ?
2. መምህራን የትምህርቱን ይዘት ለማቅረቢያነት የበለጠ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች የትኞቹ ናቸው?

3. መምህራን የቃላትን ትምህርትን በተገቢው ሁኔታ እንዳያቀርቡ በሙሉም ሆነ በከፊል የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች አሉ?

1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በትግራይ ክልል በሰሜን ምዕራብ ዞን በሚገኙ የሽሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ የሐክፈን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ የእንደባኃና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና የአዲዳሮ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርትን እንዴት እንደሚያቀርቡ መፈተሽ ነው። በዚህ አብይ ዓላማ ስርም ከዚህ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ይተኮሩባቸዋል።

- መምህራን የቃላት ትምህርት ይዘቶችን በክፍል ውስጥ ማቅረባቸውን ወይም አለማቅረባቸውን መፈተሽ፣
- መምህራን የቃላትን ትምህርት በአግባቡ እንዳያቀርቡ የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ማመልከት፣
- መምህራን ትምህርቱን ለማከናወን በበለጠ የሚጠቀሙባቸው የማቅረቢያ ስልቶችን ለይቶ ማመልከት፣

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

የቃላት ትምህርት ዓላማን ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ መምህራን እና ሌሎች የትምህርት ግብዓቶች ድርሻቸው የጎላ ነው። ስለዚህ ትምህርቱ በተገቢው ሁኔታ መቅረቡን ወይም አለመቅረቡን መፈተሽ አሰፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ በትምህርቱ አቀራረብ ወቅት ከመምህሩ አንባር የሚታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን ማየት እንዲሁም በአቀራረቡ ወቅት የትምህርት ግባቶችን ድርሻ በመፈተሽ የተጽኖአቸውን ሁኔታ መጠቆም የመማር ማስተማሩን ሂደት የተቃና ሊያደርገው ይችላል። ስለዚህ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይጠበቃል።

- መምህራኑ ቃላትን የሚያቀርቡባቸውን ስልቶች ለይቶ ለማስገንዘብ ይችላል።
- የቃላት ትምህርት በአግባቡ እንዳይከናወን የሚያደርጉ አደናቃፊ ሁኔታዎች ካሉ በመለየት መፍትሄ ሊጠቁም ይችላል።
- ለወደፊቱ የሚመለከታቸው ክፍሎች ሊያሟሏቸው የሚገባቸውን እና ችግሩ የሚቃለልባቸው የመፍትሄ ሀሳቦችን ለመጠቆም ያስችላል። በዚሁ ርዕስም ሰፋ ያለ ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልግ አጥኚ እንደ መሻገሪያ ድልድይ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

1.4 የጥናቱ ክልልና ገደብ

ይህ ጥናት በትግራይ ክልል የሚገኙትን ሁሉንም ትምህርት ቤቶች አያካትትም። በክልሉ ከሚገኙት ዞኖች ውስጥ በአመቺነት ናሙና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞን ተመርጧል። በዚህ ዞን ከሚገኙት ስምንት ትምህርት ቤቶች መካከል በነሲብ የዕጣ ናሙና የተወሰዱት አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው። እነዚህም ትምህርት ቤቶች የሽሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ የሐክፈን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ የእንደባኅና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና የአዲዳሮ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። በእነዚህ ትምህርት ቤቶችም በአመቺ ናሙና ዘጠነኛ ክፍል ብቻ ተወስዷል።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚያስተምሩ መምህራንም መካከል ፭ኛክፍልን ብቻ የሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይካተታሉ። ከቋንቋው ይዘቶችም አንፃር ይህ ጥናት በቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ ላይ ይመሰረታል ይሁን እንጂ የቃላት ትምህርት አቀራረቡን ከመማሪያ መጽሐፉ፣ ከመምህሩ መምሪያ እና ከመርሃ ትምህርቱ አንፃር ለመገምገም አይሞክርም። ትኩረቱ መምህራን ይህንን ዘርፍ እንዴት በክፍል ውስጥ ያቀርቡታል? በሚለው ላይ ተመስርቶ ትምህርቱን በሚያቀርቡበት ወቅትም አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተለዋዋጮች ካሉ መፈተሽ ነው።

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን

2.1 የቃላት ምንነት

ስለ ቃላት ምንነት በርካታ ፀሃፍት የየራሳቸውን ብያኔ ሲሰጡ ይስተዋላል። ለአብነት ያክል የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል።

ባየ (1986) ቃል ፍቺ አልባ ድምፆች ስርዓት ባለው መንገድ ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ፍቺ አዘል አካል እንደሆነ ይናገራሉ። Ur (1996:60) በበኩላቸው ሲያብራሩ ደግሞ ቃል ከአንድ በላይ የሆኑ ድምፆች ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ትርጉም ያለው የድምፅ ስብስብ ነው። በፈሊጣዊ አገላለፃቸው ደግሞ ከመደበኛው ትርጉም የተለየ ፍቺ ሊኖራቸው የሚችሉ የድምፆች ስብስብ ቃላት ይባላሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን አስተያየት በተጨማሪ McCarthy (1990:3) ቃል ራሱን ችሎ የሚቆምና ትርጉም ሊሰጥ የሚችል ምዕላድ መሆኑን ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ ምሁራኑ በቃላት ዙሪያ የተሰጡትን ብያኔዎች ስንመረምር ቃላት የሚፈጠሩት ከአንደበት በሚወጡ ድምፆች ሲሆን ድምፆቹም በሥርዓት መቀናጀት ይኖርባቸዋል። በመጀመሪያ ድምፆቹ ትርጉም አልባ ይሁኑ እንጂ በቋንቋው መዋቅራዊ በስርዓት ከተሰደሩ ትርጉም አዘል የሆኑትን ቃላት ይመሰርታሉ። እነዚህም ቃላት ነጠላ ትርጉምን ይሸከማሉ። ቃላት ነጠላ ትርጉምን ይሸከሙ እንጅ አመሰራረታቸውን ስናይ የድምፆች፣ የምዕላዶች እና የቃላት የእርስ በርስ ቅንጅት ሊሆን ይችላል። በዚህ ጥናትም ስለ ቃላት አቀራረብ ሲነሳ ነጠላ ቃልን፣ ድርብ ቃልን እና ፈሊጦችን ታሳቢ በማድረግ ነው።

2.2 ቃላትን የማስተማር አስፈላጊነት

የአንድ ቋንቋ መሠረቱ ቃላት ናቸው። እነዚህ ቃላትም በቋንቋ ውስጥ ለሚገኙ ጽንስ ሐሳቦች መግለጫ ሆነው ያገለግላሉ። በመሆኑም ቃላት በቋንቋ ውስጥ ቁልፍ ሚናን ይጫወታሉ። Celce Murcia (1991:277)፣ Malay (1990:10)፣ Taylor (1990:1) እና Allen (1983) በቋንቋ ውስጥ ለቃላት የተሰጠውን ትኩረት በሚመለከት ሲገልፁ ቀደም ባሉት ዘመናት የቃላት ትምህርት ሆን ተብሎ ሳይሆን የቋንቋውን አገባብ (ሰዋሰው) በሚማሩበት ጊዜ በአጋጣሚ ይሰጥ እንደነበር በማስታወስ ነው። በዚህም ቃላትን ማስተማር የተረሳ ጉዳይ እንደነበር አውስተዋል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በየጊዜው የሚፈልቁት የቋንቋ ፍልስፍናዎች ቃላትን የማስተማር አስፈላጊነት ምንም የማያሻማ

እና ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ሲያስረግጡ ይታያሉ። Allen (1983:5) እንደሚያስረዱት ይህ የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት ከታመነበት የትምህርቱን ይዘቶች በአግባቡ ለተማሪዎች ማቅረብ ተገቢ ነው። በመሆኑም ለቃላት ትምህርት የማቅረቢያ ስልቶች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። ለዚህም ሁለት ነጥቦች በምክንያትነት ተጠቅሰዋል።

1. መምህራን ቃላትን ለማስተማር ብዙ ጊዜ ያባክኑ ነበር። ነገር ግን ይህ የመምህራን ድካም ውጤታማ አልሆነም።
2. በዚህ ዘርፍ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ተማሪዎች በቋንቋው ተግባቦት የመፍጠር ችግር ምንጩ ከቃላት ጋር የተያያዘ መሆኑ የሚሉት ናቸው።

ይህንንም ወንድወሰን (1995፣134) ሲያስረዱ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ችግሮች ተብለው ከሚጠቀሱት አንዱ የቃላትን ትምህርት የሚመለከት ነው። በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከተፈጥሯዊ መቼት ጋር ባልተዛመደበት ሁኔታ የክፍል ውስጡ የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት መሰረታዊ ይሆናል። ስለዚህ ቋንቋውን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች በየደረጃው የተመረጡ ቃላት በተስማሚ ቅደም ተከተል (መመዘኛው ድግግሞሽ ጠቀሜታ፣ ወዘተ. ሊሆን ይችላል) ሊቀርቡላቸው ይገባል። በሌሎች ክሊሎችና የዕውቀት ዘርፎች ለሚኖራቸው "ብቃት" የቃላት ትምህርት የጀርባ አጥንት ነውና።

የቃላት ትምህርት ፋይዳ የቃላትን ትርጉም ከማወቅ ባሻገር ለሌሎቹ የቋንቋ ዘርፎች ትምህርትም ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይህንን በቋንቋ ትምህርት የቃላትን ቁልፍ ሚና ለማስረዳት ምሁራኑ የሰጧቸውን አስተያየቶች ማጤን ያስፈልጋል። Richards & Rogers (2001) በቋንቋ ትምህርት ለተግባቦት እንደመሰረተ ድንጋይ የሚቆጠሩት የሰዋሰው ይዘቶች ሳይሆኑ ቃላት ናቸው ሲሉ ይገልፃሉ። በመዋቅር ውስጥ የትኛው ሰዋሰው ነው? የትኛው ሰዋሰው አይደለም? የሚሉትን ትርጉም የሚወስኑት ቃላት ናቸው። Wilkins (1972:111) ያለሰዋሰው በጣም ውስን ነገሮችን ማለት ሲቻል ያለ ቃላት ግን ምንም ማለት እንደማይቻል ይገልፃሉ። በተመሳሳይ መልኩ Maley (1990:10) እና Taylor (1990:1-7) ቃላትን በተሟላ መልኩ ማወቅ የሚከተሉትን ያካትታል።

- የቃሉን የንበት ቅርጽ ለመለየት
- የቃሉን የጽህፈት ቅርጽ ለማወቅ
- የቃሉን የንግግር፣ የእርባታ ክፍል ለመገንዘብ
- ሥነ አገባባዊና ሥነ መዋቅራዊ ቅደምተከተሉን ለመለየት
- በቋንቋ ውስጥ ያለውን የድግግሞሽ መጠን ለማወቅ

- ውስን አገባቡን (ዐውዱን) ለመገንዘብ
- የቃሉን መሠረታዊ ፍች ለማወቅ ይረዳል።

አንድ ተማሪ ከላይ የተጠቀሱትን ይዘቶች ከተገነዘበ በቋንቋው በማዘዝ በተግባቦት ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉትን በርካታና ወሳኝ ችግሮችን ማስወገድ ይችላል። ይህም ሲባል ተማሪው በቋንቋው የተፃፈን ነገር አንብቦ መረዳት፣ ቃላትን በመመስረት እና በማራባት እንዲሁም ንበቱን በመገንዘብ ሥነ አገባባዊ እና ሥነ መዋቅራዊ ቅደም ተከተልን በመጠበቅ ለመፃፍ፣ የሚነበብን እና የሚነገርን መልዕክት ሳይዛባ ለመገንዘብ፣ በተጨማሪም የቋንቋውን ሰዋሰው ለመገንዘብ የቃላት ሁለንተናዊ እውቀት መኖር ተገቢ እና አስፈላጊ ነው። ከዚህም በመነሳት የቃላት ትምህርት ከሌሎቹ የቋንቋ ዘርፎች በበለጠ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን።

2.3 ቃላትን ማስተማር

ቀደም ሲል በተለያዩ ምሁራን ከተዘረዘሩት አስተያየቶች እንደምንገነዘበው በቋንቋ ትምህርት ወቅት የቃላት ሚና የላቀ ነው። ስለዚህ ይህን ይዘት በትምህርትነት ማቅረቡ አያጠያይቅም። በመሆኑም ቀጥሎ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ቃላትን ለማስተማር የሚረዱ መርሆዎች የትኞቹ ናቸው? ቃላትን በማስተማር ወቅት የምናስተምረው ምንድነው? ቃላትን መምረጥ እና ቃላትን የማቅረቢያ ስልቶች የሚሉት ናቸው።

2.3.1 ቃላትን ለማስተማር የሚረዱ መርሆዎች

ማንኛውንም ሥራ በአግባቡ ማከናወን ይቻል ዘንድ ቀላል፣ ግልፅ እና አቋራጭ መንገድን የሚጠቁመ መርሆዎችን መታጠቅ አስፈላጊ ነው። መምህሩም በተለያዩ ምሁራን በየጊዜው የሚፈልቁ ሃሳቦችን በማመዛዘን ይዞት የተነሳውን ዓላማ እንደ ግብ መምቻ መሳሪያነት ቢጠቀምባቸው መልካም ነው።

እነ Wallace (1987:251) እና Cumino (1990:15) በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላትን ከማስተማራቸው በፊት መምህራን ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ነጥቦችን እንደሚከተለው አስፍረዋል።

2.3.1.1 ዓላማ

መምህሩ ምን ማስተማር እንዳለበት ግልጽ የሆነ መነሻ መያዝ ይኖርበታል። ይህም ማለት መምህሩ እንደ ዓላማ ይዞት የሚነሳው ጉዳይ የትኞቹን እና ምን ዓይነት የቃላት

ይዘትን ማሳወቅ አለብኝ? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ነው። ይህ ካልሆነ ግን ቃላትን የማስተማር ሂደት ውጤታማ ላይሆን ይችላል።

2.3.1.2 ብዛት ወይም መጠን

ቃላትን ከማስተማር በፊት የትኞቹ ቃላት መካተት እንደሚገባቸው መምህሩ አስቀድሞ መወሰን ይጠበቅበታል። ለህፃናትና ለአዋቂዎች የሚቀርቡትን የአዳዲስ ቃላት መጠን መምህሩ አስቀድሞ ማወቅ አለበት።

የሚቀርበው የቃላት ብዛት እንደየተማሪዎቹ ዓይነት እና እንደየክፍል ደረጃቸው የሚታይ ነው። በርካታ አዳዲስ ቃላት ሲቀርቡ በተማሪው ዘንድ የፍርሃት እና የፍላጎት ማጣት ሁኔታን ይፈጥርበታል። ለምሳሌ በአንድ ምንባብ ውስጥ በርካታ ቃላት ለተማሪው አዲስ ከሆኑ ተማሪው የማንበብ ተግባሩን ሊያቋርጥ ይችላል።

Gairns and Redman (1986:67) ምን ያክል ቃላትን እናቅርብ የሚለው ነገር ሲነሳ ሁለት ነገሮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርብን ያስረዳሉ።

ከውጫዊ ሁኔታዎች አንፃር፦

- የተተኪሪው ቋንቋ ቃል ከተማሪው ቋንቋ ቃል ጋር ምን ያክል የቅርፅ ተመሳስሎ ይታይበታል?
- የቃሉን ትርጉም ተጨባጭነት ከማድረግ አንፃር ምን መደረግ አለበት?
- የተማሪው የመማር አካባቢ ምን ይመስላል?
- ምን ያክል ከመርሃ ትምህርቱ ጋር አጣጥሞ ማቅረብ ይቻላል? የሚሉት ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው።

ከመምህሩ አንፃር የሚታዩ ጉዳዮች፦

- በተመደበልህ ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ምን ያክል ተዘጋጅተሃል?
- ለታላሚዎቹ ቃላት ተማሪዎቹ ምን ያህል ተጋልጠዋል? የሚሉት ቁልፍ ጉዳዮች መልስ ሊያገኙ ይገባቸዋል።

2.3.1.3 ፍላጎት

በመማሪያ መጽሐፉ ወይም በመርሐ ትምህርቱ የሚቀርቡ ይዘቶች የተማሪዎችን ፍላጎት ያማከሉ ከሆኑ ተማሪዎች ቃላቱን በቀላሉ የሚያስታውሱበት አጋጣሚ ይፈጠራል። በዚህ ጊዜ ቃላቱን በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ የመጠቀም ዕድሉ ሰፊ ይሆንላቸዋል። አስረጅ፦ ለቴክኖሎጂ ውጤቶች ጉጉት ካላቸው እንደ መኪና፣ ቴፕ፣ ኮምፒውተር ላሉት ቃላት የማወቅ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ሊሆን ይችላል።

2.3.1.4 ተዘውታሪነትና ተደጋጋሚነት

ተማሪዎች የተለያዩ ቃላትን በተደጋጋሚ የሚጠቀሙበት ከሆነ በማንኛውም ጊዜ በማስታወስ ሊተገበሩ ይችላሉ። እግረመንገዳቸውን የቃሉን ትክክለኛ ንበት ለይተው እንዲያውቁ ያስችላል። በመሆኑም መምህራን ቃላትን ከማስተማራቸው በፊት ይህንን መርህ ከግምት ውስጥ ማስገባት መቻል አለባቸው። ለምሳሌ፦ "ደብተር" የሚለው ቃል በመምህራቸው ሲታዘዙም ሆነ እርስ በራሳቸው ሲዋዋሱ አዘውትረው ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በመሆኑም እንደዚህ ያሉ ቃላት ተዘውታሪና ተደጋጋሚ ስለሚሆኑ በተማሪዎች ዘንድ እየታወሱ ይተገበራሉ ማለት ነው።

2.3.1.5 ትርጉም ሰጪ አቀራረብ መከተል

ተማሪዎች አሻሚ ባልሆነ መንገድ የቃላትን ፍች እንዲገነዘቡ መምህሩ ከቃላት ቅርጽ በተጨማሪ የቃሉ ፍቺ ምን ሊወክል እንደቀረበና የትኛውን ቁስ እንደሚያመለክት ጥሩ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። አስረጅ፦ "ትንሽ" የሚለውን ቃል ለማስተማር በመጠን የተለያዩ ሁለት ቁሶችን በማቅረብ በንጽጽር አንዱ ማነሱን በማሳየት ቃሉን መጥራት።

2.3.1.6 ሁኔታዊ አቀራረብ

መደበኛ እና ኢ-መደበኛ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ ልንጠቀምባቸው የሚገቡ ቃላትን መምህሩ መግለጽ መቻል አለበት። ከቋንቋው ተፈጥሯዊ አውድ በመመስረት የሚፈጠረውን ሁኔታ እንደ ፍርድ ቤት፣ ከሃይማኖት አባት ጋር ወይም በሀዘን ቦታ የሚደረጉ ንግግሮችን እንደ ይዘት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። አስረጅ፦ እንደሻጭና ገዢ በመሆን ሻጩ የሚጠቀምባቸውን ቃላትና ገዢው የሚጠቀምባቸውን ቃላት በጭውውት እንዲያቀርቡ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል።

2.3.1.7 በዐውድ ማቅረብ

እያንዳንዱ ቃል በአገባብ (በዐውድ) ውስጥ ሲቀርብና ከዓውድ ውጭ ሲቀርብ የፍች ለውጥ ያመጣል። ይህን በተመለከተ መምህሩ ሊመጡ የሚችሉትን የትርጉም ለውጦች ለማስገንዘብ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት መቻል አለበት። ለምሳሌ፦ "ሰፈረ" በሚለው ቃል ሁለት የተለያየ ትርጉም ያላቸው አረፍተ ነገሮች በሚከተለው መልኩ እንዲሰሩ በማድረግ ማቅረብ ይቻላል።

1. የተፈናቀለው ህዝብ ጉዳት እንዳይደርስበት በተመረጡ ቦታዎች <u>ሰፈረ</u> → ተቀመጠ
2. አቶ አየለ ሽምብራውን ለመሸጥ በኩባያ <u>ሰፈረ</u>። → ለካ

ከላይ የተብራሩት የቃላት ማስተማሪያ መርሆዎች በተለያዩ ምሁራን እንደመመሪያ እንዲጠቀሙባቸው ለመምህራን ይመከራሉ። በእርግጥ መርሆዎቹ ከላይ የተጠቀሱት ብቻ እንደማይሆኑ ይታመናል። ነገር ግን እነዚህ የተጠቀሱት ለቃላት ትምህርት አቀራረብ በጣም ወሳኝና አስፈላጊ መሆናቸውን መረዳት አስፈላጊ ይሆናል።

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላትን ከማስተማራችን በፊት መምህራን ሊያስተውሏቸው ስለሚገቡ መርሆዎች ይህን ያህል ካልን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላትን ስናስተምር ምን ምን ነገሮችን እንደምናስተምር ቀጥሎ ቀርቧል።

2.3.2 ቃላትን በማስተማር ሂደት ውስጥ የምናስተምረው ምንድነው?

ቃላትን በምናስተምርበት ወቅት ምን ምን ነገሮች እንደሚዳስሱ Ur(1996:60) እንደሚከተለው አስፍረዋል። እነዚህም የቃላት ይዘቶች የቃሉ ቅርፅ፣ ሰዋሰው፣ አብሮነት፣ ትርጉም እና የቃላት ግንባታ የሚሏቸው ናቸው።

2.3.2.1 ቅርጽ (ንበት እና ሆሄያት):– ቃላትን ስናስተምር ተማሪዎች የአንድን ቃል አጠራር ንበትና የሆሄያትን ቅርጽ መለየት አለባቸው። ለዚህም በመማር ማስተማር ሒደት መምህሩ ሁለቱን ቅርጾች በትክክል መተግበራቸውን ማጤን ይጠበቅበታል። ለምሳሌ:– "አለ" የሚለው ቃል በስነ ድምፅ አፃፃፍ ሲፃፍ ሀ. ሲላላ አልኝ

ለ. ሲጠብቅ አልልኝ

ከአስረጁ እንደምንገነዘበው "አለ" የሚለው ቃል ንበት ሁለት ዓይነት ነው። ስለዚህ ይህ ቃል ጠብቆ ሲነበብ እና ላልቶ ሲነበብ የተለያዩ አፃፃፎች እና ትርጉሞች እንዳሉት እንረዳለን።

2.3.2.2. ሰዋስው:– የእያንዳንዱን የቃል ክፍል ከቅርፅ እና ከአገባብ አንፃር መለየት ይቻላል። ሰዋስዋዊ አገባብ ማለት በባለቤት፣ በተሳቢ እና በማሰሪያ አንቀፅ ቃሉ ያለው ማለት ነው። በመሆኑም የቃሉን ሰዋሰዋዊ አገባብ ተማሪዎች እንዲለዩ በማድረግ አዳዲስ ቃላትን ማሳወቅ ይቻላል።

ለምሳሌ:–1. ተማሪው ነገ ይመጣል። የዚህን ዓረፍተ ነገር ቃላት ተማሪው-ባለቤት፣ ነገ-ተውሳከ ግስ እና ይመጣል ማሰሪያ አንቀፅ በማለት ማስረዳት።

2.3.2.3 አብረው የሚሄዱ ቃላት:– ሁሉም ቃላት እርስ በርስ አብረው ሊሄዱ አይችሉም። Harmer and Rossner (1998:19) አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ቃላት በምሳሌ አሳይተዋል።

ምሳሌ፡-

	ሰው	ተራራ
ረጅም	✓	×
ከፍተኛ	×	✓

2.3.2.4 ትርጉም፡–

ሀ. የቃላት ተናጥላዊ ፍች፡– የቃላትን ተናጥላዊ ፍች ስናሠይ በውስጡ የተለያዩ ጽንሰ ሐሳቦችን ልናገኝ እንችላለን፡፡

1. እማሬያዊ ፍች፡– ይህ ፍች የቃላትን መደበኛ፣ ጥሬ ወይም ዝርዐ ትርጉም የሚያመለክት ነው፡፡ አንድ ቃል የሚያስተላልፈውን ቀጥተኛ ፍች የያዘ ነው፡፡

አስረጅ፡- ከሁሉም በላይ አንበሳ እፈራለሁ፡፡ "አንበሳ" የሚለው ቃል የእንስሳ ዓይነት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

2. **ፍካሬያዊ ፍች**፡–ከቃላቱ ጥሬ ትርጉም ጋር እየተጎዳኘ የሚገልጸውን ተደራቢ የምስጢር ትርጉም የሚይዝ ነው፡፡ አስረጅ፡- አበበ በትምህርቱ አንበሳ ነው፡፡ "አንበሳ" የሚለው ቃል ጀግንነት፣ ጥንካሬን.... የሚያመለክት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ቃላትን በመስጠት የያንዳንዱን ቃል ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ በአረፍተ ነገር እንዲያሳዩ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡

3. ተገቢነት፡- ተመሳሳይ ቃላት በተመሳሳይ ወይም በተለያየ ዐውድ ውስጥ ሲገቡ ሊኖር የሚችለውን ፍች ይመለከታል፡፡ አስረጅ፡- 1. በመኪና አደጋ ሕይወቱ አለፈ፡፡
2. በመኪና አደጋ ሕይወቱ ሄደ፡፡

ከሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች የተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ቢኖራቸውም ለዚህ ዓረፍተ ነገር ሄደ የሚለው ቃል ተገቢ አይደለም፡፡

ለ. ተዛምዷዊ ትርጉም

አንድ ቃል ከሌላው ቃል ጋር ያለውን ተዛምዶ በተለያየ መልክ ማየት ይቻላል፡፡ ይህንን ለይቶ ማወቅ ለመማር ማስተማሩ ሒደት ውጤታማነት ጠቃሚ ነው፡፡ Ur (1996:62) የቃላትን ተዛምዷዊ ፍች በተለያየ መልኩ ያሰፈረውን እንመልከት፡፡

1. ተዛማጅ ቃላት፡- እነዚህ ቃላት ትርጉማቸው ፍፁም ተመሳሳይ ወይም የተቀራረበ ተመሳስሎ የሚታይባቸውን ቃላት ይመለከታል፡፡

አስረጅ፡- ደግ፣ የዋህ፣ ሩህሩህ ...

2. ተቃራኒ ቃላት፡- ተዛራሪ ትርጉሞን ወይም ሃሳቦችን የሚያካትቱ ቃላትን የሚመለከት ነው፡፡ እነ Gairns and Redman (1986:25) ተቃራኒ ቃላትን በሶስት የተለያዩ ምድብ እንደሚከተለው ከፍለዋቸዋል፡፡

- **ንፅፅራዊ ተቃራኒ /Gradable antonmys/**

በዚህ ዓይነቱ የተቃራኒ ክፍል ውስጥ የሚመደቡ ቃላት አንዣራዊ የሆነ የደረጃ ልዩነት የሚታይባቸው ናቸው።

አስረጅ፡- የማርታ ቤት <u>ትልቅ</u> ነው።

የአስቴር ቤት <u>ትንሽ</u> ነው።

«ትንሽ» እና «ትልቅ» የሚሉት ቅጽሎች ልዩነት አላቸው። ነገር ግን የልዩነቱ መጠን የማርታ ቤት ከአስቴር ቤት አንዣራዊ በሆነ መልኩ ትልቅ መሆኑንና የአስቴርም ቤት ከማርታ ቤት ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑን ያሳያል። ይህ ንፅፅራዊ ተቃርኖ በእድሜና በመጠን ላይ ይንፀባረቃል።

አስረጅ፡- ሽማግሌ - ወጣት

አሮጌ - አዲስ

- **ማሟያ ተቃራኒ /Complementaries/**

በዚህ ቅርጽ ውስጥ የሚገኙ ተቃራኒ ቃላት በደረጃ የይለያዩና አንዱ ከአንዱ ጋር የማይገናኙ ናቸው። አስረጅ፡- "ወንድ"

"ሴት"

ማንኛውም ህይወት ያለው ፍጡር አንደኤ ወንድ ሆኖ ከተፈጠረ ሴት የመሆን ዕድል (አጋጣሚ) ባለመኖሩ ቁርጥ ያለ ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

- **ግልባጫዊ ተቃራኒ /Converseness/**

አንድ ቃል በሌላ አገባብ ውስጥ ሲገባ የሚኖረውን ግልባጫዊ ትርጉም ያመለክታል።

አስረጅ፡- 1. ማርታ የዓለሙ <u>ሚስት</u> ነች።

ዓለሙ የማርታ <u>ባል</u> ነው።


2. ሥዕሉ ከቴሌቭዥኑ <u>በላይ</u> አለ።

ቴሌቪዥኑ ከሥዕሉ <u>በታች</u> አለ።

- **ተክታች ቃላት (Hyponyms)**

በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙ ቃላት በአንድ ጥቅል ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር ነገሮችን ያመለክታል።

አስረጅ፡- 2. እንስሳት



ውሻ በግ አንበሳ ወዘተ.

የቃላትን ተዛምዷዊ ፍች ስናስተምር ትርጉምን አብረን እናስተምራለን።

ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ እነ Harmer and Rosser (1998)፣ Gairns and Redman (1986:28) ቃላትን በምናስተምርበት ጊዜ የሚከተሉትንም መገንዘብ እንደሚቻል ይመክራሉ::

- ዐውዳዊ ተዛምዶ:-
  ምሳሌ:- ከእርሻ ጋር የሚዛመድ መስኖ፣ ገበሬ፣ ትራክተር
- አንዱ ከሌላው ጋር ያለው ተዛምዶ (Part whole relation)
  ምሳሌ:- እጅ ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች እንደ እግር፣ ራስ ካሉት ጋር ያለውን ተዛምዶ ማሳየት::

Ur (1996) ምንድን ነው የምናስተምረው? ለሚለው በመጨረሻ ያሰፈረው የቃላት ግንባታን ነው::

2.3.2.5 የቃላት ግንባታ

ይህ አንድን ቃል ወይም ጥምር በላይ የሆነን ቃል ሊያካትት ይችላል:: በቃላት ግንባታ ጊዜ መምህሩ የተለያዩ ነገሮችን ሊያስተምር ይችላል:: ከእነዚህም ውስጥ ቅጥያዎችን፣ ጥምር ቃልን እና ፈሊጦችን በተለያየ መልኩ በማቅረብ ማስተማር አስፈላጊ ነው::

ሀ. ቅጥያዎች:- የተለያዩ የቅጥያ ዓይነቶችን ማስተማር ይቻላል:: ቅጥያዎቹ ቁጥርን፣ ያታን፣ መደብን ጊዜን እና ባለቤትን አመልካች ሊሆኑ ይችላሉ::

ለምሳሌ:- "ስለፈረሳችሁ" የሚለውን ቃል በመውሰድ በሚከተለው መልኩ ማሳየት ይቻላል::

ቃል	ዋናው ቃል	ቅድመ ቅጥያ	ድህረ ቅጥያ
ስለፈረሳችሁ	ፈረስ	ስለ–	–ኣችሁ

ለ. ፈሊጥ:- Gairns and Rdman (1986:35) የፈሊጦች ትርጉም ከተጣመሩት ቃላት ተናጥላዊ ፍቺ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው ይናገራሉ:: የተለያዩ ሁለት ቃላትን በማጣመር አዳዲስ ቃላትን ማስተማር ይቻላል:: በዚህም ፈሊጣዊ አነጋገሮች የህብረተሰቡን ባህል፣ ወግና ልማድ... የሚያንፀባረቁትን በተለያየ መልኩ ማስተማር ይቻላል:: ከተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ጋር አብረው የሚዛዱ ቃላትን በማሰባሰብ እንዲገነዘቡ ማድረግ ይቻላል::

ምሳሌ:- ሙሬ አፍ = ተከፊ፣ አኩራፊ፣ አሳባቂ

ሆደ መጋዝ = ክፉ ሰው

ሐ. ጥምር ቃል:- Wallace (1981:184) ጥምር ቃል ከሁለት ነጠላ ቃላት የሚመሰረት ቃል ነው። በአብዛኛው የጥምር ቃሉ ትርጉም ከተጣማሪዎቹ ቃላት ትርጉም የተለየ አይደለም። በእርግጥ አልፎ አልፎ የጥምር ቃሉ ትርጉም ከተጣማሪዎቹ ቃላት ትርጉም ፍፁም የተለየ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ በማለት ያብራራሉ። ስለዚህ ጥምር ቃላትን በተለያዩ የአቀራረብ መንገዶች ማስተማር ይቻላል። ለጥምር ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ፣ ጥምር ቃላትን እንዲያዛምዱ በማድረግ፣ ጥምር ቃላትን በመስጠት ሁለት የተለያዩ ነጠላ ቃላትን እንዲያወጡ በማድረግ ማቅረብ ይቻላል።

ምሳሌ:– እንጀራ እናት → የአባት ሚስት

ትምህርት ቤት → ትምህርት የሚሰጥበት ቦታ

በቃላት ትምህርት ለተማሪዎች በይዘትነት የሚቀርቡት በርካታ ቢሆኑም ጠቅለል ባለ መልኩ የቃላት ቅርፅ፣ የቃላት ሰዋሰው፣ የቃላት ትርጉም እና የቃላት ግንባታ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ስለዚህ አንድ መምህር በክፍል ውስጥ ቃላትን አስተምራለሁ ብሎ ከተነሳ እንደአስፈላጊነቱ ከላይ የተዘረዘሩትን ይዘቶች በማዋሀድ ወይም በተናጠል ማቅረብ ይኖርበታል። እነዚህ የቃላት ይዘቶች በክፍል ውስጥ መቅረባቸው የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ከማዳበር አንፃር ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ።

2.3.3 ቃላትን መምረጥ

HyCraft (1991:15) ቃላትን ለትምህርትነት በምንመርጥበት ጊዜ መሠረት የምናደርጋቸው መመሪያዎችን እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

2.3.3.1. የተለመዱ ቃላት

የተለመዱ ቃላት ሲባል በአገልግሎት ሽፋናቸው ተመዝነው ከሌሎች ቃላት በበለጠ ለየዕለት ተዕለት መስተጋብር አገልግሎት የሚሰጡትን ነው። ማንኛውንም የተለመደ ቃል ተጠቅመን በምናስተምርበት ጊዜ ቃሉ በቀላሉ በተማሪዎች አእምሮ የመቀረጽ ሐይሉ ከፍተኛ ነው።

2.3.3.2 ተማሪዎች ምን ያስፈልጋቸዋል?

የተማሪዎችን ዳራ ማወቁ ለቃላት መረጣው ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ለምሳሌ አንድ ተማሪ "ቢራቢሮ" የሚወድ ከሆነ እያንዳንዱን የቢራቢሮን የሰውነት ክፍል ለማወቅ ስለሚጓጓ በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል። በመሆኑም የተማሪዎችን ፍላጎት ያማከለ ቃላት መምረጡ አስፈላጊነት አለው።

2.3.3.3 ከተማሪዎች ቋንቋ አንፃር

የታላሚው ቋንቋ ቃል የያዘው ፅንሰ ሀሳብ የተማሪው ቋንቋ ቃል ከያዘው ፅንሰ ሀሳብ ጋር ሊለያይ ይችላል። ስለዚህ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በአንድ ቋንቋ በምናስተምርበት ጊዜ የትኛው ቃል በሌላ ቋንቋ ከሚገኘው ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው የሚለው መታወቅ አለበት።

2.3.3.4 ርዕሰ ጉዳይ፡-

ቃላትን በቀላሉ ለማስተማር በአንድ በተወሰነ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ ይዘትን መምረጥ ተገቢ ነው። በዚህም ተማሪዎች የሃሳቡን ቅደም ተከተል በመከተል የቃላትን ፍች እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል።

ምሳሌ፡- ተማሪዎችን በሁለት በመክፈል የህክምናና የበሽተኛን ባህሪ ተላብሰው አጭር ጭውውት ቢያደርጉ በሚያካሂዱት የሃሳብ ልውውጥ የተወሰኑ አዳዲስ ቃላትን ሊረዱ ይችላሉ።

2.3.3.5 መፈረጅ (ማጣቀስ)

የተወሰኑ ቃላት ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያለውን ሌላ ቃል በምንጠራበት ወቅት በአእምሮ ውስጥ የሚመጡበት አጋጣሚ አለ። ስለዚህ እንደእነዚህ ያሉ ቃላትን በማምጣት በእነዚህ ዙሪያ ሊታወሱ የሚችሉትን በርካታ ቃላትን ማስተማር ይቻላል።

ምሳሌ፡- «ትምህርት ቤት» የሚለው ቃል ሲነሳ እንደ ደብተር፣ እርሳስ መፅሀፍ ወንበር፣ መምህር፣ ቤተመጻሕፍት፣ ወዘተ. ያሉት ቃላት ሊታወሱ ይችላሉ።

2.3.3.6 ተዛማጅ ምሥረታ

በዓረፍተ ነገር እና በሐረግ መዋቅሮች ውስጥ አንዱ ቃል በገባበት ሌላው ቃል ሊገባ ይችላል። ለዚህም ከተነሳው ነጥብ ጋር አብረው የሚሄዱ ተዛማጅ ቃላትን መጠቀሙ ተገቢ ነው።

ለምሳሌ፡- እኔ _____ እበላለሁ።

እኔ _____ እጠጣለሁ። በመጀመሪያው ክፍት ቦታ የሚበሉ ነገሮችእንደ እንጀራ፣ ዳቦ፣ ሙዝ ያሉት ሲገቡ በሁለተኛው ደግሞ የሚጠጡ ነገሮች እንደ ውሃ፣ ጠላ፣ ወተት የመሳሰሉት ይገባሉ።

የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከተለዩ በኋላ ለትምህርትነት የሚቀርቡት ቃላት ይመረጣሉ። በርካታ የቃላት መምረጫ መስፈርቶች በተለያዩ ምሁራን ሲቀርቡ ይታያል። ከነዚህም መስፈርቶች መካከል የሚመረጡት ቃላት የተለመዱ፣ የተማሪዎቹን ፍላጎት ያገናዘቡ፣ ከተማሪዎች ቋንቋ ትርጉም ጋር የማይፋለስ ፅንሰ ሀሳብ የያዙ፣ ግንባታን የሚያስተምሩ፣

የተወሰነ ርዕሰ ጉዳይና መፈረጅን የሚያስገነዝቡ የቃላት ይዘቶችን መምረጥ ወሳኝና አስፈላጊ መስፈርቶች መሆናቸውን ለመረዳት ችለናል።

2.3.4 አዳዲስ ቃላትን የማቅረቢያ ስልቶች

በመማሪያ ክፍል ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ከማስተማራችን በፊት በምን ዓይነት ስልት ቃላቱን ማቅረብ እንደሚገባ መገንዘብ አለብን። የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመገንዘብ የሚያስችሉ የተለያዩ የማቅረቢያ ስልቶችን Ur (1996:63)፣ HyCraft (1991:47) እንደሚከተለው አስፍረዋል።

2.3.4.1 ብያኔ በመስጠት፡- ይህ የማቅረቢያ ዘዴ የቀረበውን ቃል በዚያው ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የያዘውን ፅንሰ ሐሳብ ትርጉም የሚያሳይ ነው። Wallace (1987፣67) ብያኔ የቃላትን ትርጉም በቀላሉ ለተማሪዎች ለማሳየት የሚያገለግል ስልት መሆኑን ያብራራሉ።

ለምሳሌ. በሚከተለው መልኩ ማቅረብ ይቻላል። መፅሐፍት እና ሌሎች የፅውቀት ምንጭ የሆኑ ፅሑፎች ሁሉ በሥርዓት የሚደረደሩበት፣ ሰዎች ገብተው የሚያነቡበት ቦታ "ቤተ መፅሐፍት" ነው።

ብያኔ በመስጠት ለማስተማር ሲፈለግ በተቻለ መጠን ለብያኔው አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቃላት ግልፅነት የሌላቸው እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። የቃሉ ብያኔ ቃሉ የሚወክለውን ቁስ ከተሰራበትና ከቁሱ ባህሪ አንፃር ሊሰጥ ይችላል።

2.3.4.2 ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት


የቃላትን ትርጉም ለማስገንዘብ ሲሞክር ተማሪዎቹ በቀላሉ ላይረዱት ይችላሉ። ስለዚህ ይህንን የግንዛቤ ችግር ለማስወገድ መምህሩ የተቻለውን ሁሉ ጥረት የሚያደርግበት ዘዴ ነው። ይህም ሲባል ያ ቃል የወከለውን ነገር ወይም ፅንሰ ሐሳብ ሁለንተናዊ ባህሪ በዝርዝር መንገር ወይም መግለፅ ማለት ነው። አስረጅ፡- "በግ ማለት አራት እግር ያለው፣ ስጋው የሚበላ፣ ፀጉሩ ለብርድልብስ መሥሪያ የሚያገለግል፣ ላቱ ወፍራም የሆነ የቤት እንስሳ ነው" በማለት ማብራራት ይቻላል።

2.3.4.3 ለዋና ቃል (Hyponym) ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት

Wallace (1987፣67) ዋና ቃል የሚለው የሚዘረዘሩ ነገሮችን አጠቃሎ የሚይዝ ቃል ነው። ማለትም ዝርዝር ፅንሰ ሐሳቦችን አካቶ የሚይዘውን ነው። ስለዚህ ይህንን ዋና ቃል ከሌሎቹ ዝርዝር ፅንሰ ሃሳብ ካላቸው ቃላት ጋር ዝምድናውን በማሳየት ማለማመዱ የቃሉን ትርጉም ከማስጨበጥ አንፃር ፋይዳው የጎላ ነው።

አስረጅ:- የፍራፍሬ ዓይነቶች _____ ፣ _____ ፣ _____ ፣ _____ ናቸው::

መልሱ:- ብርቱካን፣ ሎሚ፣ መዝ፣ ዘይቱን፣ ወዘተ. የሚሉት ይሆናሉ:: በዲያግራም ለማሳየት ሲሞክር ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል::



Gairns and Redman (1986:24)

ከምሳሌዎች መገንዘብ የሚቻለው ጥቅል ፅንሰ ሀሳብን የያዘው ቃል ዝርዝር ፅንሰ ሃሳብን ከሚወክሉት ከእያንዳንዱ ቃል ጋር አቻ ትርጉም የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

2.3.4.4 የተለያዩ መግለጫዎችን በማቅረብ

ቁሳቁሶችን በአካል አምጥቶ በማሳየት የዚያን ቁስ መግለጫ ከሆነው ቃል ጋር በማዛመድ የቃልን ፍቺ ማስተማር ትምህርቱን የበለጠ ተጨባጭ እንደሚያደርገው ከማንም የተሰወረ አይደለም:: በእርግጥ ጠቀሜታው የጎላ ይሁን እንጂ መምህሩ ሁሉንም የቁስ ዓይነት ወደክፍል አምጥቶ ያስተምራል ማለት አስቸጋሪ ነው:: ለምሳሌ እንደ "ፈረስ" ያለን ቃል ለማለማመድ መምህሩ ፈረሱን ወደ ክፍል እንዲያመጣ አይጠበቅም፤ አይቻልምና:: ሌሎችን ግን እንደ ወንበር፣ ብርጭቆ፣ ወዘተ. ዓይነቶችን ለማሳየት በጣም ቀላል ነው::

ስዕሎቹም ቢሆኑ የቃላትን ትርጉም ለማስተማር ያላቸው ፋይዳ ከቁሶች ያልተናነሰ ነው:: ይህም ሲባል መምህሩ ትምህርቱን ተጨባጭ ከማድረግ አንፃር ከላይ እንደተጠቀሰው ቁሶችን በአካል ወደ ክፍል ማምጣት በማይቻልበት ወቅት ቁሶቹን በመተካት በስዕል ማሳየት ይችላል:: Wallace (1987:67) ይህንን ሲያስረዱ በስዕሎች የሁለተኛ ቋንቋን ትምህርት ማቅረብ በዘመኑ ተመራጭ የሆነ የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ የሚያሳድግ ስልት ነው:: ስዕሎች ተማሪዎችን ከማነቃቃት አንፃር፣ ትምህርቱን ግልፅ ከማድረግ አንፃር፣ ቁስ አካሉን ወይም ድርጊቱን ከእነ ባህሉ ከማሳየት አንፃር

ሚናቸው የጎላ ነው። በተጨማሪም ስዕሎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይም ከዚያው ክፍል ውስጥ ማሳየት ይቻላል።

ስለዚህ መምህሩ የእነዚህን መግለጫዎች ፋይዳ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቁሶችን ከተቻለ በአካል በማምጣት ካልተቻለ ስዕሎችን በራሱ በመምህሩ የተሰሩትን፣ በተማሪዎች የተሰሩት ወይም ከሌሎች ምንጮች የተገኙትን ወደ ክፍል ማምጣት ክንውኑን የተሳካ ያደርገዋል ማለት ነው።

2.3.4.5 አካላዊ ምላሽ ዘዴን በመጠቀም

አካላዊ ምላሽ ትምህርቱን ነባራዊ ከሚያደርጉ የማቅረቢያ ስልቶች ይመደባል። አካላዊ ምላሽ በሚታዩ እንቅስቃሴዎች ላይ የተመሰረቱ ሲሆን የሚተገበሩትም በመምህሩ ወይም በተማሪዎች ሊሆን ይችላል።

Gairns and Redman (1986:73) መምህራን የቃላትን ትርጉም ለማሳየት የሚያደርጉት የአካል እንቅስቃሴ ከሰርቶ ማሳያ ስልት እንደሚመደብ ያስረዳሉ። ተማሪዎች በዚህ ስልት እያደረጉ ወይም እየሰሩ እንዲማሩ ስለሚገፋፋ ትምህርቱን ለማስጨበጥ ድርሻው የላቀ ነው። ትምህርቱንም በሚከተለው መልኩ ማቅረብ ይቻላል። በመጀመሪያ ለተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው መመሪያዎችን በካርድ ፅፎ መስጠት። መመሪያዎቹ ሁለት አይነት ሊሆኑ ይችላሉ። አንደኛው የተወሰኑ ተማሪዎችን የታዘዙትን ከካርዱ ላይ አንብበው እንዲፈፅሙ ማዘዝ የሚያስችል ይሆናል። ሁለተኛው ደግሞ ሌሎች ተማሪዎች አንደኛውን መመሪያ ተከትለው ያከናወኑትን የተማሪዎች ድርጊት እንዲያስረዱ የሚያዝዝ መመሪያ የያዘ ካርድ በማደል ማለማመድ። አስረጅ:- አንዱን ተማሪ በሩን እንዲቆልፍ ማድረግ ከዚያም ሌሎች ተማሪዎችን ተማሪው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ድረስ ያከናወነውን ድርጊት በቃላት እንዲገልፁ ማድረግ።

2.3.4.6 አውድ በመፍጠር ማቅረብ

የቃላትን ትርጉም ከአውድ አንፃር ማቅረብ ሲባል ቃሉ በቁመ- ከሚሰጠው ትርጉም በተለየ ሁኔታ በሌሎች ከጎኑ በሚቆሙት ቃላት አማካይነት ትርጉሙ የሚወሰንበት ሁኔታ ነው። Pettigrew (2006) የቃላትን ፍቺ ከተለያዩ የአውድ ዓይነቶች አንፃር ማቅረብ እንደሚቻል ይጠቁማሉ።

- ከምክንያትና ውጤት አውድ አንፃር በአንድ ዓ. ነገር ውስጥ የጎደለውን ቃል እንዲገምቱ በማድረግ፣ አለሚቱ በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት ስለዚህ ፈተናውን ____ ። ቢሆን፣ መልሱ የሚሆነው "ታልፋለች" እንጂ "ትወድቃለች" አይሆንም ለዚህም ምክንያቱ "ጎበዝ" የሚለው ቃል ነው።

- ከተቃራኒ ፍቺ አንፃር:– መሃመድ አጭር ሲሆን አለሚቱ ደግሞ _____ ናት።
  መልሱ:– ረጅም ይሆናል።
- ከዓረፍተ ነገር መልዕክት አንፃር:– አባትዬው ኳሷን በእግሩ ለህፃኑ ልጅ _____ ።
  መልሱ:– ለጋለት/መታለት ሊሆን ይችላል።

በአጠቃላይ ተማሪዎች በአውድ የቀረበን ትምህርት በቀላሉ ይገነዘባሉ፣ የሚገነዘቡትም ከሌሎች ተያያዥ ነገሮች ጋር ስለሚሆን በአእምሯቸው ተቀርፆ ለብዙ ጊዜ ይቆያል።

2.3.4.7 ተመሳሳይ ቃላትን በማቅረብ (Synonym):– ይህ ማለት ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት በማቅረብ ማለማመድ ይቻላል። ተመሳሳይ ቃላትን ማወቅ በመናገርና በመፃፍ ወቅት በበለጠ ተስማሚ የሆነን ቃል መርጦ ለመጠቀም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። Wallace (1981) የተመሳሳይ ቃላት ትምህርትን በተለያየ መልክ ማቅረብ እንደሚቻል ይናገራሉ።

- ቃላትን በተመሳሳይ ፍቻቸው እንዲያዛምዱ በማድረግ
- ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ
- አንድ ቃል በመስጠት ለዚያ ቃል ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውን ቃላት እነዲዘረዝሩ በማድረግ ማለማመድ

እንደ እነ Allen (1983) ሃሳብ ከሆነ ፍፁም የሆነ ተመሳስሎ አለ ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ቃላት በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይ ቢሆኑም የሚለያዩበትም መጠነኛ ባህሪ ይኖራቸዋል። ይህም ማለት የአንዱ ቃል የሰፋ ፅንሰ ሃሳብ መያዝ፣ አንዱ በገባበት ሌላው አለመግባት፣ ሰዋሰዋዊ ባህሪያቸው መለያየት፣ ወዘተ. የሚሉት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። ስለዚህ መምህሩም ትምህርቱን በሚያቀርብበት ወቅት እነዚህን ጉዳዮች ማጤን ይጠበቅበታል። አስረጅ:– ከበደ ጥሩ ልብወለድ ደረሠ። ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ትርጉሙ _____ ነው። መልሱ ፃፈ ይሆናል።

2.3.4.8 ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን በማቅረብ

ተቃራኒ ፅንሰ ሐሳብ የያዙ ቃላትን በተለያዩ የማቅረቢያ አይነቶች በማቅረብ ማለማመድ ይቻላል። Grains and Redman (1986:24-27) በዝርዝር ያሰፈሯቸው የተቃራኒ ዓይነቶች አቻዊ ተቃርኖ፣ ተገላቢጦሽ ተቃርኖ እና የደረጃ ተቃርኖ ናቸው። እነዚህን ተቃራኒ ቃላት ለማስተማር የተለያዩ የጥያቄ ዓይነቶችን መቅረፅ ይቻላል።

- ተቃራኒ ቃላትን እንዲያዛምዱ ማድረግ፣
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ፣

- ቃሉን በመስጠት ለዚያ ቃል ተቃራኒ ፍቺ የያዙ ቃላትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ መምህራን ሁሉም የተቃራኒ ዓይነቶች የየራሳቸው የተቃርኖ ባህሪ ስለሚኖራቸው ተቃራኒ ፍቺ የሚለውን ጥቅል ሀሳብ በማቅረብ ተማሪዎች ግራ እንዳይጋቡ ሊያስረዷቸው ይገባል። አስረጅ:- አተረፈ ብሎ ከሰረ ቢል አዘነ ብሎ _____ይላል። መልሱ ተደሰተ፣ ፈነጠዘ የሚሉት መልስ ሊሆኑ ይችላሉ።

2.3.4.9 በመተርጎም ማቅረብ

የዚህ አቀራረብ ትኩረት በተተኳሪው ቋንቋ የቀረበን የቃላት ፍቺ በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ አቻዊ ትርጉም መስጠት ነው። Wallace (1987) ተማሪው የቃላትን ትርጉም ከአውዱ መፍታት ካልቻለ፣ ሌሎችን ስልቶች በመጠቀም ማስረዳት ካልተቻለ ያለው አማራጭ በተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ አቻ ቃል መተርጎም ነው። በተለይም ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ትምህርቱን ለማስረዳ ጊዜ ቆጣቢ ዘዴ ነው በማለት ያብራራሉ። በእርግጥ አንዳንድ ምሁራን ከአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በስተቀር ለሌሎች የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች ይህንን ዘዴ ከመጠቀም ይልቅ በተተኳሪው ቋንቋ ማብራሪያና ገለፃ በመስጠት ማስተማር ተመራጭነት እንዳለው ይከራከራሉ።

ትምህርቱን በሚከተሉት የጥያቄ ዓይነቶች ማለማመድ ይቻላል

- በተተኳሪው ቋንቋ የቀረበን ቃል በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲተረጉሙ በማድረግ
- በአፍ መፍቻቸው ቋንቋ ቃሉ የያዘውን ፅንሰሐሳብ በተተኳሪው ቋንቋ ቃል አቻ ትርጉም እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል። አስረጅ:- "ሱቅ" ለሚለው የአማርኛ ቃል በትግርኛ ቅንቋ "ድንኳን" የሚለው ቃል ይተካዋል።

2.3.4.10 ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ

ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ለማስተማር የሚያስችል ጥሩ የማስተማሪያ ስልት መሆኑን እነ Grains (1986) ያስረዳሉ። በተለይ ፅሑፉ በተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነት ካለው ትምህርቱን እንዳይረሳ ስለሚያደርግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ስለዚህ መምህሩ ፅሑፉን ከመረጠ በኋላ በሚከተለው መልኩ ማቅረብ ይችላል።

- ቃላትን ከምንባቡ በማውጣት በምንባቡ መሠረት እና ከምንባቡ ውጭ ያላቸውን ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ
- ቃላትን በመስጠት በምንባቡ ውስጥ የእነዚህን ቃላት ተቃራኒ ወይም ተመሳሳይ ፍቺ የያዙ ቃላትን ከፅሑፉ ፈልገው እንዲያወጡ ማድረግ

- ከምንባቡ የወጡ ቃላትን በየቃል ክፍላቸው እንዲመድቡ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል። በእርግጥ የሚቀርበው ፅሑፍ ለትምህርቱ ካለው ጠቀሜታ አንፃር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተመዝኖ መቅረብ ይኖርበታል።

ከላይ ከተዘረዘሩት የማቅረቢያ ስልቶች ውስጥ ከተማሪዎች ደረጃ፣ ከትምህርቱ ዓይነት ከጊዜው አንፃር በማጣጣም መምረጡ የመምህሩ ድርሻ ይሆናል።

2.3.4.11 በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

Gairns and Redman (1986፣ 70-71) ተማሪው መምህሩን ወይም ጓደኛውን በመጠየቅ ለመረዳት በማይችልበት ወቅት መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ችግሩን ሊፈታ እንደሚቻል ያብራራሉ። በመዝገበ ቃላት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሆኑት መካከል ንበትን፣ ሰዋሰውን እና ፍቺን ማስተማር ይቻላል።

ከንበት አንፃር ቃሉ እንዴት እንደሚነበብ፣ አፅንኦቱ የት ላይ እንደሚያርፍ እና ስነድምፃዊ አጣፋን ሲያስተምር፣ ከሰዋሰው አንፃር ደግሞ የቃል ክፍሉን፣ አህፅሮተ ቃሉን ያስረዳል። ለምሳሌ የሥምን ብዙ ቁጥር፣ የሚቆጠርን እና የማይቆጠርን ስም፣ ተሻጋሪ እና ኢ ተሻጋሪ ግሶችን፣ የአሁን እና የኃላፊ ግዜን በቀላሉ ያሳያል። ሌላው ደግሞ ከፍቺ አነፃር ብያኔውን አውዳዊ በሆነ መልኩና ከመግለጫዎች አንፃር ያብራራል። የፊሊጦችን፣ የጥምር ቃል ግሶችን እና የአባባሎችን ትርጉምም ያስገነዝባል።

የሺጥላ (1997፣37) በመዝገበ ቃላት አስደግፎ የቃላትን ማቅረብ አንዱ ስልት እንደሆነ ያስረዳሉ። Harmer (1995፣174)ም ይህ ስልት በርካታ የቃላት ትምህርት ተማሪዎች ይህንን ሁሉ መረጃ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለባቸው ይመክራሉ። ስለዚህም የሚከተሉትን ዓይነት አቀራረቦችን በመከተል ተማሪዎች ከመዝገበ ቃላት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል።

- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ የቃላትን ዝርዝር በመስጠት ማለማመድ
- ቃላትን በስነ ድምፃዊ አጣፋ እንዲፅፉ ጥያቄዎች በመስጠት ማለማመድ
- ለፊሊጦች፣ ለጥምር ግሶች እና ለአባባሎች ትርጉም እንዲሰጡ በማድረግ ተማሪዎች መዝገበ ቃላት እንዲጠቀሙ ማለማመድ ተገቢ ነው።

2.3.4.12 ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ማቅረብ

የሺጥላ (1997፣34) Mingን በመጥቀስ ሲያብራሩ ተማሪዎች የተረዷቸውን አዳዲስ ቃላት አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ መጠቀም የሚጀምሩት አስቀድመው የአቀባይ

ክሂሎቻቸውን ተጠቅመው ቃላቱን በተረዱበት አገባብ ቢሆንም፣ ቃላቱን ተጠቅመው ሃሳባቸውን ለመግለፅ በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ሙከራ ወደ ማመንጨት ይሸጋገራሉ።

ስለዚህ በመጀመሪያ የቃላትን ንበት፣ ሰዋሰው እና ፍቺ የሚገነዘቡት ከሚያነቡት እና ከሚያዳምጡት ነገር ነው። ይህንን እውቀታቸውንም በሚናገሩበት እና በሚፅፉበት ወቅት ደግሞ የበለጠ ያዳብሩታል። በዚህ መልኩ የሚማሩት የቃላት ትምህርት ተጨባጭነቱ ከፍተኛ ነው። በክሂሎች አስደግፎ ቃላትን ማስተማር ተማሪ አሳታፊነቱ ስለሚጎላ የወቅቱ ተመራጭ የማቅረቢያ ዘዴ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። ስለሆነም መምህሩ በዚህ ዘዴ በሚከተለው መልኩ ይዘቱን ማቅረብ ይችላል።

- በቃላት አረፍተ ነገር እንዲሰሩባቸው በማድረግ
- በቃላት እንዲከራከሩ በማድረግ
- በምንባቡ መሠረት ለቃላት ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ
- በአዳመጡት መሠረት የቃላትን ትርጉም በፅሑፍ እንዲሰጡ በማድረግ ማቅረብ ይቻላል።

CelceMurcia (1991:298) በበኩላቸው የቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎች በሁለት ይከፍሏቸዋል። እነርሱም በዕቅድ ቃላትን ማስተማር እና ያለዕቅድ ቃላትን ማስተማር ናቸው።

1. በዕቅድ ቃላትን ማስተማር

ቃላትን በዕቅድ በምናስተምርበት ጊዜ የመምህሩ ተቀዳሚ ተግባር ይዘቶችን በማዘጋጀት እና ተዘጋጅቶ ወደ ክፍል በመምጣት ትምህርቱን በገለፃና በልምምድ ማካሄድ ነው። ለዚህም ቃላትን በውይይት፣ በምልልስ፣ በንባብና ማዳመጥን በመሳሰሉት ተግባራት ማስተማር ይቻላል። በዕቅድ ቃላትን ማስተማር ሦስት የተለያዩ ደረጃዎች ሲኖሩት እያንዳንዱ ደረጃ በከፍተኛ ጥንቃቄ የተዘጋጀ ሒደት አለው።

ደረጃ አንድ

ሃሳብን ማስተላለፍ (Convey meaning)

በዚህ ደረጃ አዳዲስ ቃላትን ለተማሪዎች ለማቅረብ የሚያስችሉ በጣም በርካታ ስልቶች ቢኖሩም እንደ መምህሩ የፈጠራ ችሎታ ቁጥራቸው ሊወሰን ይችላል። ከበርካታ የማቅረቢያ መንገዶች መካከልም የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው።

1. **የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎች**:– በዚህ ምድብ ውስጥ የተለያዩ ተጨባጭ ነገሮች እንደ ሥዕል፣ ፎቶግራፍ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ካታሎግ . . . በመውሰድ ረቂቅ የሆነ ጽንሰ ሐሳብ ያላቸውን ቃላት ማስገንዘብ ይቻላል።

2. **አብረው የሚሄዱ ቃላት**:– ሁለት ዓይነት የተለመዱ አብረው የሚሄዱ የቃላት ቡድኖች አሉ።

1. ተመሳሳይ ፍች ያላቸው ቃላት
2. ተቃራኒ ፍች ያላቸው ቃላት

3. ሥዕላዊ ሠንጠረዦች:– Lindstromber (1985)ን ዋቢ በማድረግ CelceMurcia (1991:301) እነዚህ ሥዕላዊ ሠንጠረዦች ሥዕላዊ መግለጫዎችንም፣ ሊያካትቱ ይችላሉ። በእነዚህ አማካይነት ተማሪዎች የተለያዩ የቃላትን ዝምድና መገንዘብ ያስችላቸዋል።

4. ገለጻ፣ ምሳሌና ልዩ ልዩ ነገሮችን መንገር:– አንዳንዴ መምህሩ የሚሰጠው ብያኔ እንደ መዝገበ ቃላት ግልጽ ላይሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ የተለያዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ የቃሉን ፍች እንዲገነዘቡት ማድረግ ይቻላል።

5. ዐውድ:– አስቸጋሪ የሆኑ የቃላትን ፍች ለማስተማር ከምንጠቀምበት ዘዴ አንዱ ዐውድ ነው። የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮችን በመመሥረት ተማሪዎች የአዲሱን ቃል ፍች ከዐውድ እንዲረዱ ማድረግ ተገቢ ነው።

6. መሠረታዊ ቃላትና ቅጥያዎች:– በዚህ ምድብ ውስጥ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን ከዋና ቃላት እንዲለዩ ማስቻል የመምህሩ ድርሻ ነው።

ደረጃ ሁለት

የግንዛቤ ማረጋገጫ (Check understanding)

በሁለተኛው ደረጃ ላይ የሚካተቱት የተማሪዎችን ግንዛቤ በማረጋገጥ የቀረቡ ልዩ ልዩ መልመጃዎች ናቸው።

1. ክፍት ቦታን መሙላት:– ይህ ዘዴ ተለምዷዊ የሆነውና የተማሪዎችን ቃላት የመገንዘብ ችሎታ ለማረጋገጥ ከሚውሉት ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው። ለምሳሌ ከምንባብ ውስጥ አንድን ቃል በመውሰድ ለዚያ ቃል ትክክለኛ ፍች ሊሰጥ የሚችለውን ቃል አይተን የምናሰፍርበት ነው።
2. ማዛመድ:–ይህ በአንድ በኩል ተቃራኒ፣ ተመሳሳይ ቃላት፣ ብያኔዎች ወይም ሥዕሎች ሊሰፍሩ ይችላሉ። በጣም ጥሩ የሚባለው የተዛምዶ ጥያቄ ተቀራራቢነት ያላቸውን ሁነቶች እንዲያዛምዱ መጠየቅ ነው።
3. ልዩ ልዩ የምድብ መልመጃዎች:– በዚህ ዘዴ መምህሩ በርካታ መልመጃዎችን ሊሰጥ ይችላል። ተማሪዎች ከተዘረዘሩት ውስጥ እንደየ ባህርያቸው በተለያየ ዘርፍ እንዲመደቡ በማድረግ ማስተማር ይቻላል። ለምሳሌ:- የተለያዩ እንስሳት ስሞችን በመዘርዘር ቢቀርብ ተማሪዎች እንስሳቱን አጥቢ፣ እንቁላል ጣይ፣ በራሪ . . . በማለት መከፋፈል ይችላሉ።

በደረጃ ሁለት ውስጥ መምህሩ የተለያዩ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ለቀረቡት የቃላት ዝርዝር የ(×) እና (✓) ምልክቶችን በስንጠረዥ መልክ እንዲያስፍሩ በማድረግ ግንዛቤያቸው ማረጋገጥ ይቻላል።

ደረጃ ሦስት

ማጠናከሪያ (Consolidation)

ቃላትን በዕቅድ ማስተማር የመጨረሻ ደረጃ ውስጥ የተለያዩ ነጥቦች ሊካተቱ ይችላሉ።

1. ችግር ፈቺ ተግባራት፦ በርካታ የሆኑ ችግር የመፍቻ ተግባራት አሉ። ተመራጭ የሚሆነው ግን የተማሪዎችን ችሎታ ያገናዘበ ተግባር መምረጥ ነው። ለምሳሌ የሳምንቱን የቴሌቭዥን ፕሮግራም እንዲመዘግቡ በማድረግ አዳዲስ ቃላት የማወቅ ግንዛቤያቸውን ማረጋገጥ ይቻላል።
2. **ግልጽነትን የተላበሰ አቀራረብ፦** ይህ የሚመለከተው የተለያዩ ነገሮችን በማቅረብ ደረጃ እንዲሰጧቸው ማድረግን ነው። በዚህ ጊዜ ተማሪዎች የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀም ደረጃ የመስጠት፣ የመተርጎምና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በግልጽ ሊያስፍሩ ይችላሉ። በዚህም የአዳዲስ ቃላትን ፍች እንደተገነዘቡ ማረጋገጥ ይቻላል።
3. ውይይት፦መምህሩ የተወሰኑ የቃላት ምድቦችን በመስጠት ማወያየት። ተማሪዎች እርስ በርስ በሚያነሷቸው ጥያቄዎችና መልሶች የተለያዩ ገጠመኞችን፣ ዕውቀቶችን፣ አመለካከቶችን ሊለዋወጡ ይችላሉ። ለምሳሌ፦ አዲሱ ቃል በህመም ምልክቶች (ስሜቶች) ላይ ከሆነ ጉንፋን፣ ራስ ህመም... በማለት ሊዝረዝሩ ይችላሉ። እነዚህን ጉዳዮችን አንድ ሐኪም ሌላው በሽተኛ በመሆን በጨዋታ መልክ ማቅረብ ይቻላል።
4. **ታሪክ ወይም አጭር ምልልስ መፃፍ፦** መምህሩ ከ10–15 የሆኑ ቃላትን በመስጠት ቃላቱን በትረካ ወይም በምልልስ መልክ እንዲያቀርቡ በማድረግ ቃላትን የመገንዘብ ችሎታቸውን ማረጋገጥ ይቻላል።

2. ያለ ዕቅድ ቃላትን ማስተማር

Seal Bernard (1991) እንደሚሉት ይህ የማስተማርያ ስልት መምህሩ ካለምንም በቂ ዝግጅት ቃላትን በገለጻ የሚያስተምርበት ስልት ነው። በዚህ ስልት መምህሩ አዳዲስ ቃላትን ሲያስተምር የሚከተላቸው ቅደም ተከተላዊ ደረጃዎች አሉ። የእነዚህ ደረጃዎች ስያሜ በዕቅድ ቃላትን ከማስተማር ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው። ነገር ግን ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴያቸው ስለሚለያይ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. ሃሳብን ማስተላለፍ፡- በዚህ ውስጥ በጣም በርካታ የሆኑ ከአዲሱ ቃል ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ምሳሌዎችን፣ አማራጮችን ... መጥቀስ ይቻላል። ለዚህም ተመሳሳይ ቃላትን፣ ተረታ ተረቶችን የተለያዩ ጉዳዮችን በማንሳት የቃሉን ጽንሰ ሐሳብ ለማስረጽ ይሞክራል።
2. የግንዛቤ ማረጋገጫ፡- ይህ ደግሞ መምህሩ ተማሪዎች የቃሉን ፍች በትክክል መገንዘባቸውን የሚያረጋግጡበት ክፍል ነው። ቀልድ መሰል ነጥቦች የተቀላቀለበት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች በተከተታይ የሚጠየቁበት ደረጃ ነው። መምህሩም ከተማሪዎች ትክክለኛ የሆነ ተከታታይነት ያለው ምላሽ ካገኘ የአዲሱን ቃል ፍች ተገንዝበውታል ለማለት የሚያስችል ድምዳሜ ላይ ይደርሳል።
3. ማጠናከሪያ (መደምደሚያ)፡- በዚህ ውስጥ መምህሩ ማጠናከሪያ የሆኑ ነጥቦችን ያነሳል። ይኸውም ከተማሪዎች ልምድ፣ ገጠመኝ እና ፍላጎት ጋር የሚያያዙ ሌሎች ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቃሉን ፅንሰ ሐሳብ ለማዳበር ይሞክራል።

ከላይ ያየናቸው ቃላትን ካለዕቅድ ለማስተማር የሚረዱ ደረጃዎችን በክፍል ውስጥ ለማስተማር ሲሞክር የሚከተለውን ዓይነት ገፅታ ይኖረዋል (CelceMurcia 1991)። ቅድሚያ መምህሩ አዳዲስ ቃል ይመርጣል። ለምሳሌ "አሰልቺ" (boring) ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልጽ በመጠየቅ የሚከተሉትን ደረጃዎች ይተገብራል።

ደረጃ አንድ

መምህር : (ለክፍሉ) ወደ ፊልም ቤት በምትሄዱበት ጊዜ አንዳንዴ የሚታየው ፊልም አስደሳች አይሆንም። እንዲያውም ሂዳችሁ ተኙ የሚያሰኝ ሊሆን ይችላል። (መምህሩ በዚህ ጊዜ እጆን አፉ ላይ በማድረግ ለማዛጋት ይሞክራል።) ፊልሙም በጣም አሰልቺ ነው። ወይም መምህራችሁ አልፎ አልፎ ሲናገር በጣም በዝቅተኛ ድምጽ ከሆነና ቀልድ ቢጤ ሳይጨምር ቢያስተምር መምህሩ ራሱ አሰልቺ ነው።

ደረጃ ሁለት

መምህር: (ለአንድ ተማሪ) አሰልቺ መምህር ትወዳለህ?
(ለሁለተኛው ተማሪ) ይህ ትምህርት አሰልቺ ነው?
(ለሦስተኛው ተማሪ) ይህ መጽሐፍ ያሰለቻል?
(ለአራተኛው ተማሪ) አንተ አሰልቺ ሰው ነህ?
(ለአምስተኛው ተማሪ) እኔ አሰልቺ መምህር ነኝ?

ደረጃ ሦስት

መምህር፡ (ለክፍሉ) በክፍሉ ውስጥ በመንቀሳቀስ ከአጠገቡ የሚገኙትን ተማሪዎች የሚያሰለች የዕረፍት ቀን ነው ያሳለፋችሁት? መልሳቸው «አዎ» ከሆነ ለምን? (በክፍሉ ጫጫታ፣ ሁካታ ... ይኖራል) ሌላውን ተማሪ በቴሌቪዥን ምን አየህ? አሰልቺ ነው ብለህ ታስባለህ? (ማጉረምረም ሊኖር ይችላል።)

CelceMurcia (1991) እነዚህን ደረጃዎች በርካታ መምህራን በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉንም ተማሪዎች በጅምላ በአንዴ በመጠየቅ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ያቆማሉ። ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎች የሚጠየቁበትን ስልት በመንደፍ መምህሩ የቃላትን ጽንሰ ሐሳብ ማስገንዘብ ይኖርበታል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የማቀረቢያ ስልቶች በምሁራኑ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የተጠቆሙ ናቸው። በእርግጥም የማቅረቢያ ስልቶቹ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ነገር ግን እነዚህን ስልቶች ተጠቅሞ ትምህርቱን ለማቅረብ ሲሞክር ክፍል ውስጣዊ ሁኔታዎች ላይፈቅዱ ይችላሉ። ስለዚህ መምህሩ ከዚህ ላይ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት ይመከራል። ይህም ማለት እንደሁኔታው አመቺነት እየመረጠ እንዲጠቀምባቸው ነው። Celce Murcia (1991) ይህንን ሲያስረግጡ ቃላትን የማስተማሪያ ስልቶች እነዚህ ብቻ አለመሆናቸውን በመጥቀስ ውጤታማ የሆነው የማስተማሪያ ስልትም ከሁሉም ዓይነት የማስተማሪያ ዘዴ የተውጣጣ ስልት ተመራጭነት እንዳለው አስገንዝባለች።

2.3.5 ቃላትን ማስታወስ

የስነልቦና ምሁራን እንደሚሉት መማር በአጭር ጊዜ ብዙ መረጃን ማጠናቀር ነው። ይህ መረጃ ሲጠናቀር ተከታታይነትና ድግግሞሽነት ያለበት፣ ያለምንም አደናቃፊ ሁኔታዎች የተከናወነ ከሆነ እንዳይረሳ ያደርገዋል።

ስለመርሳት ሲታሰብ የማስታወስ ሁኔታዎችን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል /Gairns and Redman 1986፣ 371/

1. የቅርብ ትውስታ /short term memory/
2. ዘላቂ ትውስታ / long term memory/

የቅርብ ትውስታ የሚያመለክተው አንድ ነገር ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በአእምሮ ውስጥ ማቆየት ሲሆን፣ ይህም ለደቂቃ፣ ለሳምንት ሊሆን ይችላል። ለዘላቂነት ማስታወስ

የማያልቅ አዲስ መረጃን መዝግቦ መያዝ ነው። ለዚህ ችሎታ ግን በቂ ድግግሞሽ አስፈላጊ ነው።

ስለ ቋንቋ ስናስብ የአንድ ቃል ትርጉም፣ ንበት፣ እርባታ፣ ቅርፅ፣ አገባብ በአእምሮአችን ውስጥ ተደራጅቶ ይቀመጣል። Brown and Mcvell (1966) እንደገለፀት አእምሮአችን አንድን ቃል ለማስታወስ ተደራጅቶ የሚቀመጥበት ሁኔታ አንዳለ ነው።

ለምሳሌ፡- ፍራፍሬ የሚለው ቃል ቢጠራ፣ አእምሮ ፍራፍሬ በሚለው ዋና ቃል ስር አደራጅቶ ያስቀመጠውን ቃል በሙሉ እናስታውሳለን። ከፍራፍሬ ውስጥ የመጀመሪያው ፊደል በ«ብ» የሚጀምር ቃል ቢባል "ብርቱካን" የሚለውን ቃል ማስታወስ ይቻላል። በዚህ ሁኔታ ቃላት በአእምሮ ውስጥ ተደራጅተው እንደሚቀመጡ ምሁራን በአስረጅ አሳይተዋል።

የተማርናቸውን ቃላት እንዴት እንረሳለን?

መርሳት አንድን ነገር በሚገባ አለመገንዘብን ሊያመለክት ይችላል። የተማርነውን ለማስታወስ ነገሩን መደጋገምና በተግባር ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው ካለበለዚያ ቀስ በቀስ ሊረሳ ይችላል።

Allen (1983) በ19ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የቃላት ትምህርት አሰጣጥ ችግር የሚታይበት ነበር። የቃላትን ትርጉም ማወቅ አንድን ቋንቋ ማወቅ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ቃላት በደረቁ ይጠኑ ነበር። ይሁን እንጂ የቃላትን ትርጉም ብቻ ማወቅ አንድን ቋንቋ ለማወቅ በቂ ስለማይሆን ቃላቱ በዐ. ነገር ውስጥ ገብተው ከአገባባቸው አንፃር ያላቸውን ፍቺ ማገናዘብ አስፈላጊ እንደሆነ ያሰረዳሉ። የተማርነውን ቃል እንዴት እንረሳለን ስንል ምሁሩ የገለጿቸውን ልዩ ልዩ ምክንያቶች ከዚህ ቀጥሎ ለማየት ይሞክራል።

- **ቃላትን በደረቁ ማስተማር**:– አንድ ቋንቋ ሲጠና ቃላትን ብቻ በደረቁ ማስተማር የቃላትን ትርጉም እንዲረሳ ያደርጋል። ቃላትን በደረቁ ከማስተማር በዐ.ነገር ውስጥ ከነአገባባቸው ማስተማር እንዳይረሱ ያደርጋል።
- **የአፍ መፍቻ ቋንቋውን ቃል በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ያለውን አቻ ፍቺ አለመገንዘብ**:– ቃላት በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያለውን ትርጉም ከታላሚው ቋንቋ አቻ ፍቺ ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በአንድ ቋንቋ ውስጥ አንድ ቃል ያለው ፍቺ በሌላ ቋንቋ ፍፁም ተመሳሳይ ነው ማለት አይቻልም።

  አስረጅ፡- በእንግሊዝኛ - garden - የአትክልት ቦታ
  በእስፓኒሽ - Jardin - የአበባ መትከያ ቦታ

Allen (1983) በመቀጠል አንደገለፀት የቃላትን ፍች ለመረዳትና እንዳይረሳም ለማድረግ ሶስት ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል በማለት ይገልጻሉ::

- ቃላትን በደረቁ ከማስተማር በአገባባቸው ማስተማር የበለጠ ጠቀሜታ አለው::
- ከአገባቡ በፊት ብዙ ቃላትን ቀድሞ ማስተማር ለስህተት ስለሚዳርጋቸው፣ ቀድሞ ብዙ ቃላትን ከማስተማር መቆጠብ ነው::
- ቃላትን በክፍል ውስጥ ብቻ እንዲማሩ ከማድረግ በተግባር ከልምድ እንዲማሩ ማድረግ የበለጠ ጠቀሜታ አለው::

Ur (1996) በበኩሉ እንደገለፀው አንድን ቃል ከሌላው በተለየ መንገድ የምናስታውስበት ብዙ ምክንያት ሊኖር ይችላል:: ከነዚህም ምክንያቶች መካከል ሶስቱ የሚከተሉት ናቸው::

1. የቃሉ ባህርይ
2. የተማርንበት ሁኔታ
3. የተማርንበት ዘዴ ናቸው::

አስረጅ:- የያታን ልዩነት ለማሳየት የሚችል ስዕል በማቅረብ እንዲለዩ ማድረግ ሊሆን ይችላል:: በቀጥታ የቃሉን ትርጉም ከመንገር በስዕል በማሳየት ልዩነቱን ማስገንዘብ ይቻላል:: Gairns and Redman (1986) በበኩላቸው ሲገልፀ ቃላት እንዳይረሱ ለማድረግ በምን ዓይነት መንገድ ማስተማር እንዳለብን በሚከተለው ሁኔታ ያመለክታሉ::

1. ትርጉም ያለው ልምምድ በማድረግ ማስተማር:– ቃላትን በምናስተምርበት ጊዜ ትርጉም ያለው ልምምድ ማድረግና ከተማሪዎች ተሞክሮ ጋር በማዛመድ እና የራስን ፈጠራ በማከል ማስተማር አስፈላጊ ነው::
2. ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም ማስተማር:– ቃላትን ለማስተማር ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም አእምሮ ውስጥ ተቀርጾ እንዲቀር ለማድረግ ይረዳል:: በዚህ ሁኔታ ሁሉንም ቃል ለመግለፅ ቢያስቸግርም የተወሰኑትን ለመግለፅ ይረዳል::
3. በመደጋገም ማስተማር:– የተማሩትን ቃል ፍች በቃልም ይሁን በፅሁፍ እንዲደጋግሙት በማድረግ ማለማመድ ይቻላል:: ይህም ልምምድ ለቃሉ ፍች በመስጠት፣ ቃሉ በታላሚው ቋንቋ ያለውን ፍች በመጻፍ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ በመጻፍ እንዲሁም መደበኛ ቅርፅ የሌላቸውን ቃላት በመጻፍ ማሳየት ይቻላል::
4. የተማሩትን ትምህርት እንደገና በማስተማር:–አንድን ቃል ከተማሩ በኋላ፣ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከተጠቀሙበት ሊረሱት ይችላሉ:: ስለዚህ ያንን ቃል በተለያየ መልክ እንደገና እንዲከልሱት ማድረግ ያስፈልጋል::

Gairns and Redman (1986) Peter Russellን ጠቅሰው እንደገለፀት ክለሳውን በዚህ መንገድ ማከናወን ይቻላልል፡

1. ከዕለቱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ለአምስት ደቂቃ መከለስ፡፡
2. ከአንድ ቀን በኋላ እንደገና መከለስ
3. ከአንድ ሳምንት በኋላ እንደገና ማስታወስ
4. በመጨረሻም ከወር በኋላ እና ከስድስት ወር በኋላ መድገም ይቻላል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ተማሪው የተማረውን ቃል እንዳይረሳ ማድረግ ያለበትን ክንውን Gairns and Redman /1986/ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

ሀ. በዕሁፍ መዝግቦ ማስቀመጥ፡– ተማሪው የተማረውን ቃል እንዳይረሳ ቃሉን በመጻፍ የቃሉን ክፍልና የሚሰጠውን ፍቺ ከፊት ለፊቱ በራሱ ቋንቋ መዝግቦ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ተጨማሪ ምሳሌዎችን በማካተት መመዝገብና፣ ትንሽ ባዶ ቦታ በመተው ሌላ ጊዜ ተጨማሪ ተያያዥነት ያለው ምሳሌ ሲኖር መጻፍ ይቻላል፡፡

ለ. የግል ማስታወሻ አያያዝ መጠቀም፡–ቃላትን በየጎራው በመክፈል በአንድ ጎራ ስር የሚዘረዘሩትን በማስቀመጥ መዝግቦ መያዝ ይቻላል፡፡

ሐ. በስዕል መልክ ማስቀመጥ፡–ቃላትን ያላቸውን አንድነትና ተዛምዶ በዛፍ መልክ በማስቀመጥ ዘርዝሮ በዕሁፍ ማሰቀመጥ ይቻላል፡፡

መ. በፊደል ተራ መዝግቦ ማስቀመጥ፡– መመዝገቢያ ደብተር ማዘጋጀትና የተማሩትን ቃል በፊደል ተራ መዝግቦ መያዝ ለማስታወስ ይረዳል፡፡

ሠ. መሰየም፡– ተማሪዎች የተማሩትን ቃል ፍቺ ከነገሩ ጋር በማገናኘት በቁሳቁሱ ላይ በመጻፍ እና በመለጠፍ ለማስታወስ መሞከር ይችላሉ፡፡

ቃላትን እንዳንረሳ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ይቻላል፡፡ Yorkey /1982/ እና Nation /1980/ን ዋቢ በማድረግ Murcia /1991/ እንዳመለከቱት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቃላትን በካርድ በመመዝገብ ንበቱን፣ ፍቺውን እንዲሁም ተመሳስሎውን በመመዝገብ በፊደል ተራ መደርደር አንዱ ዘዴ እንደሆነ ይመክራሉ፡፡

Murcia/1991/ Cohen and Aphek /1980/ን ዋቢ በማድረግ የተገለፀት ደግሞ ከላይ የተገለፀውን መንገድ ከመከተል በተሻለ መልኩ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን ሲማሩ ከመጀመሪያ ቋንቋቸው ተመሳሳይ ከሆነ ድምፅና ቃል ጋር በማዛመድ መማራቸው አይረሴነት እንደሚፈጥር ይመክራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከገለፃው ለመረዳት እንደሚቻለው የቃልን ትርጉም በተናጥል መማር በቋንቋው ተግባቦትን ለመፍጠር አያስችልም። ስለዚህ የምናውቃቸውን ቃላት አስታውሰን በቋንቋው ለመጠቀም እንችል ዘንድ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው።

2.4 በቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተለዋዋጮች

ETP (1994:2-3) እንዳሰፈረው ለትምህርት ጥራት መውደቅ በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ የሆኑት ችግሮች በቂ የሆነ የመምህራን ስልጠና አለመኖር፣ በክፍል ውስጥ ከሚገባው በላይ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ መፅሐፎችና የተለያዩ የማስተማሪያ ማቴሪያሎች እጥረት የሚሉት ናቸው። እነዚህ ችግሮች በቋንቋ ትምህርት በተለይም በቃላት ትምህርት ሂደት ውስጥ ያላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው።

የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች በተለይም ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት ሲገልፁ ቆይተዋል። ስለዚህ ይህን በጣም አስፈላጊ የትምህርት ይዘት ለተማሪዎች ለማቅረብ ሲፈለግ በጣም አስፈላጊ እና ተገቢ የማቅረቢያ ስልቶችን መጠቀም የግድ ነው። ነገር ግን የማቅረቢያ ዘዴዎች እና ስልቶች ተገቢነታቸው የማያጠያይቅ ሆኖ ቢገኝም በተገቢው ወቅት ተገቢውን ዘዴ እና ስልት ለመጠቀም የማያስችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ማጋጠማቸው የማይቀር ነው። እነዚህ ችግሮችም West (1963) ጠቅለል ባለ መልኩ ከመምህሩ አንፃር፣ ከተማሪው አንፃር እና ከማስተማሪያ ግብዓቶች አንፃር ሊታዩ እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

ሀ. ከመምህሩ አንፃር

የትምህርት ዘርፉ ለተማሪዎች በሚቀርብበት ወቅት ከራሱ ከመምህሩ አንፃር የሚታዩ ችግሮች ይኖራሉ። ይህም ማለት መምህሩ ራሱ የሚፈጥረው ችግር ወይም ሌሎች ምክንያቶች ባሳደሩበት ተፅዕኖ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ከመምህሩ አንፃር ሊታዩ የሚችሉ ችግሮችም አመለካከት፣ የአቅም ችግር፣ የክፍለ ጊዜ ጫና ተጠቃሾች ናቸው።

1. **የአመለካከት ችግር**:– መምህራን መምህር ከመሆን ጀምሮ የአማርኛ ቋንቋን ወይም የቃላት ትምህርትን ለማስተማር፣ እንዲሁም አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመጠቀም ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል። Papalia and Sally (1985) አመለካከትን ሲያስረዱ ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ነገር አወንታዊ ወይም አሉታዊ አተየይ የሚሰጥበት እንደሆነ ነው። በአንድ ነገር ላይ አሉታዊ አመለካከትን ለመያዝ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም

ይህ የመምህራን አመለካከት በተለይ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መልኩ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው።

የቋንቋ መምህራን ከቃላት ትምህርት ዘርፍ ይልቅ የሰዋሰውን ትምህርት ዘርፍ ለማስተማር የላቀ ዝንባሌ እንዳላቸው (Richards 1985:176) በሰፊው ለማስገንዘብ ሞክረዋል። ስለዚህ የቃላትን ትምህርት አስፈላጊነት ያላመነ መምህር ሁልጊዜ ለሌሎች የቋንቋው ዘርፎች ትኩረት በመስጠት ሙሉ ጊዜውን ያጠፋል ማለት ነው። እንግዲህ ቃላት ለሌሎች የቋንቋ ዘርፎች ሁሉ መሠረት ከሆኑ ቃላትን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የቋንቋውን ዘርፎች መምህሩ አላስተማረም ማለት ይቻላል።

2. የአቅም ችግር:– ይህ ችግር በቋንቋ ትምህርት ወቅት ከችግሮች ሁሉ የከፋ ችግር የሚባለው ነው። እንደሚታወቀው በሃገሪቱ በ1994 በወጣው የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ መሠረት የትምህርት እርከኖች በውል ተለይተዋል። ለእነዚያ የትምህርት እርከኖች ደግሞ ለደረጃው የሚመጥኑ መምህራን በየትምህርት ዓይነቶቹ ሰልጥነው እንዲመደቡ የሚል ነው። ስለዚህ የአጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ማጠቃለያ የትምህርት እርከን ማለትም ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ የክፍል ደረጃዎች የሚመደቡ መምህራን በትምህርት ዓይነቱ በዲግሪ ደረጃ ሰልጥነው የወጡ መሆን አለባቸው።

ነገር ግን የመጀመሪያ ዲግሪ ሳይኖራቸው፣ በቋንቋ ዘርፉ ሳይመረቁበት በተለይ የአማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩባቸው አካባቢዎች የክፍለ ጊዜ ጫና የሌለባቸው እና በሌላ የትምህርት ዘርፍ የተመረቁ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ስለተናገሩ ብቻ የሚመደቡበት ሁኔታ ይታያል። በዚህ ወቅትም የተመደቡት መምህራን ከተማሪዎቹ የተሻሉ ሆነው የማይገኙበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። ምክንያቱም የትምህርት ዓይነቱ ባህሪ የሚጠይቀው የማስተማሪያ ዘዴ አለና ነው።

ሌላው ደግሞ በቋንቋ ዘርፉ በመጀመያ ዲግሪ ደረጃ የተመረቁ መምህራንም ቢሆኑ ከከፍተኛ ተቋም ተመርቀው የወጡበት ዘመንም ሩቅ ከሆነ በየጊዜው በፈጣን ሁኔታ ለሚለዋወጠው የቋንቋ ትምህረት የማስተማሪያ ዘዴ እና ብልሃት ባዕድ ሊሆኑ ይችላሉ። ለእነዚህ መምህራን በሥራ ላይ ሥልጠና ወይም አጫጭር ስልጠናዎች ካልተሰጧቸው ድሮ እነሱ የሚያውቋቸውን ዘዴዎች ብቻ መከተላቸው አይቀሬ መሆኑን Alemu (1994:49) በሰፊው ያብራራሉ። ይህ ሲባል ግን መምህራን በሥራ ቆይታቸው በርካታ ነገሮችን መማር እንደሚችሉ መዘንጋት የለበትም። ማስተማር መማር ነው የሚባለውም ለዚህ ነው።

ከላይ ከተነሳው ሃሳብ በተቃራኒ ደግሞ በሞያው ተመርቀው የሚወጡትም መምህራን ቢሆኑም ከተቋሙ ከወጡ በኋላ የሚገጥማቸውን ነባራዊ ሁኔታ በትምህርት ካገኙት ሳይንሳዊ መርህ ጋር የማስታረቅ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። ይህም ማለት ሳይንሱ እና ተጨባጩ ሁኔታ ላይጣጣሙ ስለሚችሉ፣ በተጨባጭ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያላቸው ጉዳዮች እንደ የተማሪው ዕድሜ፣ የዕውቀት ደረጃና ፍላጎት አንባር ይዘትን መርጦ እና የማቅረቢያ ዘዴን እንደሁኔታው ለዋውጦ ለማቅረብ አስቸጋሪ ይሆናል። ምክንያቱም Nunan (1988:10) እንደሚያስረዱት ከሆነ ለተማሪው የሚቀርበው ይዘት የተማሪውን ዳራ እና ፍላጎት ያሟላ መሆን ይኖርበታል።

በአጠቃላይ ከመምህሩ አቅም አንባር በትምህርት ዘርፍ አለመመረቅ፣ በትምህርት ዘርፉ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚመጥን ስልጠና አለማግኘት፣ የሥራ ልምድ ወይም ተሞክሮ እጥረት፣ ከአዳዲስ የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች ጋር አለመተዋወቅ ለቃላት ትምህርት አቀራረብ በእንቅፋትነት የሚፈረጁ ናቸው።

3. **የክፍለ ጊዜ ጫና**:– ማንኛውም ሥራ በአግባቡና በጥራት ይሰራ ዘንድ ሥራው እጅግ አድካሚና አሰልቺ መሆን የለበትም። ስለዚህ አንድ መምህርም በሳምንት የሚያስተምረው ክፍለ ጊዜ እጅግ ከበዛ በተለይ በቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። Wright (1989:136) ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርትን በሚማሩበት ወቅት ለማነቃቂያነትና ትምህርቱን ግልፅ ለማድረግ ስዕሎች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይናገራሉ። እነዚህ ስዕሎችም ሆኑ ሌሎች የትምህርቱ ማቅረቢያ ስልቶች ከመምህሩ አእምሯዊ ፈጠራ የሚገኙ ናቸው። እነዚህን ዘዴዎች ለመፍጠር እና ለማዘጋጀት መምህሩ ጊዜ ስለማይኖረው እና የተማሪዎችንም ፍላጎት በማጥናት እንዲሳተፉ አድርጎ ምጋቢ ምላሽ ስለማይሰጣቸው ትምህርቱን እንዲሁ እንደተመቸው ያቀርበዋል። በዚህ ሁኔታ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ያለው እድል የመነመነ ይሆናል።

ለ. ከተማሪዎች አንፃር

ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ለቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ የላቀ ነው። እንዲያውም የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት ስነ ዘዴ ተማሪው እያደረገ ወይም እየሰራ ከሚያደርገው እና ከሚሰራው እንዲማር፣ መምህሩ ግን ሁሉን ነገር አቀባይ ሳይሆን እንደ አስተባባሪ እና እንደ አቅጣጫ ጠቋሚ መሆን እንዳለበት Alemu (1994:1) ያስረግጣሉ። ይህ እንዳይሆን ግን ከተማሪው አንፃር በርካታ ችግሮች ይገጥማሉ። ከችግሮች ውስጥ የተወሰኑትን እንደሚከተለው ለማየት ይቻላል።

1. **የአመለካከት ችግር**:– የአመለካከት ችግር ሲባል ለአንድ ነገር ያለን አዎንታዊው ሳይሆን አሉታዊውን እሳቤ ነው። ለየትኛውም ዓይነት አመለካከቶች መፈጠር ምክንያቶቹ በርካታ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ይህ የተማሪዎቹ አመለካከት በቋንቋው ዘርፍ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። አመለካከታቸው ከቋንቋው አንፃር፣ ከቃላት ትምህርት አንፃር፣ ከመምህሩ አንፃር እና ከመማሪያ መፅሐፍ አንፃር ሊታይ ይችላል። ከተዘረዘሩት ውስጥ በአንዱ ወይም በሁሉም ላይ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው በትምህርቱ ወቀት እራሳቸውን ላለማሳተፍ ይወስናሉ ወይም ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ይሆናል።

2. **የተማሪዎች ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት**:– Kassie (1995) የተለያዩ ምሁራንን እየጠቀሰ እንደሚያብራራው ከሆነ ሰፊ ክፍል ለሚለው ወጥ የሆነ ብያኔ የለውም። ቁጥሩ ምን ያክል የሆነው ነው ሰፊ ክፍል የሚባለው? የሚለውን እንደየሀገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ እና እንደ ትምህርቱ ባህሪ ይገለፃል ይላል። በእርግጥም ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ለቃላት ትምህርት የተማሪዎች መጠን ከበዛ አስቸጋሪ የሚሆንበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ይህም ማለት በዋናነት ተማሪ አሳታፊ የሆነ አቀራረብን ለመከተል ያዳግታል። West (1963:6) በአንድ ክፍል ውስጥ ከ30 በላይ ተማሪዎች መገኘት የቋንቋ ትምህርትን አስቸጋሪ ያደርገዋል ይላሉ።

Brown (1994:416) የሰፊ ክፍልን አስቸጋሪነት እንደሚከተለው ለማስረዳት ሞክረዋል። መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ምጋቤ ምላሽ አነስተኛ መሆን፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሰፊው እየተሳተፉ የሚማሩበትን አጋጣሚ ስለሚያጠብ፣ መምህሩ የእየንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት፣ ችሎታ እና ተሳትፎ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርግ አሉታዊ ተፅዕኖው በቀላሉ አይገመትም።

ስለዚህ በቃላት ትምህርት ወቅት እያንዳንዱን ተማሪ እየሰራ እና እያደረገ እንዲማር ከማድረግ ይልቅ ሁሉንም የክፍሉን ክንውን መምህሩ በመኖፖል እነዲቆጣጠረው ይጋብዛል። West (1963:6) ሁሉም የክሂል ትምህርቶች ግባቸው ትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀምን ማሳደግ ነው። በመሆኑም ክሂልን መማር የሚቻለው በልምምድ ነው። መምህሩ በዚህ ወቅት አጋዥ በመሆን ልምምዱን ያሳያል፣ እንዴት እንደሚለማመዱ ይጠቁማል፣ ከዚያም ለልምምዳቸው ምጋቤ ምላሽ መስጠት እንጂ በቃል ማነብነብ እንደሌለበት ያትታሉ። እናም የዚህ በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር ከሚገባው በላይ መጨመር ለትምህርቱ ይዘት አቀራረብ መሰናክል ይሆናል።

ሐ. ከማስተማሪያ ግብዓቶች አንፃር

የማስተማሪያ ግብዓቶች ለቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ከመምህሩ ቀጥሎ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው::"አንድ ሰው አይቶ ሲያደርግ የሚማረውን አዳምጦ ከሚማረው በላቀ ሁኔታ በአእምሮው ቀርፆ ያስቀምጣል" Nasr (1979:114):: ጥቅሱ የሚያስገነዝበው ነገር ቢኖር 'ማየት ማመን ነው' የሚለውን የአማርኛ አባባል ነው:: በመሆኑም የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የቃላትን ትምህርት ለማስተማር ያላቸውን ፋይዳ ከዚህ አንፃር ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል::

ሺመልስ (1993፣16) Pratt (1994)ን በመጥቀስ ለቋንቋው ይዘት የተሳካ ትግበራ እንዲይኖር ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ነገሮች መካከል ተገቢና ብቃት ያላቸው የማስተማሪያ መሣሪያዎች አቅርቦት አለመሟላት እንደሆነ ይገልፃሉ:: ይህም ሲባል የመማሪያ መፅሐፍቱ ለእያንዳንዱ ተማሪ አለመዳረስ፣ ስዕሎች እና ቁሳቁሶች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፣ እነዚህ የመርጃ መሣሪያዎች ቢገኙም እንኳ በመምህሩ እና በተማሪው የሚሰሩበት ሁኔታ አለመመቻቸት፣ የትምህርት ቤቱ የማቴሪያል እና የገንዘብ አቅርቦት አለመኖር የሚሉት ናቸው::

ሌላው ከማስተማሪያ ግብአቶች አንፃር ሊነሳ የሚችለው ነገር መሣሪያዎቹ በተገኙበት ሁኔታም ቢሆን ይህንን የቃለት ትምህርት ከማስተማር አንፃር ያላቸው ፋይዳ ምን ያክል ነው? የሚለው ጥያቄ ነው:: Richards እና Rodgers (1986:416) የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ተገቢነቱ የሚመዘነው ይዘቶቹን ማቅረብ፣ ይዘቶቹን ማለማመድ፣ በተማሪዎች መካከል ተግባቦት እንዲፈጠር ማመቻቸትና ተማሪዎች ያለመምህሩ እገዛ ይዘቶችን እንዲለማመዱ ማስቻል እንደሆነ ይገልፃሉ:: ሌሎች የመርጃ መሣሪያዎችም ከተገቢነታቸው አንፃር ታይተው ጥቅም ላይ ከዋሉ በተለይ ስዕሎች ሚናቸው የላቀ መሆኑን ያብራራሉ:: የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎች ከብቃት እና ከተገቢነት አንፃር ተመዝነው ለቃላት ትምህርት ማቅረቢያነት ስራ ላይ ካልዋሉ ትምህርቱ በተገቢው ሁኔታ ተከናውኗል ለማለት ያስቸግራል::

2.5 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት

ከዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ጋር በቀጥታ የሚመሳሰሉ ሥራዎች ባይኖሩም በተወሰነ መልኩ የሚዛመዱ ጥናታዊ ፅሁፎች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ ሲሳይ (1990)፣ አንበሴ (1993)፣ የሺጥላ መንግስቴ (1997)፣ እሸቱ አጋ (1997) ትንሳኤ (1988) ይጠቀሳሉ::

ትንሳኤ በ1988 ዓ.ም "የአማርኛ ቃላት አፈታትን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ አቅርቧል:: የጥናቱ ዓላማ ከ1980 እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ በተዘጋጁት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ

ፈተናዎች ናሙና በመውሰድ የቀረቡትን የቃላት ጥያቄዎች መገምገም ነበር። በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የደረሰበት ውጤትም የቃላት ጥያቄዎች አቀራረብ አውድን ያልተከተሉ፣ ግልፅነት የሌላቸው፣ አቀራረባቸው የማስተማሪያ መጽሐፉን መሠረት ያላደረጉ መሆኑን አረጋግጧል።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ እና የትንሳኤን ሥራ የሚያመሳስላቸው በቃላት ላይ ማተኮራቸው ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የትንሳኤ ስራ የሚያተኩረው በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የሚቀርቡ የቃላት ጥያቄዎችን መመርመረ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ የቃላት ትምህርትን መምህሩ እንዴት በክፍል ውሰጥ ያቀርበዋል የሚለውን በመፈተሽ ላይ ማተኮሩ ለየት ያደርገዋል።

የሲሳይ ተበጀ በ1990 ዓ.ም "በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሥራ ላይ ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት" በሚል ርዕስ የቀረበው የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሑፍ ሲሆን ዓላማው በ1985 ዓ.ም የታተመውን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፅሐፍ ከቃላት ትምህርት አቀራረብ አንፃር መገምገም ነው። በጥናቱ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከቃላት ትምህርት አጠቃቀም ይልቅ በፍቻቸው ላይ የተመሰረተ መሆኑን አመልክተዋል። የሲሳይን ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በሚሰራበት የ9ኛ ክፍል መፀሐፍ ላይ ጥናቱን መመስረቱ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሚማሩባቸው በትግራይ ክልል በሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ ማተኮሩ በሁለቱ ጥናቶች መካከል ቀጥተኛ ዝምድና አለመኖሩን ያሳያል።

ሌላው ከዚህ ጥንታዊ ፅሑፍ ጋር ተዛማጅነት ያለው ጥናት የአንበሴ በቀለ በ1993 ዓ.ም "በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህረት አቀራረብ ትንተና" በሚል ርዕስ የቀረበው ነው። ትኩረቱ ለኦሮምኛ አፈፈቶች የተዘጋጀ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ ያለውን አቀራረብ የሚፈትሽ ሲሆን የመምህራን የክፍል ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ጉዳይ ግን ከጥናቱ ርዕይ ውጭ ነው። ይህን ጥናትና የአንበሴን ስራ የሚያመሳስላቸው በቃላት ላይ ማተኮራቸውና ኢ አፈፈቶች ላይ መሆኑ ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ አንበሴ ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው የመማሪያ መፅሐፍ ማተኮሩ እና፣ ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ ደግም ትኩረቱ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር መሆኑ ነው።

"በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ውስጥ የቃላት ትምህርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል የየሽጥላ መንግስቴ ሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ፅሑፍ የሆነው ሰራ ይዞት የተነሳው ዓላማ በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህረት ይዘት አመራረጥን፣ አደረጃጀትንና አቀራረብን በመመርመር የትምህርቱን ጠንካራና ደካማ ጎን መለየት እንዲሁም ጠንካራ ጎኖቹ ስለሚጠናከሩበት ሁኔታ አስተያየት መሰንዘር ነው። ከዚህ ጥናት ጋር የየሺጥላን ሥራ የሚያመሳስለው በቃላት ላይ ማተኮሩና የክፍል ደረጃው ሲሆን የሚለየው ደግሞ ይህንን የቃላት ትምህርት ከመምህሩ አንባር ሳይሆን ከመፅሐፉ አንባር ግምገማ ማድረጉ ነው።

በስተመጨረሻ የሚነሳው ደግሞ እሸቱ አጋ (1997) "በአዲስ አበባ መስተዳደር ክልል በሚገኙ ሦስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ግምገማ" በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ፅሑፍ ነው። በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ የተገኘውም ውጤት መምህራን የቃላት ትምህርቱን ሲያቀርቡ አብዛኛው ትኩረታቸው በፍቺ እና በመዋቅር ላይ እንደሆነና ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎች በሚያዳብሩ መልኩ እንደማይቀርቡ ያሳያል። የእሸቱን ፅሑፍ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የቃላትን ትምህርት አቀራረብ ከመምህራን አንባር ማየቱ ነው። የእሸቱ ጥናት ያካተታቸው ትምህርት ቤቶች ሶስት መሆን፣ ተተኳሪዎቹም ቋንቋውን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚማሩትን ተማሪዎች የሚየስተምሩ መምህራን መሆን እና ይህ ጥናት ደግሞ አራት ትምህርት ቤቶችን በመውሰድ የአማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት የሚመሩትን ተማሪዎች የሚያስተምሩ መምህራንን ተተኳሪዎች ማድረጉ፣ በተጨማሪም በቃላት አቀራረብ ወቅት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተለዋዋጮችን ማካተቱ ለልዩነታቸው ተጠቃሾች ናቸው።

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የተከተለው የአጠናን ዘዴ አይነታዊ እና አሃዛዊን ምርምር ሲሆን መረጃዎችን ለመተንተን የተጠቀመበት አቀራረብ ደግሞ በገለፃ ላይ የተመሠረተ ነው። በገለፃው ላይ የተመሠረተበት ምክንያት መረጃዎችን በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በዕሁፍ መጠይቅ ለመሰብሰብና ለመተንተን የሚያስችል ስለሆነ ነው።

3.1 የናሙና አመራረጥ ዘይት

ይህ ጥናት በትግራይ ክልል የሚገኙትን የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት አቀራረብን የሚያመለክት ሲሆን ቢችልም ከጊዜ፣ ከሰው ኃይልና ከበጀት እጥረት የተነሳ በሰሜን ምዕራብ ዞን ብቻ ለመወሰን ተገዷል። በመረጃ ምንጭነት አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ናሙናዎች ለመምረጥ የተለያዩ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን መጠቀም ተችሏል። የናሙና አወሳሰድ ዘዴዎችም መረጃው የተሟላ እንዲሆን ያላቸው ሚና ሲመዘን እጅግ በጣም ወሳኝ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ለዚህ ጥናት አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ ሰሜን ምዕራብ ዞን በአመቺ ናሙና ከተመረጠ በኋላ በዞኑ ከሚገኙት አራት ትምህርት ቤቶች ደግሞ በእጣ ናሙና ተወስደዋል። እንደሰሜን ምዕራብ ዞን ሁሉ የክፍል ደረጃውም 9ኛ ክፍል በአመቺ ናሙና ሊመረጥ ችሏል። በተመረጠው የክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉም በጥናቱ ሲካተቱ፣ በዚሁ የክፍል ደረጃ በጥናቱ የተካተቱት መምህራን ከሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች መካከል በእጣ ናሙና ሩብ ያህሉ ተመርጠዋል። በናሙናነት ከተመረጡት የመማሪያ ክፍሎች የሚማሩት ተማሪዎች ደግሞ በሥርዓታዊ ናሙና አወሳሰድ ስልት ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል።

3.1.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በሰሜን ምዕራብ ዞን ከሚገኙት ስምንት ትምህርት ቤቶች አራቱን በናሙናነት መምረጥ በማስፈለጉ በእጣ ናሙና፡-

- ሽሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣
- ሐክፈን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣
- እንደባጎና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና
- አዲዳሮ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጀ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል።

3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ክፍል ነው። የናሙና አመራረጥ ዘዴውም በአመቺ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ሲሆን ለዚህም ምክንያቶች፣-

1. አንዳንድ ት/ቤቶች 10ኛ ክፍልን ገና በዚህ ዓመት ማስተማር መጀመራቸው፣
2. የዘጠነኛ ክፍል የመማር ማስተማር ክንውን ከአስረኛ ክፍል በተሻለ እስከትምህርት ዘመኑ መጨረሻ መቀጠሉ የሚሉት ናቸው።

3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በየትምህርት ቤቶቹ ያሉት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቁጥር ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህም በሁሉም በጥናቱ በሚካተቱት ት/ቤቶች የሚያስተምሩ ስድስት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ ተካተዋል።

3.1.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

በናሙናነት የተመረጡት መምህራን ከሚያስተምሩባቸው 71 መማሪያ ክፍሎች መካከል በእጣ ናሙና 1/4 የሚሆኑት 18 የመማሪያ ክፍሎች ለጥናቱ በስራ ላይ ውለዋል። በየመማሪያ ክፍሎቹ ያለው የተማሪ ቁጥር ስርጭት ተመጣጣኝ ባለመሆኑና ለእያንዳንዱ የመማሪያ ክፍል እኩል ድርሻ መስጠት ስለሚያስፈልግ ከየክፍሉ የሥም ዝርዝራቸውን በመውሰድ ተራ ቁጥራቸውን በመጠቀም በሥርዓታዊ ናሙና አንድ አምስተኛ (1/5) የሚሆኑ በአጠቃላይ 190 ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በመነጋገር ተመርጠዋል።

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በቂና አስተማማኝ መረጃ ይገኝ ዘንድ ሁለት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ባገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። እነሱም ምልከታ (በመከታተያ ቅፅና በቪዲዮ ቀረፃ) እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው።

3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

የአቀራረብ ሁኔታን በተጨባጭ ለመረዳትና በቂ የሆነ ግንዛቤ ለማግኘት የክፍል ውስጥ ምልከታ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው Brandt (1981) ያብራራሉ። እንደ Richards and Rodgers (1995) አገላለጽ ከሆነ በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት የክፍል ውስጥ ምልከታ የመምህሩን ብቃትና አቀራረቡን በጥሩ ሁኔታ ማሳየት እንደሚችል ያስረዳሉ። የጥናቱ ዋና ዓላማ የመምህራንን የቃላት ትምህርት አቀራረብ መፈተሽ ሲሆን ይህንን ዓላማ በአግባቡ ለማሳካት ይቻል ዘንድ በዋናነት ለመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጠው ዘዴ

3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ክፍል ነው። የናሙና አመራረጥ ዘዴውም በአመቺ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ሲሆን ለዚህም ምክንያቶች፣-

1. አንዳንድ ት/ቤቶች 10ኛ ክፍልን ገና በዚህ ዓመት ማስተማር መጀመራቸው፣
2. የዘጠነኛ ክፍል የመማር ማስተማር ክንውን ከአስረኛ ክፍል በተሻለ እስከትምህርት ዘመኑ መጨረሻ መቀጠሉ የሚሉት ናቸው።

3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በየትምህርት ቤቶቹ ያሉት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቁጥር ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህም በሁሉም በጥናቱ በሚካተቱት ት/ቤቶች የሚያስተምሩ ስድስት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ ተካተዋል።

3.1.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

በናሙናነት የተመረጡት መምህራን ከሚያስተምሩባቸው 71 መማሪያ ክፍሎች መካከል በእጣ ናሙና 1/4 የሚሆኑት 18 የመማሪያ ክፍሎች ለጥናቱ በስራ ላይ ውለዋል። በየመማሪያ ክፍሎቹ ያለው የተማሪ ቁጥር ስርጭት ተመጣጣኝ ባለመሆኑና ለእያንዳንዱ የመማሪያ ክፍል እኩል ድርሻ መስጠት ስለሚያስፈልግ ከየክፍሉ የሥም ዝርዝራቸውን በመውሰድ ተራ ቁጥራቸውን በመጠቀም በሥርዓታዊ ናሙና አንድ አምስተኛ (1/5) የሚሆኑ በአጠቃላይ 190 ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በመነጋገር ተመርጠዋል።

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በቂና አስተማማኝ መረጃ ይገኝ ዘንድ ሁለት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ባገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። እነሱም ምልከታ (በመከታተያ ቅፅና በቪዲዮ ቀረፃ) እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው።

3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

የአቀራረብ ሁኔታን በተጨባጭ ለመረዳትና በቂ የሆነ ግንዛቤ ለማግኘት የክፍል ውስጥ ምልከታ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው Brandt (1981) ያብራራሉ። እንደ Richards and Rodgers (1995) አገላለጽ ከሆነ በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት የክፍል ውስጥ ምልከታ የመምህሩን ብቃትና አቀራረቡን በጥሩ ሁኔታ ማሳየት እንደሚችል ያስረዳሉ። የጥናቱ ዋና ዓላማ የመምህራንን የቃላት ትምህርት አቀራረብ መፈተሽ ሲሆን ይህንን ዓላማ በአግባቡ ለማሳካት ይቻል ዘንድ በዋናነት ለመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጠው ዘዴ

የክፍል ውስጥ ምልከታ ነው። ምልከታው የሚካሄደው በተደራጀ ቅፅ (Check list) አማካይነት ነው። ይህ ቅፅ መሠረት ያደረገው መምህሩ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርባቸው የሚጠበቅበትን ተግባራት ነው። የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅፅም አስተማማኝነቱን ይጠብቅ ዘንድ በጥናቱ አማካሪ ከታየና ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዓመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ከተበተነ በኋላ ተሰብስቦ እንዲስተካከል ተደርጓል።

ምልከታ ከመካሄዱ በፊት አጥኚውና ተጠኚው ተገናኝተው ምልከታ የሚካሄድበትን የጊዜ ሰሌዳ በስምምነት አመቻችተዋል። መረጃ የሚሰበስበውም ሁለት የአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ረዳቶች እና አጥኚው ክፍል ውስጥ በመገኘት ነው። የክፍል ምልከታውም በእያንዳንዱ ተጠኚ መምህር ሦስት ሦስት ጊዜ ተካሂዷል።

ሌላው ከመከታተያ ቅፁ በተጨማሪ የቪዲዮ ቀረፃ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ነው። የቪድዩ ቀረጻው መሠረታዊ ዓላማ ክንውኖችን ደጋግሞ ማሳየትና በምልከታው የሚሰበሰበውን መረጃ ለማጠናከርና አስተማማኝ ለማድረግ ነው። በመጀመሪያው ቀን በክፍል ውስጥ የፍተሻ ወይም የማስመሰያ ቀረፃ ተደርጓል። ይህም አስፈላጊ የሚሆነው በቀረፃው ወቅት ተማሪዎች ሙሉ ትኩረታቸውን በቀረፃው ላይ ስለሚያደርጉ ትክክለኛ ውን የቀረፃ ጊዜ እንዳያውቁት ለማድረግ ነው። ከዚያም በኋላ በጥናቱ በተካተቱ መምህራን ላይ በቀጣዩ ቀን ትክክለኛው ቀረፃ ተካሂዷል።

3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ

በምልከታው እና በቪዲዮ ቀረፃው የተሰበሰቡትን መረጃዎች የበለጠ ለማጠናከር እና በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ሊሰበሰቡ የማይችሉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ የፅሑፍ መጠይቅ አስፈላጊ ነው። ለዚህም ሁለት ዓይነት የፅሑፍ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል። መጠይቆቹ መሠረት የሚያደርጉት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን እና የእነዚህ ይዘቶች የክፍል ውስጥ አቀራረብን ነው። እነዚህ መጠይቆች የተዘጋጁት የክፍል ደረጃውን ለሚያስተምሩት መምህራንና ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ነው። የእነዚህን መጠይቆች አስተማማኝነት ለመጠበቅ እንዲያስችል በመጀመሪያ በጥናቱ አማካሪ ከታዩና ማስተካከያ ከተደረገባቸው በኋላ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ፅሑፍ የሁለተኛ ዓመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች አስተያየት

እንዲሰጥባቸው ተደርጓል። ከዚያም የሙከራ ጥናት (Pilot Study) ተካሂዶ ከሙከራ ጥናቱ በተገኘው ምጋቤ ምላሽ መሠረት ማሻሻያ ተደርጎበታል።

የመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ መምህራን ምላሽ እንዲሰጡበት የተዘጋጀ ሲሆን መጠይቁ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ክፍል ስለ መምህራኑ አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የመማር ማስተማር ሁኔታን የሚመለከቱ በድግግሞሽ ደረጃ 5 በጣም ከፍተኛ፣ 4 ከፍተኛ፣ 3 መካከለኛ ፣ 2 ዝቅተኛ እና 1 በጣም ዝቅተኛ በሚሉ መስፈርቶች ምላሽ የሚያገኙ ጥያቄዎች ናቸው። በሁለተኛው ክፍል ሌሎች ሶስት ክፍት ጥያቄዎችም የመጠይቁ አካል ናቸው።

የተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ እንደ መምህራኑ ሁሉ ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጥባቸው ተብለው ተዘጋጅተዋል። ክፍል አንድ ስለተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የሚገኝበት ነው። ሁለተኛው ክፍልም የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በድግግሞሽ ደረጃ እና በክፍት ቦታዎች መልስ የሚሰጥባቸው ናቸው።

እነዚህ ሁለት የፅሑፍ መጠይቆች አጥኚው በተገኘበት ተሞልተዋል። አጥኚው ስለመጠይቁ ዓላማና አሞላል ገለፃ ተደርጓል። በመጨረሻም ከየትምህርት ቤቱ የተሰበሰበውን መጠይቅ በመቁጠር ሁሉም ተሞልቶ መመለሱ ተረጋግጧል።

3.3 የመረጃዎች አተናተን

መረጃዎች ከግንቦት 4 ቀን 1999 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰብስበዋል። እነዚህ በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ፣ በመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ እና በተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተንና ለማብራራት ስታትስቲካዊ ስልት ሥራ ላይ ውሏል። ከመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙት መረጃዎች በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ በመመደብ ትንተና ከተደረገባቸው በኋላ ተብራርተዋል።

በመጀመሪያ በሶስት ምልከታ አድራጊዎች የተሰበሰበው መረጃ ወደ አንድ የምልከታ ቅፅ ተጠቃሎ እንዲመዘገብ ተደርጓል። ከዚያም በአንድ ቅፅ የተጠቃለለውን መረጃ በቪዲዮ ቀረፃ በተገኘው መረጃ እንዲረጋገጥ ለማድረግ ተሞክሯል። ከእያንዳንዱ መምህር በሶስት ክፍለ ጊዜያት የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደገና አሁንም ወደ አንድ የምልከታ ቅፅ እንዲጠቃለሉ ተደርጎ የእያንዳንዱ መምህር የአቀራረብ ሁኔታ በእያንዳንዱ የምልከታ

መስፈርት በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በማለት ደረጃ ተሰጥቶታል። ከዚያም ከሁሉም መምህራን የተገኙትን መረጃዎች በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ በመመደብ እና ታሊ (Tally) በማድረግ በሰንጠረዥ ውስጥ በቁጥር ለማስቀመጥ ተሞክሯል። እነዚህ በሰንጠረዦች የሰፈሩት መረጃዎችም ተተንትነዋል።

በመምህራን የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ ስለአቀራረባቸው ሁኔታ በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በማለት የሰጧቸውን ምላሾች በሚያነሷቸው ርዕስ ጉዳዮች በመመደብ እና ድግግሞሾቹንም በአሃዝ በሰንጠረዦች ውስጥ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። ሌላው በተማሪዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ናቸው። ከተማሪዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተቆጠሩ በኋላ በአቀራረብ ደረጃዎች ማለትም በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በማለት የሰጧቸው ምላሾችን ድግግሞሽ በየማቅረቢያ ደረጃው በሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች በመመደብ በቁጥር እና በመቶች በሰንጠረዥ ውስጥ ለማስፈር ተሞክሯል። ከዚያም በየሰንጠረዦቹ የሰፈሩትን መረጃዎች ለመተንተን ተሞክሯል።

በመጨረሻም በምልከታው እንዲሁም ከመምህራን እና ከተማሪዎች በዕሑፍ መጠይቆች የተሰበሰቡት መረጃዎች ትንተና ከተካሄደባቸው በኋላ በርዕሰ ጉዳይ የሚዛመዱትን ወደ አንድ በማምጣት ጥልቅ እና ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። እንዲሁም በክፍት ጥያቄዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደአስፈላጊነቱ ለማብራሪያው በማጠናከሪያነት ለማካተት ተሞክሯል።

A2 D

ምዕራፍ አራት

የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ፣ ከመምህራንና እና ከተማሪዎች በፅሑፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች በሰንጠረዥ አማካኝነት የሚቀርቡበት ነው። ለምርምሩ መነሻ የሆኑትን ጥያቄዎች ከመመለስ አንፃር የመተንተንና የማብራራት ተግባርም ተከናውኖበታል።

4.1 የመረጃዎች ውጤት ትንተና

መረጃዎች በክፍል ምልከታው፣ ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰቡ እና በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ከተደራጁ በኋላ በሰንጠረዥ፣ በአሃዝና በመቶኛ ሰፍረው በውጤቶች ላይ ትንተና ተሰጥቶባቸው። መረጃዎች የሚያነሱትን ርዕሰ ጉዳይ መሠረት በማድረግ በ4 ርዕሶች ሥር ተፈርጀው በሰንጠረዥ ከሰፈሩ በኋላ ትንተና ተደርጎባቸዋል። ርዕሶቹም፡-

1. በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች፣
2. የቃላት ትምህርትን በአግባቡ እንዳይቀርብ የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች፣
3. የቃላት ትምህርት ከማቅረቢያ ስልቶች አንፃር፣
4. ተማሪዎች ቃላትን እንዲያስታውሱ ከማድረግ አንፃር የሚሉት ናቸው።

4.1.1 በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች

የቃላት ትምህርት ይዘቶች የሚባሉት የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት፣ የሚቧድኑ ቃላት፣ የቃላት ትርጉም (አማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ፣ ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍቺ፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች) እና የቃላት ግንባታ ናቸው። እነዚህ ይዘቶች የቃላትን ትምህርት ከማስተማር አንፃር በይዘትነት መካተት ያለባቸው እንደሆኑ ከሊቃውንት አገላለፅ መገንዘብ እንችላለን። እነዚህ ይዘቶች በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች መቅረባቸውን ለማረጋገጥ በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ፣ ለመምህራን እና ለተማሪዎች በተበተነ መጠይቅ መረጃው ተሰብስቧል።

ሠንጠረዥ 1:- የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት ትምህርት ይዘትን በተመለከተ በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ።

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት	3	2		1	

በክፍል ምልከታው (ከመከታተያ ቅፁ እና ከቪዲዮ ቀረፃው) በተገኘው መረጃ መሠረት የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት የሚለው ይዘት በ3 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ በ2 መምህራን በከፍተኛ እና በ1 መምህር ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2:- የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅንና ንበትን ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ።

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
2	የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት አስተምራለሁ	2	3	1	1	

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት አስተምራለሁ የሚለውን ይዘት 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 3 መምህራን ከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ ደረጃ እንደሚያቀርቡት ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 3:- የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅንና ንበትን ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ።

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
3	የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት እንማራለን	36	18.95	99	51.10	38	20	17	8.95		

የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት የሚለውን ይዘት በክፍል ውስጥ የአቀራረቡን ሁኔታ ተማሪዎች ተጠይቀው 36(18.95%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 99(52.10%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 38(20%) ተማሪዎች መካከለኛ፣ 17(8.95%) ተማሪዎች ዝቅተኛ ነው በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

A4

የቃላትን ሰዋስዋዊ ቅርፅ እና ንበት በተመለከተ በምልከታ፣ በመምህራንእና በተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት መምህራን አዘወትረው እንደሚያቀርቡት ለመገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም በምልከታው 5 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ ሲያቀርቡት በተደጋጋፊነት ከፅሑፍ መጠይቆችም የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው 6 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እና ከተማሪዎች 70.5% ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀርብ በምላሻቸው አረጋግጠዋል። የቃላትን ቅርፅ እና ንበት ተማሪዎች ቢማሩ የቃላትን ሁለገብ ትርጉም ለመገንዘብ ስለሚያስችላቸው አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም።

ሠንጠረዥ 4:– የቃላት ትርጉም ትምህርት ይዘት አቀራረብን በተመለከተ በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ።

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላት ትርጉም	1	2	1	1	1

የቃላት ትርጉምን 1 መምህር በጣም ከፍተኛ፣ 2 መምህራን ከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ ደረጃ ሲያቀርቡት፣ 1 መምህር በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ አቅርበውታል።

ሠንጠረዥ 5:– የቃላት ትርጉምን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
3	የቃላትን ትርጉም አስተምራለሁ	4		2		

የቃላትን ትርጉም አስተምራለሁ የሚለውን የቃላት ትምህርት ይዘትን 4 መምህራን በጣም ከፍተኛ እና 2 መምህራን ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ እንደሚያቀርቡት በሰጡት ምላሽ አረጋግጠዋል።

ሠንጠረዥ 6:– የቃላት ትርጉምን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
5	የቃላትን ትርጉም እንማራለን	152	80	19	10	9	4.74	4	2.10	6	3.16

የቃላትን ትርጉም እንማራለን ተብሎ የተገለፀው ይዘት 152(80%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 9(4.74%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 4(2.10%) ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 6(3.16%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ እንደሚቀርብ ተናግረዋል።

የቃላትን ትርጉም ከማሰተማር አንፃር መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአቀራረቡ ሁኔታ ከፍተኛ ነው። በምልከታው እንደታየው አቀራረቡ በከፍተኛ ደረጃ በ4 መምህራን የታየ ሲሆን በፅሑፍ መጠይቆች መሠረትም አራት መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እናቀርበዋለን ማለታቸው እና በተማሪዎችም አቀራረቡ ከፍተኛ እንደሆነ 90% ከሚሆኑት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል። ለተማሪዎች የቃላት ትርጉምን አዘወትሮ ማቅረብ አስፈላጊ እና ትክክለኛ አካሄድ ነው። ምክንያቱም የቃላት ትርጉም እውቀት ችግር መሠረታዊ የቋንቋ ትምህርት ችግር ነውና። የቃላት ትርጉም ሲባል የቃላት ፍካራዊ እና እማራዊትርጉም፣ የቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ትርጉም እና የቃላት ፈሊጣዊ ትርጉምን አጠቃሎ የያዘ ፅንሰ ሐሳብ ነው። እናም ተማሪዎች እነዚህን ሁሉ መማር ማለት በቋንቋ የመግባባት ችግራቸውን በከፍተኛ ደረጃ ቀነሱ ማለት ነው። መምህራን ለዚህ ይዘት ትኩረት መስጠታቸውም የይዘቱን አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ አስገብተው ሳይሆን አይቀርም።

ሠንጠረዥ 7:– የቃላት ግንባታን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ።

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላት ግንባታ (ቅጥያ፣ ጥመራ)	2	1	3		

የቃላት ግንባታ ይዘትን 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 1 መምህር በከፍተኛ እና 3 መምህራን በመካከለኛ ሁኔታ ማቀረባቸውን በምልከታው ወቅት ታይቷል።

ሠንጠረዥ 8:– የቃላት ግንባታን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
3	የቃላት ግንባታ አስተምራለሁ	3	2	1		

የቃላት ግንባታን አስተምራለሁ የተባለውን ይዘት 3 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 2 መምህራን ከፍተኛ እና 1 መምህር መካከለኛ በሆነ መልኩ እንደሚያቀርቡት ከመምህራኑ ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል።

ሠንጠረዥ 9:– የቃላት ግንባታን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
4	የቃላትን ግንባታ እንማራለን።	36	18.95	99	51.10	38	20	17	8.95		

በተራ ቁጥር 4 የሰፈረው የቃላትን ግንባታ እንማራለን ይዘት 36(18.95%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 99(51.10%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 38(20%) ተማሪዎች በመካከለኛ እና 17(9.95%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚቀርብ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

መምህራን የቃላት ግንባታን ከማስተማር አንፃር ሲገመገሙ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይቀመጣሉ። በምልከታ በተገኘው መረጃ መሠረት ሶስት መምህራን በከፍተኛ ደረጃ አቅርበውታል። በፅሑፍ መጠይቆችም 5 መምህራን ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ማቅረባቸውን ሲናገሩ 70.5% የሚሆኑ ተማሪዎችም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀርብላቸው ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ መምህራን ይህን ይዘት ማቅረብ የሚገባቸውን ያክል ማቅረብ እንደቻሉ ለመገንዘብ ይቻላል። የዚህ ይዘት በበቂ ሁኔታ መቅረብ ደግሞ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ከማዳበር አንፃር ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ነው።

በክፍል ውስጥ መቅረብ የሚገባቸው የቃላት ትምህርት ይዘቶች ማለትም የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት፣ የቃላት ትርጉም እና የቃላት ግንባታ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀርቡ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ የእነዚህ ይዘቶች

ለተማሪዎች መቅረብ የቃላት ትምህርት አሰጣጥን የተሟላ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

ከመረጃዎች ለመረዳት እንደሚቻለው ሁሉም የቃላት ትምህርት ይዘቶች የአቀራረባቸው ድግግሞሽ ይለያይ እንጂ በመምህራን እንደሚቀርቡ ለማረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን የእነዚህን ይዘቶች አቀራረብ ስንመለከት እንደየመምህራኑ ትኩረት የአቀራረባቸው ሁኔታ ከይዘት ይዘት ሊለያይ ችሏል። ይህም ማለት አንዳንድ መምህራን አንድን የቃላት ትምህርት ይዘት ትኩረት በመስጠት ሲያቀርቡ አንዳንድ መምህራን ደግሞ ለአንዳንድ ይዘቶች ትኩረታቸውን ይነፍጓቸዋል።

4.1.2. የቃላት ትምህርትን በአግባቡ እንዳይቀርብ የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች

መምህራን የቃላትን ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚያቀርቡበት ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ተለዋዋጮች አሉ። እነዚህ ተለዋዋጮች ተለይተው አስፈላጊው ትኩረት ካልተሰጣቸው የመማር ማስተማር ሂደቱን በከፍተኛ ደረጃ ያደናቅፋሉ ማለት ነው። ተፅዕኖ የሚያደርጉትም አመለካከት ችግር፣ የመምህራን የስልጠና ሁኔታ፣ የተማሪው ቁጥር መብዛት፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች ችግር እና የክፍል ጊዜ ጫና ናቸው።

ሀ. ከአመለካከት ችግር አንፃር

ሠንጠረዥ 10፦ ስለቃላት ትምህርት አቀራረብ ያላቸውን አስተያየት መምህራን ምላሽ የሰጡበት ሰንጠረዥ።

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
1	የቃላት ትምህርትን በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ።	3	2	1		

መምህራን ስለ ቃላት ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በተጠየቁት ጥያቄ የይዘቱን የክፍል ውስጥ አቀራረብ 3 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 2መምህራን ከፍተኛ እና 1 መምህር መካከለኛ እንደሆነ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

A6

ሠንጠረዥ 11:– ስለቃላት ትምህርት የአቀራረብ ሁኔታ የተማሪዎች ምላሽ።

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
1	የቃላት ትምህርትን መምህራን ያቀርቡልናል	115	60.53	56	29.47	10	5.26	9	4.74		

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የቃላት ትምህርትን የመምህራን የአቀራረብ ደረጃ 115(60.53%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 56(29.47%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 10(5.26%) ተማሪዎች መካከለኛ እና 9(4.74%) ተማሪዎች ዝቅተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

ከሁለቱም መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት በመምህራን እንደታመነበት ነው። ከቋንቋ ትምህርት አብይና ንዑስ ክሂሎች መካከል አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸውን ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ተጠይቀው የቃላት ትምህርትን በ5ኛ ደረጃ አስቀምጠውታል። ነገር ግን መምህራን በዚህ ደረጃ ያስቀምጡት እንጂ በዝግ ጥያቄዎች 5 መምህራን እና 80% ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የቃላት ትምህርት እንደሚቀርብ የሰጡት መልስ የትምህርት ዘርፉ ትኩረት እንደተሰጠው ማረጋገጫ ነው። መምህራን እና ተማሪዎች የቃላት ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ካመኑ የመማር ማስተማር ሂደቱን የተቃና እና የተቀላጠፈ ሊያደርገው እንደሚችል መረዳት ይቻላል። ስለዚህ ይህ ተለዋዋጭ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደማያሳድር መረዳት ይቻላል።

በሌላ መልኩ ደግሞ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማወቅ ስለቃላት ትምህርት ያላቸውን አስተያየት እንዲያሰፍሩ ተጠይቀው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ካሰፈሯቸው መካከል 1ኛ. የአማርኛ ቃላትን ስለማናውቅ መምህራን በደንብ እንዲያስተምሩን፣ 2ኛ. ቃላትን ስለማናውቅ ብዙ ክፍለ ጊዜ ብንማር ጥሩ ነው። 3ኛ. መምህራን ድርሰት ዓፃሲሉን በቃላት እጥረት እንቸገራለን የሚሉት ይጠቀሳሉ። ስለዚህ የቃላት ትምህርት በጣም እንደሚያስፈልጋቸው እና በአግባቡ እንዲቀርብላቸው እንደሚፈልጉ መረዳት ይቻላል።

ለ. ከማስተማሪያ ግብዓቶች አንፃር

ሠንጠረዥ 12:- ለቃላት ትምህርት የመማሪያ መፅሐፍን ከመጠቀም አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
21	ለቃላት ትምህርት የመማሪያ መፅሐፍን እጠቀማለሁ።	3	1	2		

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው ለቃላት ትምህርት የመማሪያ መፅሐፍን እጠቀማለሁ ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 3 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 1 መምህር ከፍተኛ እና 2 መምህራን ደግሞ በመካከለኛ ሁኔታ የመማሪያ መፅሐፍን እንደሚጠቀሙበት ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 13:- የመማሪያ መጽሐፍን ከመጠቀም አንፃር ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ።

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
21	የቃላት ትምህርት ከመማሪያ መፅሐፋችን እንማራለን	125	65.79	17	8.95	37	19.47	11	5.79		

የቃላት ትምህርት ከማቅረቢያ ግብዓቶች አንፃር የቃላት ትምህርት ከመማሪያ መፅሐፋችን እንማራለን ተብሎ የተጠቀሰውን መምህራን መጠቀማቸውን ሲጠየቁ 125 (65.79%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 17(8.95%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 37(19.47%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 11(5.79%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ በትምህርቱ ማቅረቢያነት እንደሚጠቀሙበት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍ መምህራን አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ከመምህራን አራቱ በከፍተኛ ደረጃ እና ከተማሪዎች 74.74% የሚሆኑት በከፍተኛ ደረጃ በማለት ምላሽ ከሰጡት መረዳት ይቻላል። በእርግጥም ይህን መፅሐፍ መጠቀማቸው የመማር ማስተማሩን ሂደት የተቃና ያደርገዋል። ይህም ሲባል መለማመጃ ጥያቄዎችን ከማቅረብ አንፃር፣ የክፍል እና የቤት ሥራ ከማሰራት አንፃር፣ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲለማመዱ ከማድረግ አንፃር ድርሻው የላቀ ነው።

ሠንጠረዥ 14፡- ለቃላት ትምህርት የግል ማቴሪያል ከመጠቀም አንፃር መምህራን የሰጡት ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
21	ለቃላት ትምህርት የግል ማቴሪያል አዘጋጅቼ አስተምራለሁ			6		

ለቃላት ትምህርት የግል ማቴሪያል አዘጋጅቼ አስተምራለሁ ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 6 መምህራን ማለትም የተጠየቁት ሁሉም የግል ማቴሪያል አዘጋጅቶ የማስተማርን ሁኔታ በመካከለኛ ደረጃ አስቀምጠውታል፡፡

ሠንጠረዥ 15:– የግል ማቴሪያልን አዘጋጅቶ ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች ምላሽ፡፡

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
22	መምህራችን የግል ማቴሪያል በማዘጋጀት ቃላትን ያስተምረናል	14	7.37	15	7.88	97	51.04	22	11.57	52	27.37

በተራ ቁጥር 22 መምህሩ የግል ማስተማሪያ ማቴሪያል በማዘጋጀት ትምህርቱን ያቀርቡ እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡ በዚህም መሠረት 14(7.37%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 15(7.88%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 97(51.04%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 22(11.57%) ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 52(27.37%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ መምህራን ለቃላት ትምህርት ማቅረቢያነት እንደሚጠቀሙበት መልሰዋል፡፡

ለቃላት ትምህርት መምህራን የግል ማቴሪያል አዘጋጅቶ ማቅረብን በተመለከተ 6 መምህራን እና 97(51.04%) ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ለቃላት ትምህርት የግል ማቴሪያል አዘጋጅቶ ማስተማርን በተመለከተ ከመምህራንም ሆነ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ የሚያሳየው መምህራን የሚፈለገውን ያክል አዘውትረው እንደማያዘጋጁ እና እንደማይጠቀሙ ነው፡፡ ይህንን የማስተማሪያ ግብአት አዘወትረው የማያዘጋጁት ሁልጊዜ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል ብለው ስለሚያምኑ ሊሆን ይችላል፡፡

የማስተማሪያ ግብዓቶች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ይህም ማለት የመማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ከማስተማር አንፃር አመቺነቱ ተመዝኖ ከተረጋገጠ በኋላ አገልግሎት ላይ ከዋለ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት አመቺ ካልሆነ መምህራን የራሳቸውን የማስተማሪያ ማቴሪያል አዘጋጅተው ትምህርቱን ቢያቀርቡ ተመራጭ ይሆናል።

ሐ. የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ

ሠንጠረዥ 16:– አጠቃላይ የመምህራንን ዳራ ለማወቅ ለቀረቡ ጥያቄዎች የመምህራን ምላሽ

የአገልግሎት ዘመን በዓመት			የትምህርት ደረጃ		የስልጠና ሁኔታ				የክፍለ ጊዜ ብዛት በሳምንት	
1-5	6-10	ከ10 በላይ	ዲግሪ	ዲፕሎማ	ዓብይ		ንዑስ		ከ18-25	ከ25 በላይ
					አማርኛ	ሌላ	አማርኛ	ሌላ		
4	-	2	4	2	6	-	-	6	3	3

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የመምህራን ያገልግሎት ዘመናቸውን ተጠይቀው ሲመልሱ 4 መምህራን ከ1-5 ዓመት፣ 2 መምህራን ከ10 ዓመት በላይ እንደሆነ ተናግረዋል። የትምህርት ደረጃቸው 4 መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ እና 2መምህራን ዲፕሎማ ያላቸው ናቸው። የሰለጠኑበትን የትምህርት መስክ ሲገልፁ 6 መምህራን የአማርኛ ቋንቋን በዓብይነት ሲያጠኑ በንዑስ የትምህርት ዓይነት ያጠኗቸው ደግሞ ሌሎች ቋንቋዎችን ነው። የክፍለ ጊዜ ብዛት በሳምንት 3 መምህራን ከ18-25፣ 3 መምህራን ደግሞ ከ25 በላይ እንዳላቸው ከሰንጠረዡ መረዳት ይቻላል።

የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ በቃላት መማር ማስተማር ክንውኑ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። ተፅዕኖው በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ መልኩ ሊሆን ይችላል። ከዚህ መረጃ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው የመማር ማስተማር ሂደቱን ከማቀላጠፍ አንፃር ከፍተኛውን ሚና እንደሚጫወት ነው።

የአገልገሎት ዘመን ለመማር ማስተማሩ በአንድ በኩል ለረጅም ጊዜ ሲያስተምሩ የቆዩ መምህራን ልምድ ከማካበት አንፃር ጠቀሜታ ቢኖረውም በየጊዜው ለሚለዋወጠው የቋንቋ ማስተማሪያ ሥነ ዘዴ ባዕድ ሊሆኑ ስለሚችሉ በቅርብ ጊዜ ከተቋም የወጡ

ተማሪዎች የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ እነዚህ በቅርቡ ከተቋም የመጡ መምህራን ከተቋሙ ከወጡ ረጅም ጊዜን ባለማስቆጠራቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አያሳድሩም ተብሎ ይገመታል።

የትምህርት ደረጃን በተመለከተ ለ9ኛ ክፍል የሚመደቡ መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲኖራቸው ይጠበቃል። ከዚህ አንፃር በርካታ ቁጥር ያላቸው መምህራን ይህንኑ ሊያሟሉ ጥቂቶቹም ቢሆኑ ከዲፕሎማ የትምህርት ማሻሻል በማድረግ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ለመያዝ እጅግ በጣም የተወሰኑ ኮርሶች ብቻ እንደቀራቸው ከሰጡት ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም የትምህርት ደረጃ በአሉታዊ ተፅዕኖ የሚያዝ አይደለም።

የስልጠና ሁኔታን በሚመለከት ሁሉም መምህራን የአማርኛ ቋንቋን በአብይ የሰልጠና ሁኔታ የተማሩት መሆኑ ለመማር ማስተማሩ ክንውን ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን የቃላት ትምህርት አቀራረብን የሚመለከት አጫጭር ስልጠና አለመውሰዳቸውን መምህራን ተናግረዋል። ይህን አጫጭር ስልጠና አለማግኘት በየጊዜው ለሚለዋወጠው የቋንቋ የማስተማር ሳይንስ ባዕድ ሊያደርጋቸው ይችላል። ከዚህ አንፃር አዳዲስ የይዘት ማቅረቢያ ስልቶችን አለማወቅና አለመጠቀም በትምህርቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

በሳምንት የመምህራን የክፍለ ጊዜ ብዛት ከፍተኛ እንደሆነ ከመረጃው መረዳት ይቻላል። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመምህራን የክፍለ ጊዜ ብዛት እስከ ሰላሳ ሊደርስ እንደሚችል ቢታወቅም የእነዚህ መምህራን የክፍለ ጊዜ ብዛትም ቢሆን ዝቅተኛ ሊባል አይችልም። ምክንያቱም መምህራን በተለይም የቋንቋ መምህራን የራሳቸውን ፈጠራ ተጠቅመው ትምህርቱን ያቀርቡ ዘንድ በቂ ጊዜ ስለሚያስፈልጋቸው በሳምንት ከ15 ክፍለ ጊዜያት የበለጠ ባይዙ ይመረጣል። በቃላት ትምህርት አቀራረብ ወቅት አደናቃፊ ሁኔታዎች ካሉ እንዲጠቅሱ መምህራን ሲጠየቁ ከዘረዘሯቸው አደናቃፊ ሁኔታዎች መካከል የክፍለ ጊዜ ጫና አንዱ መሆኑ ይህንን እውነታ ያረጋግጣል። ስለዚህ እነዚህ መምህራን ከፍተኛ የክፍለ ጊዜ ጫና ስላለባቸው የግል ማቴሪያል ለማዘጋጀትና የመርጃ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል።

መ. የተማሪ ቁጥር

ሠንጠረዥ 17:– የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ቁጥር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ጥያቄ	የመማሪያ ክፍሎች		
	7	4	7
በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪ ቁጥር	55-60	61-65	66-70

ምልከታ በተካሄደባቸው 18 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ከ55-70 በ7 መማሪያ ክፍሎች፣ ከ61-65 በ4 የመማሪያ ክፍሎች እና ከ66-70 በ7 የመማሪያ ክፍሎች መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር እስከ 30 ከሆነ ጥሩ የመማር ማስተማር ክንውን ማካሄድ ይቻላል። ነገር ግን ጥናት በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ቁጥር በጣም ከፍተኛ የሚባል ነው። ይህ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ተመራጭ የማስተማሪያ ስልቶችን ለመጠቀም ያላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ለዚህም ነው መምህራን የቃላት ትምህርት ይዘትን በአግባቡ እንዳያቀርቡ ከሚያደርጉ አደናቃፊ ሁኔታዎች መካከል የተማሪ ቁጥር መብዛትን አንዱ አድርገው የገለፁት።

ሠንጠረዥ 18:– የቃለት ትምህርት በአግባቡ እንዳይቀርብ ለሚያደርጉ ሁኔታዎች መምህራን የሰጡት ምላሽ።

ተ.ቁ	ጥያቄ	በመምህራን በተደጋጋሚ የተጣቀሱ ችግሮች			
		የተማሪ ቁጥር መብዛት	የትምህርት መርጃ ለማዘጋጀት የሚቴሪያል እጥረት	ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክ/ጊዜ ማነስ	ለቃላት ትምህርት የመፅሐፉ አመቺ አለመሆን
1	የቃላትን ትምህርት በአግባቡ እንዳያቀርቡ የሚያደርጉ አደናቃፊ ሁኔታዎች አሉ? ካሉ በዝርዝር ይጠቀሱ	2	2	5	2

የቃላትን ትምህርት በአግባቡ እንዳያቀርቡ የሚያደርጉ አደናቃፊ ሁኔታዎች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን እንዲናገሩ እና ካሉ በዝርዝር እንዲጠቅሱ ተጠይቀው መምህራን ምላሽ ሰጥተዋል። የተማሪው ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት የሚለው በ2 መምህራን፣ የማቴሪያል እጥረት በ2 መምህራን፣ ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ማነስ የሚለው በ5 መምህራን እና የመማሪያ መፅሐፉ ለቃላት

ትምህርት ማቅረቢያነት አመቺ አለመሆን በ2 መምህራን አደናቃፊ ተብለው የተዘረዘሩ ችግሮች ናቸው።

በመምህራን በችግርነት የተጠቀሰው የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ቀደም ሲል የተተነተነውን መረጃ የሚያጠናክር ሆኖ ነው የተገኘው። ምክንያቱም መምህራን ይዘቱን በአግባቡ ከማቅረብ አንፃር እንደሚቸገሩባቸው ከጠቀሷቸው መካከል አንዱ ነውና። ይህ ችግር ቀደም ብሎ አንደተገለፀው መምህራን ለተማሪዎች ትምህርቱን ለማስጨበጥ የተሻለውን የማቅረቢያ ስልት ለመጠቀም ላያስችላቸው ይችላል። በእርግጥ ይህንን ችግር የቡድን ማስተማር ስልትን በመጠቀም መቀነስ የሚቻል ቢሆንም በተለይ እያንዳንዱን ተማሪ እያደረገ እንዲማሩ ከማድረግ አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖው ከፍተኛ ሊሆን ይችላል።

በመምህራን እንደችግር የተጠቀሰው ሌላው ደግሞ የማቴሪያል እጥረት ነው። ለተማሪዎች የመርጃ መሣሪያ በመጠቀም ትምህርቱን ለማስጨበጥ ይቻል ዘንድ ለመርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጃ የሚሆኑ ማቴሪያሎች ሊሟሉ ይገባል። ምክንያቱም የመርጃ መሣሪያዎች ትምህርቱን በቀላሉ ለማስተላለፍ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነውና። ይሁን እንጅ መምህራኑ ለትምህርት መርጃ መሣሪያነት የሚያገለግሉ ማቴሪያሎችን እጥረት መጥቀሳቸው ምንአልባትም ትምህርቱን በተሻለ መልክ ለማቅረብ እንዳይችሉ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮባቸው ይሆናል።

የአንድን ትምህርት ይዘት ለተማሪዎች በአገባቡ ለማስገንዘብ ይቻል ዘንድ በቂ ጊዜ ያስፈልጋል። ይሁን እንጅ በመምህራን በተደጋጋሚ እንደትልቅ ችግር የተነሳው የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሳምንት ሁለት ብቻ መሆኑን ነው። ስለዚህ የክፍለ ጊዜው ማነስ ለቃላት ትምህርት ተሸንሽኖ የሚደርሰው ክፍለ ጊዜ በጣም አናሳ ስለሚሆን በአግባቡ እና በተደጋጋሚ የዚህን ትምህርት ይዘት ለማስተላለፍ አስቸጋሪ ይሆናል።
የመማሪያ መፅሐፉ ለቃላት ትምህርት አመቺ አለመሆን እንደችግር በመምህራን ከተጠቀሱት መካከል አንዱ ነው። የመማሪያ መፅሐፍ መልመጃዎችን ከማቅረብ አንፃር፣ ተማሪዎችን በራሳቸው እንዲለማመዱ ከማድረግ አንፃር፣ የመምህሩን ጊዜ ከመቆጠብ አንፃር ሚናው የጎላ ነው። ይሁን እንጅ መምህራን የመማሪያ መፅሐፉ የቃላት ትምህርትን ከማቅረብ አንፃር አመቺ አለመሆኑን በችግርነት ጠቅሰዋል። ምንአልባትም

መፅሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘትን እንደሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ርዕስ ሰጥቶ አለማስፈሩን እንደ ችግር ቆጥረውት ይሆናል እንጂ በሌሎች ክሂሎች ሥር ተካቶ በመፅሐፉ መቅረቡን በአስተያየታቸው ሲገልፁ ትኩረት እንዳልተነፈገው መረዳት ይቻላል።

በቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተለዋዋጮች አመለካከት፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች፣ የመምህራን ዳራ፣ የተማሪዎች ቁጥር፣ የመማሪያ መፅሐፍ እና የተመደበው ክፍለ ጊዜ ናቸው። የእነዚህ ተለዋዋጮች ተፅዕኖ በአሉታዊ እና በአዎንታዊ መልኩ የሚታይ ነው። በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩት የመምህራንና የተማሪዎች አመለካከት፣ የመማሪያ መፅሐፍ መጠቀም፣ የአገልግሎት ዘመን፣ የትምህርት ደረጃ እና የስልጠና ሁኔታ (በአብይ) ናቸው። እነዚህ ተለዋዋጮች የመማር ማስተማር ሂደትን ከማቀላጠፍ አንፃር በአዎንታዊ መልኩ የሚፈረጁ ሆነው ተገኝተዋል።

መምህራን ለቃላት ትምህርት ያላቸው አመለካከት፣ የመምህራን በትምህርት ዘርፉ የተለየ የማሻሻያ ስልጠና አለማግኘት፣ የመምህራን የክፍለ ጊዜ ጫና፣ የተማሪው ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት፣ ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ማነስ በመማር ማስተማር ሂደቱ ወቅት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተለዋዋጮች ናቸው። ለዚህም ከመረጃ መሰብሰቢያዎች የተገኘው ውጤት ማረጋገጫ ነው።

4.1.3 የቃላት ትምህርት ከማቅረቢያ ስልቶች አንፃር

የቃላት ትምህርትን ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ በርካታ የማቅረቢያ ስልቶች አሉ። እነዚህ ስልቶችም ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር በሚከተለው መልኩ ተፈርጀዋል።

ሀ. ቃላትን ከፍች አንፃር ማቧደን፣

ለ. ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብ፣

ሐ. ከቃላት ሰዋስው አንፃር፣

መ. ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት፣

ሠ. ቃሉን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣

ረ. ቃላትን በመርጃ መሳሪያዎች አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር፣

ሰ. ለቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ከመስጠት አንፃር፣

ሀ. ቃላትን ከፍች አንፃር ማቧደን

ሠንጠረዥ 19:– የቃላትን ፍቺ በተመሳሳይና በተቃራኒ ቃላት ከማቅረብ አንፃር በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ።

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን በመጠቀም ማቅረብ	2		3	1	

በምልከታው የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን በመጠቀም ማቅረብ 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 3 መምህራን በመካከለኛ እና 1 መምህር በዝቅተኛ ደረጃ አቅርቦበታል።

ሠንጠረዥ 20፡- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ተጠቅሞ ማቅረብን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
11	ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን በማቅረብ ትርጉምን አለማምዳለሁ	4	1		1	

በተመሣሣይና ተቃራኒ ቃላትን በመጠቀም ማቅረብ ተብሎ የተገለፀውን የማቅረቢያ ስልት 4 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 1 መምህር በከፍተኛ እና 1 መምህር በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚያቀርቡበት ከሰንጠረዡ ለመረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 21:– በተመሳሳይና በተቃራኒ ቃላት ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ።

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
11	በተመሳሳይ እና በተቃራኒ ቃላት ትርጉምን እንለማመዳለን	124	65.26	26	13.68	22	11.58	18	9.47		

ከተማሪዎች በተሰጠው ምላሽ መሠረት በተመሣሣይና በተቃራኒ ቃላት ትርጉምን እንለማመዳለን ተብሎ የቀረበውን 124(65.26%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣

26(13.68%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 22(11.58%) ተማሪዎች በመካከለኛ እና 18(9.48%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ መምህራን የማቅረቢያ ስልቱን እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል።

ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን በመጠቀም የማቅረብ ስልትን ከምልከታው የተገኘው መረጃ መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ያሳያል። 5 መምህራን ከፍተኛ እና 78.94% ተማሪዎች ምላሽም በተደጋጋፊነት ከፍተኛ በሆነ ደረጀ መምህራን እንደሚጠቀሙበት ያስረዳል። በዚህ ስልት ተጠቅሞ የቃላትን ትርጉም ማስተማር የቃላትን የተለያዩ ትርጉሞችን ማለትም በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ከመገንዘብ ወይም ከመጠቀም አንፃር ለተማሪዎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስለሚያደርግ መምህራን አዘውትረው መጠቀማቸው ተገቢና አስፈላጊ ነው።

ሠንጠረዥ 22:– **አብረው የሚሄዱ ቃላትን ከመጠቀም አንፃር በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ።**

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
አብረው የሚሄዱ ቃላትን በማዛመድ ማቅረብ	1	1	1	4	

አብረው የሚሄዱ ቃላትን በማዛመድ የማቅረቢያ ስልትን 1 መምህር በጣም ከፍተኛ፣ 1 መምህር በከፍተኛ እና 1 መምህር በመካከለኛ ደረጃ እና 4 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ሲጠቀሙበት ታይተዋል።

ሠንጠረዥ 23:– **አብረው የሚሄዱ ቃላትን ከመጠቀም አንፃር የመምህራን ምላሽ**

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
12	አብረው የሚሄዱ ቃላትን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት እጠቀማለሁ	1	1	1	3	

አብረው የሚሄዱ ቃላትን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት እጠቀማለሁ ተብሎ የተጠቀሰውን ደግሞ 1 መምህር በጣም ከፍተኛ 1 መምህር በከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ እና 3 መምህራን በዝቅተኛ ሁኔታ እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል።

ሠንጠረዥ 24:– አብረው የሚሄዱ ቃላትን ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
12	አብረው የሚሄዱ ቃላትን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት መምህሩ ይጠቀማል	33	17.37	17	8.95	31	16.34	100	52.63	9	4.74

አብረው የሚሄዱ ቃላትን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት መምህሩ ይጠቀማል ተብሎ የተጠቀሰውን ደግሞ 33(17.37%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 17(8.95%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 31(16.34%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 100(52.63%) ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 9(4.74%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ መምህራን እንደሚጠቀሙበት አስገንዝበዋል።

አብረው የሚሄዱ ቃላትን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት ከመጠቀም አንፃር በምልከታው 4 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ አቅርበውበታል። ከመምህራን ምላሽ 3 መምህራን እና 57.47% ተማሪዎች ዝቅተኛ እንደሆነ መልሰዋል። ከምልከታውም ሆነ ከመምህራን እና ከተማሪዎች ምላሽ በተገኘው መረጃ መሠረት መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት እንገነዘባለን። ይህ ስልት የቃላትን የአብሮነት ባህሪ ስለሚያሰገነዝብ ተማሪዎች የትኛው ቃል ከየትኛው ቃል ጋር አብሮ እንደሚሄድ ከተረዱ ሲናገሩም ሆነ ሲፅፉ የሚያጋጥማቸውን ችግር ከማቃለል አንፃር ድርሻው ከፍተኛ ይሁን እንጂ በመምህራን ትኩረት እንደተነፈገው እንረዳለን።

ለ. ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብ

ሠንጠረዥ 25:– ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብን በተመለከተ በቪድዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላትን ትርጉም አውድ ፈጥሮ ማቅረብ		1	1	3	1

ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው የቃላትን ትርጉም አውድ ፈጥሮ ማቅረብን በተመለከተ 1 መምህር በከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ፣ 3 መምህራን በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሲጠቀሙበት ተስተውለዋል።

ሠንጠረዥ 26:– ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
10	አውድ ፈጥሬ ቃላትን በማቅረብ ትርጉምን አለማምዳለሁ	1	2	1	2	

አውድ ፈጥሬ ቃላትን በማቅረብ ትርጉምን አለማምዳለሁ ለሚለው የመምህራን ምላሽ አንድ መምህር በጣም ከፍተኛ፣ ሁለት መምህራን በከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ እና 2 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ ገልፀዋል።

ሠንጠረዥ 27:– ቃላትን ከአውድ አንፃር ማቅረብን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
10	ለቃላት ትርጉም አውድ ፈጥሮ ያስተምረናል።	19	10	57	30	19	10	90	47.37	5	2.63

መምህሩ በቃላት ትርጉም አውድ ፈጥረው ያስተምሩ እንደሆነ ተጠይቀው 19(10%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 57(30%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 90(47.37%) ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 5(2.63%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚያቀርቡበት ገልፀዋል።

ለቃላት ትርጉም አውድ ፈጥሮ ማስተማር ስልትን 3 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት በምላሻቸው ቢገልፁም ከምልከታው የ4 መምህራን አቀራረብ እና በ50% ተማሪዎች ምላሽ ያቀራረብ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

ከምልከታው እና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት የቃላትን ትርጉም አውድ ፈጥሮ ከማስተማር አንፃር መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ለመገንዘብ ይቻላል። ቃላትን አውድ ፈጥሮ ማስተማር ተማሪዎች የተማሩትን ቃል በመዋቅር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ሲገባ ያለውን ትርጉም እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል። መምህራን ይህንን ስልት ላለመጠቀማቸው ምክንያቱም የቃላት ትምህርትን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ አጫጭር ስልጠናዎችን አለመውሰድ ሊሆን ይችላል።

ሠንጠረዥ 28:– በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቀረብ		1	2	1	2

ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው የቃላትን ትርጉም ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብን አንድ መምህር በከፍተኛ፣ 2 መምህር በመካከለኛ፣ አንድ መምህር በዝቅተኛ እና 2 መምህራን በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ተጠቅመውበታል።

ሠንጠረዥ 29:– ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
11	የቃላትን ትምህርት ምንባብ በማዘጋጀት አቀርባለሁ።		1	1	2	1

መምህራን በሰጡት ምላሽ መሠረት የቃላትን ትምህርት ምንባብ በማዘጋጀት አቀርባለሁ የሚለውን 1 መምህር በከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ፣ 2 መምህራን በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚያቀርቡበት ገልፀዋል።

ሠንጠረዥ 30:– የቃላትን ትምህርት ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
11	የቃላትን ትምህርት ምንባብ በማዘጋጀት መምህሩ ያቀርብልናል።			9	4.74	19	10	152	80	10	5.26

የቃላት ትምህርት ምንባብ በማዘጋጀት መምህሩ ሊያቀርብላቸው እንደሆነ ተጠይቀው 9(4.74%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች መካከለኛ፣ 152(80%) ተማሪዎች ዝቅተኛ እና (5.26%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማሰተማር ቃሉ በሌሎች ቃላት ተፅዕኖ ምክንያት ያለውን ትርጉም እና ቃሉ በቁሙ ያለውን ትርጉም በንፅፅር ማሳየት ያስችላል። ነገር ግን በምልከታው እንደታየው የ3 መምህራን አጠቃቀም ዝቅተኛ ሲሆን እንዲሁም ከፅሑፍ መጠይቆችም በተደጋጋፊነት በተገኘው መረጃ መሠረት 3 መምህራን እና 85.26% ተማሪዎች የመምህራንን የአጠቃቀም ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን በምላሻቸው አረጋግጠዋል።

ሐ. የቃላትን ሰዋሰው ከመጠቀም አንፃር

ሠንጠረዥ 31:- የቃላት ሰዋስው መጠቀምን በተመለከተ በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላትን ሰዋስዋዊ ቅርፅ እና ንበት በማሳየት			4	1	1

የቃላትን ሰዋስዋዊ ቅርፅ እና ንበት በማሳየት በኩል 4 መምህራን በመካከለኛ፣ 1 መምህር በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙ በምልከታው ወቅት ተስተውሏል።

ሠንጠረዥ 32:- የቃላት ሰዋስው መጠቀምን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
2	የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት አስተምራለሁ	2	3	1		

በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰውን የቃላትን ሰዋስዋዊ ቅርፅና ንበት አስተምራለሁ የሚለውን የማቅረቢያ ስልት 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 3 መምህራን በከፍተኛ እና 1 መምህር በመካከለኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 33:– የቃላት ሰዋስው መጠቀምን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
3	የቃላትን ሰዋስዋዊ ቅርፅና ንበት እንማራለን	36	18.95	99	51.11	38	20	17	8.95		

በተራ ቁጥር 3 የቃላትን ሰዋስዋዊ ቅርፅና ንበት እንማራለን ተብሎ የተጠቀሰውን የማቅረቢያ ስልት 36(18.55%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 99(52.11%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 38(20%) ተማሪዎች በመካከለኛ እና 17(8.95%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚያቀርቡበት ከሠንጠረዡ ለመረዳት ይቻላል።

የሰዋስዋዊ ቅርፅን እና ንበትን (ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ) በማሳየት የማቅረብ ስልትን በምልከታው መሠረት 4 መምህራን በመካከለኛ ደረጃ ሲጠቀሙበት ታይቷል። በፅሑፍ መጠይቆችም 5 መምህራን በከፍተኛ እና 70.06% ተማሪዎች መምህራን በከፍተኛ ደረጃ ለማቅረቢያነት እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል። መምህራን በተደጋጋሚ እንደሚጠቀሙበት ከምልከታው፣ ከመምህራ እና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል። የቃላትን ትርጉም ማስተማር በተለይ የአማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩት ተማሪዎች ዘንድ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ምክንያቱም አንድን ቃል ሲጠብቅ እና ሲላላ ያለውን ትርጉም ከተገነዘቡ የተነገረን የማዳመጥ እና የተፃፈን የማንበብ ችግር ላይገጥማቸው ይችላል።

ሠንጠረዥ 34:– የቃላት ግንባታን መጠቀምን በተመለከተ በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላትን ግንባታ በማሳየት ማቅረብ		4	2		

የቃላትን ግንባታ አመሰራረት በማሳየት ማቅረብን 4 መምህራን በከፍተኛ እና 2 መምህራን በመካከለኛ ደረጃ ተጠቅመውበታል።

ሠንጠረዥ 35:- **የቃላትን ግንባታ ከመጠቀም አንፃር የመምህራን ምላሽ**

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
4	የቃላትን ግንባታ አስተምራለሁ	3	2	1		

በተራ ቁጥር 4 የቀረበውን የቃላትን ግንባታ አስተምራለሁ የሚለውን የማቅረቢያ ስልት ደግሞ 3 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 2 መምህራን በከፍተኛ እና 1 መምህር በመካከለኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል።

ሠንጠረዥ 36:- **የቃላትን ግንባታ ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች ምላሽ**

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
2	የቃላትን ግንባታ እንማራለን	30	15.57	98	51.58	54	28.42	8	4.21		

የቃላትን ግንባታ እንማራለን የሚለውን 30(15.79%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 98(51.58%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 54(28.42%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 8(4.21%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ መምህራን እንደሚያቀርቡበት የተማሪዎች ምላሽ ያስገነዝባል።

የቃላት ግንባታ (የቃላትን እርባታና ምስረታ) በተመለከተ መምህራን የቃላት ትምህርትን ከማቅረቢያ ስልቶች መካከል በከፍተኛ ደረጃ በጥቅም ላይ እንደሚያውሉት ከምልከታ 4 መምህራን፣ ከፅሑፍ መጠይቁ 5 መምህራን እና 67.15% ተማሪዎች በተገኘው መረጃ ከፍተኛ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። ይህ ስልት ተማሪዎች የቃላትን የተለያዩ መዋቅሮችን፣ የአዳዲስ ቃላት አመሠራረትን እና ባህሪያትን እንዲገነዘቡ ከማድረግ አንፃር አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። ስለሆነም በመምህራን ትኩረት ተሰጥቶት መታየቱ የቃላት ትምህርትን በአግባቡ ከማስተላለፍ አኳያ የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካ ሊያደርገው ይችላል።

መ. ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብ

ሠንጠረዥ 37:- በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ስለማቅረብ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ቃላትን በሌሎች የቋንቋ ክሂሎት አካቶ ማቅረብ		5			1

ቃላትን በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አካቶ ማቅረብን በተመለከተ በምልከታው በተገኘው መረጃ መሠረት 5 መምህራን በከፍተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሲያቀርቡበት ተስተውለዋል::

ሠንጠረዥ 38:- ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብን በተመለከተ ከመምህራን ምላሽ የተገኘ መረጃ:::

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
14	የቃላትን ትምህርት በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አካትቼ አቀርባለሁ::	2	3	1		

የቃላትን ትምህርት በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አካቶ ማቅረብን በተመለከተ መምህራን ተጠይቀው ሲመልሱ 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 3 መምህራን በከፍተኛ እና 1 መምህር በመካከለኛ ደረጃ ተግባራዊ እንደሚያደርጉት መልስ ሰጥተዋል::

ሠንጠረዥ 39:- ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
15	የቃላት ትምህርት በሌሎች ክሂሎች (በንባብ፣ በፅሕፈት፣ በመናገር፣ በማዳመጥ እና በሰዋሰው) ተካቶ ይቀርብልናል::	19	10	152	80	10	5.26	9	4.74		

የቃላት ትምህርትን በሌሎች ክሂሎች አካቶ መቅረብን በተመለከተ 19(10%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 152(80%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 10(5.26%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 9(4.74%) ተማሪዎች ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ መምህሩ እንደሚጠቀምበት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

የቃላት ትምህርት በሌሎች ክሂሎች ማለትም በንባብ፣ በፅህፈት፣ በመናገር፣ በማዳመጥ እና በሰዋስው አካቶ ማቅረብ ተማሪዎች የቃላትን ሁለንተናዊ እውቀት ከማስጨበጥ አንፃር ተመራጩ የማስተማሪያ ስልት ነው። በመሆኑም ይህንን የማቅረቢያ ስልት ከምልከታ፣ ከመምህራን እና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት መምህራን በከፍተኛ ደረጃ አዘወትረው እንደሚጠቀሙበት መገንዘብ ተችሏል።

ሠ. ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

ሠንጠረዥ 40:- ቃሉን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን በተመለከተ በቪዲዮ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርር	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ		1		1	4

ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን በተመለከተ 1 መምህር በከፍተኛ፣ 1 መምህር በዝቅተኛ እና 4 መምህራን በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሲጠቀሙበት በምልከታው ወቅት ታይተዋል።

ሠንጠረዥ 41:- ቃሉን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን በተመለከተ መምህራን የሰጡት ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
	ቃላትን ተማሪዎች ከመዝገበ ቃላት እንዲማሩ አደርጋለሁ		1	2	2	1

ቃላትን ተማሪዎች ከመዝገበ ቃላት እንዲማሩ ከማድረግ አንፃር 1 መምህር በከፍተኛ፣ 2 መምህራን በመካከለኛ፣ 2 መምህራን በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 42:- ቃለትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
16	ቃላትን ከመዝገበ ቃላት እንማራለን			5	2.63	19	10	76	40	90	47.37

የሰንጠረዡ መረጃ የሚያስገነዝበው 5(2.63%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 76(40%) ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 90(47.37%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ ቃላትን ከመዝገበ ቃላት እንደሚማሩ ነው።

የቃላትን ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። የመጀመሪያው ተማሪው በራሱ የቃላትን ትምህርት ይማር ዘንድ ያግዘዋል። ሌላው ደግሞ የቃላት ትርጉም፣ አመሰራረት እና አገባብ ለማስተማር መዝገብ ቃላትን መጠቀም የተሻለ አማራጭ ነው። ይሁን እንጅ ይህ የማቅረቢያ ስልት አስፈላጊ እና ተመራጭ ሆኖ ሳለ ከምልከታ 5 መምህራን በዝቅተኛ፣ ከፅሁፍ መጠይቁ ሶስት መምህራን በዝቅተኛና 87.37% ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እንደሚውል ተገልጿል። በተገኘው መረጃ መሠረትም መምህራን ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ታይቷል። ምናልባትም መምህራን ይህንን ስልት ያለመጠቀማቸው ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት በትምህርትቤታቸው ወይም በተማሪዎች እጅ በበቂ ሁኔታ አለመገኘት ሊሆን ይችላል። ለመምህራን በቀረበ ክፍት ጥያቄ ለቃላት ትምህርት በአደናቃፊነት ከተዘረዘሩት መካከል ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ማነስ፣ የተማሪው ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት እና ለትምህርት መርጃ መሣሪያነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች አለመኖር የሚጠቀሱ ናቸው። ስለዚህ በትምህርት ቤታቸው ለትምህርት መምርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጃነት የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች እጥረት መኖሩን መጠቆማቸው ይህንን ሃሳብ ሊያጠናክረው ይችላል።

፭. የቃላት ትምህርትን በመርጃ መሣሪያዎች አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር

ሠንጠረዥ 43:- ከቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ መምህራን የተለያዩ መግለጫዎችን ከመጠቀም አንፃር የተገኘው መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ቃላትን የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም ማቅረብ			1	2	3

ቃላትን የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም ማቅረብን በሚመለከት በምልከታው የተገኘው 1 መምህር በመካከለኛ፣ 2 መምህራን በዝቅተኛ እና 3 መምህራን በጣም ዝቅተኛ በሆነ መለኩ እንዳቀረቡበት ያስገነዝበናል።

ሠንጠረዥ 44:- ቃላትን የተለያዩ መግለጫዎችን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
8	ቃላትን ለማስተማር የተለያዩ መግለጫዎችን (ስዕሎችን እና ቁሶችን) እጠቀማለሁ።		1	2	3	

በተራ ቁጥር 8 የተጠቀሰውን ቃላትን ለማስተማር የተለያዩ መግለጫዎችን እጠቀማለሁ የሚለውን 1 መምህር በከፍተኛ፣ 2 መምህር በመካከለኛ እና 3 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ምላሻቸውን ስጥተዋል።

ሠንጠረዥ 45:- ቃላትን የተለያዩ መግለጫዎችን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
13	ልዩ ልዩ መግለጫዎችን (ስዕሎቱን እና ቁሶችን) በመጠቀም የቃላትን ትርጉም ያቀርብልናል።			9	4.74	57	30	105	55.26	19	10

ልዩ ልዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የቃላትን ትርጉም መምህሩ ያቀርብላቸው ከሆነ ተጠይቀው ዘጠኝ (4.74%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 57(30%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 105(55.26%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ እና 19(10%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

የቃላትን ትርጉም ለማስተማር ስዕሎችን እና ቁሶችን መጠቀም ትምህርቱን የበለጠ ተጨባጭ የማድረጉን ጉዳይ ማንም አሌ ሊለው አይችልም። ይሁን እንጅ መምህራን ይህንን ስልት ካለው ጠቀሜታ አንፃር በሚፈለገው መልኩ ሊጠቀሙበት እንዳልቻሉ በምልከታው 5 መምህራን ዝቅተኛና በመጠይቆቹም ከ3 መምህራን እና 65.26% ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ዝቅተኛ መሆኑን ያረጋግጣል። መምህራን ይህንን ስልት አዘወትረው ላለመጠቀማቸው ለመርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጃ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እጥረትን በምክንያትነት ያስቀምጣሉ።

ሠንጠረዥ 46:- ቃላትን አካላዊ ምላሽን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
አካላዊ ምላሽ ዘዴን በመጠቀም ቃላትን ማስተማር			1	4	1

አካላዊ ምላሽ ዘዴን በመጠቀም ቃላትን የማስተማር ስልትን 1 መምህር በመካከለኛ፣ 4 መምህራን በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት በምልከታው ታይቷል።

ሠንጠረዥ 47:- ቃላትን አካላዊ ምላሽን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
9	የሰውነት እንቅስቃሴን በመጠቀም ቃላትን አስተምራለሁ	2	1	2		1

የሰውነት እንቅስቃሴን በመጠቀም ቃላትን አስተምራለሁ ተብሎ የተገለፀውን ስልት ደግሞ 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 1 መምህር በከፍተኛ፣ 2 መምህራን በመካከለኛ

እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ከምላሻቸው መገንዘብ ተችሏል።

ሠንጠረዥ 48፡– ቃላትን አካላዊ ምላሽን ተጠቅሞ ከማስተማር አንፃር የተማዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
9	የሰውነት እንቅስቃሴን በመጠቀም የቃላትን ፍቺ መምህሩ ያስተምረናል።	24	12.63	30	15.79	114	60	19	10	3	1.58

የሰውነት እንቅስቃሴን በመጠቀም የቃላትን ፍቺ መምህራን ያቀርብላቸው እንደሆነ በቀረበው ጥያቄ 24(12.63%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 30(15.79%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 114(60%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 3(1.58%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚያቀርቡላቸው በምላሻቸው አረጋግጠዋል።

የሰውነት እንቅስቃሴን (አካላዊ ምላሽን) በመጠቀም የቃላት ትምህርት ማቅረብን በተመለከተ ይህ ስልት በተለይም የአማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደአስፈላጊነቱ መጠቀሙ አስፈላጊ ነው። በምልከታው የተገኘው መረጃ የሚያስረዳው የ5 መምህራን አጠቃቀም በዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ ሲታይ ከመጠይቁቹ የተገኘው ደግሞ 3 መምህራን ከፍተኛ ነው ሲሉ 60% ተማሪዎች ደግሞ የመምህራን የአቀራረብ ድግግሞሽ በመካከለኛ ደረጃ መሆኑን ያስረዳሉ። ከሁሉም የመረጃ ምንጮች መገንዘብ የምንችለው ነገር ቢኖር ይህ የማቅረቢያ ስልት በመካከለኛ ደረጃ በመምህራን ዘንድ ሥራ ላይ መዋሉን ነው። መምህራን ይህንን የማቅረቢያ ስልት በከፍተኛ ደረጃ ላለመጠቀማቸው ምክንያቱ በዚህ የክፍል ደረጃ የመጠቀሙን አስፈላጊነት ዝቅ አድርጎ ከማየት የመነጨ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

ሰ. ለቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ከመስጠት አንፃር

ሠንጠረዥ 49:- የቃላትን ትርጉም በሌሎች ቃላት ብያኔ ከመስጠት አንፃር በቪዲዮ ቀረፃ በተደገፈ ምልከታ የተገኘ መረጃ።

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላትን ትርጉም ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ በሌሎች ቃላት ብያኔ በመስጠት ማቅረብ		1	5		

ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ብያኔ በመስጠት የቃላት ትርጉምን ማቅረብን በተመለከተ 1 መምህር በከፍተኛ እና 5 መምህራን በመካከለኛ ደረጃ ሲያቀርቡት ታይተዋል።

ሠንጠረዥ 50:- የቃላትን ትርጉም በሌላ ቃል ብያኔ ከመስጠት አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
5	ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ብያኔ በመስጠት የቃላት ትርጉም አቀርባለሁ	2	1	2	1	

በተራ ቁጥር 5 ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ብያኔ በመስጠት የቃላትን ትርጉም አቀርባለሁ ተብሎ የተጠቀሰውን 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 1 መምህር በከፍተኛ፣ 2 መምህራ በመካከለኛ እና 1 መምህር በዝቅተኛ ደረጃ ተጠቅመውበታል።

ሠንጠረዥ 51:- የቃላትን ትርጉም በሌላ ቃል ብያኔ ከመስጠት አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
6	የቃላት ትርጉም ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ብያኔ በመስጠት ይቀርብልናል።	31	16.32	112	58.95	37	19.47	7	368	3	1.58

ከተማሪዎች በተገኘው ምላሽ መሠረት የቃላት ትርጉምን ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ብያኔ በመስጠት ይቀርብልናል የሚለውን 31(16.32%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 112(58.95%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 37(19.47%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 7(3.68%)፣ ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 3(1.58%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚቀርብ ገልፀዋል።

የቃላትን ትርጉም ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ በሌሎች ቃላት ብያኔ በመስጠት ማቅረብን በተመለከተ ከምልከታው በተገኘው መረጃ መሠረት 5 መምህራን በመካከለኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ለመገንዘብ ተችሏል። በፅሁፍ መጠይቆች መሠረትም 3 በከፍተኛ እና 75.22% የሚሆኑ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ይቀርባል ብለዋል። ከመረጃዎቹ መገንዘብ የሚቻለውም ይህንን ስልት በተፈለገው ደረጃ እየተጠቀሙበት እንደሆነ ነው።

ሠንጠረዥ 52:– ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ ከመስጠት አንፃር በምልከታ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት ማቅረብ		1	1	4	

ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት ማቅረብን በተመለተ 1 መምህር በከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ እና 4 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተጠቅመውበታል።

ሠንጠረዥ 53:– ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ ከመስጠት አንፃር ከመምህራን የተሰጠ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
6	ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት ቃላትን አስተምራለሁ		1	2	3	

በተራ ቁጥር ላይ ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት ቃላትን አስተምራለሁ ተብሎ የቀረበውን የማቅረቢያ ስልት 1 መምህር በከፍተኛ 2 መምህራን በመካከለኛ እና 3 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ አቅርበውታል።

ሠንጠረዥ 54:- ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ ከመስጠት አንፃር ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
7	ጥልቅ ማብራራያ በመስጠት የቃላት ትርጉምን ያስተምራል	24	12.63	19	10	42	22.11	105	55.26		

በተራ ቁጥር 7 የሰፈረውን ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት የቃላት ትርጉምን ያስተምረናል የሚለውን ስልት 24(12.63%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች በከፍተ፣ 42(22.11%) ተማሪዎች በመካከለኛ እና 105(55.26%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ ምላሻቸውን ሰጥተዋል::

ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት የቃላትን ትርጉም ማስተማር በዚህ የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች ተመራጭ ስልት ነው:: ምክንያቱም ስለ ቃሉ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማድረግ አንፃር አስተዋፅኦው ከፍተኛ ነውና:: ይሁን እንጅ ከመረጃዎቹ መገንዘብ እንደሚቻለው ከአስፈላጊነቱ አንፃር የመምህራን አጠቃቀም በቂ አይደለም:: ምክንያቱም በምልከታው የአቀራረቡ ሁኔታ በ4 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ነው የታየው:: በተጨማሪም በፅሑፍ መጠይቆች 3 መምህራን እና 55.26% በሚሆኑት ተማሪዎች በዝቅተኛ ድግግሞሽ እንደሚቀርብ ምላሽ ሰጥተዋል::

ሠንጠረዥ 55:- ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን ከመጠቀም አንፃር ከምልከታው የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎች በመጠቀም ማቅረብ		1	2	3	

ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን በመጠቀም ማቅረብን በሚመለከት 1 መምህር በከፍተኛ፣ 2 መምህራን በመካከለኛና፣ 3 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ አቅርበውበታል::

ሠንጠረዥ 56:- ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን ከመጠቀም አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
7	ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት አቀርባለሁ	1	3		2	

ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት አቀርባለሁ የማለውን 1 መምህር በጣም ከፍተኛ፣ 3 መምህራን ከፍተኛ፣ 2 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል።

ሠንጠረዥ 57:- ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
8	ለዋናው ቃል ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት ያቀርብልናል	9	4.74	20	10.53	19	10	134	70.53	8	4.21

ተራ ቁጥር 8 በዋናው ቃል ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት ያቀርብልናል በማለት በማቅረቢያነት የተገለፀው ስልት 9(4.74%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 20(10.53%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች መካከለኛ፣ 134(70.53%) ተማሪዎች ዝቅተኛ፣ 8(4.21%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ የአቀራረብ ደረጃ አለው ብለዋል።

ለዋናው ቃል ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት ማቅረብን በተመለከተ 4 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩት ምላሽ ሰጥተዋል። ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ ከፅሑፍ መጠይቁ 74.74% ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 3 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገበር ከምላሻቸው ለመገንዘብ ተችሏል። በመረጃዎቹ መሠረት ይህ የማቅረቢያ ስልት በሚፈለገው መልኩ ተተግብሯል ለማለት አያስደፍርም። ይህ የማቅረቢያ ስልት

የአንድን ቃል ትርጉም በግልፅ ከማሰገንዘብ አንፃር ድርሻው የጎላ መሆኑን መምህራን ተገንዘበውታል ለማለት ያስችግራል።

ሠንጠረዥ 58፡- ቃሉን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመተርጎም አንፃር በምልከታው የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ቃሉ በአፍ መፍቻቸው ቋንቋ አቻ ቃል በመተርጎም ማቅረብ					6

ቃሉ በአፍ መፍቻቸው ቋንቋ አቻ ቃል በመተርጎም ማቅረብን ደግሞ 6 መምህራን ሁሉም በጥናቱ የተካተቱት በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ይህንን ስልት ተጠቅመውበታል።

ሠንጠረዥ 59፡- ቃሉን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመተርጎም አንፃር ከመምህራን የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
13	የቃላትን ፍቺ በአፍ መፍቻቸው በመተርጎም አቀርባለሁ።	1		1	3	

በተራ ቁጥር 13 የተገለፀውን የቃላትን ፍቺ በአፍ መፍቻቸው በመተርጎም አቀርባለሁ የሚለውን ደግሞ 1 መምህር በመካከለኛ፣ 3 መምህራን በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ማቅረባቸውን በምላሻቸው አስገንዝበዋል።

ሠንጠረዥ 60፡- ቃሉን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመተርጎም አንፃር ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
14	የቃላት ፍቺ በትግርኛ ቃላት ተተርጉሞ ይቀርብልናል			38	20	29	15.26	95	50	28	14.74

በተራ ቁጥር 14 የቀረበውን የቃላት ፍቺን በትግርኛ ቃላት ተተርጉሞ ይቀርብልናል የሚለውን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ 38(20%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 29(15.26%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 95(50%) ተማሪዎች በዝቅተኛ እና 28(14.74%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ መምህራን እንደሚጠቀሙበት በምላሻቸው አስገንዝበዋል።

የቃላትን ትርጉም የማቅረቢያ ስልት በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ አቻ ቃል መተርጎም ነው። ይህንን ስልት በምልከታው ወቀት በሁሉም መምህራን ዘንድ ዝቅተኛ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። 4 መምህራንም ለተጠየቁት ጥያቄ በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩት ተናግረዋል። በተደጋጋፊነት 64.74% ያህሉ ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገበር ገልፀዋል። ከመረጃዎቹ እንደምንገነዘበው ይህ ስልት በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገበር ነው። ምናልባትም መምህራን በዚህ ስልት የማያቀርቡት በዚህ የክፍል ደረጃ አስፈላጊ መስሎ ስላልታያቸው ሊሆን ይችላል።

የቃላት ትምህርትን ከማቅረቢያ ስልቶች መካከል ቃላትን ከፍች አንፃር ማቧደን፣ ቃላትን በአውድ ማቅረብ፣ ከቃላት ሰዋስው አንፃር ማቅረብ፣ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብ፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣ በመርጃ መሣሪያዎች አስደግፎ ማቅረብ እና ለቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ከመስጠት አንፃር ማቅረብ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በእያንዳንዱ ርዕስ ስር የተጠቃለሉ ሌሎች የማቅረቢያ ስልቶችም በዚህ ክፍል ትኩረት የተሰጠባቸው ናቸው።

መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በተገኘው ውጤት መሠረት መምህራን በከፍተኛ ደረጃ የተጠቀሙባቸው የማቅረቢያ ስልቶች በተቃራኒና በተመሳሳይ ፍች፣ የሰዋሰዋዊ ቅርፀንና ንበትን፣ የቃላትን ግንባታ በመጠቀም፣ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት፣ በሌሎች ቃላት ብያኔ በመስጠት ማቅረብ የሚሉት ናቸው። በዝቅተኛ ደረጃ የተጠቀሙባቸው ደግሞ አብረው የሚዜዱ ቃላትን በመጠቀም፣ ምንባብ በማዘጋጀት፣ ሲጠብቁና ሲላሉ፣ በመዝገበ ቃላት በማስደገፍ፣ መግለጫዎችን በመጠቀም፣ አካላዊ ምላሽን በመጠቀም፣ ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት በአውድ አስደግፎ ማቅረብ፣ ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት ማቅረብ እና በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመተርጎም ማቅረብ የሚሉት ናቸው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን የተወሰኑ የማቅረቢያ ስልቶተን ብቻ እንደሚጠቀሙባቸው ነው።

4.1.4 ተማሪዎች ቃላት እንዲያስታውሱ ከማድረግ አንፃር

ሠንጠረዥ 61፡- በቃላትን ትምህርት ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ ከማድረግ አንፃር በምልከታ የተገኘው መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ተማሪዎች በቃላት ትርጉም ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ		1	3	1	1

ተማሪዎች በቃላት ትርጉም ትምህርት ወቅት ትርጉም ያለው (ተጨበጥ) ልምምድ በተመለከተ 1 መምህር በከፍተኛ፣ 3 መምህራን በመካከለኛ፣ 1 መምህር በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደተገበሩት በምልከታው ወቅት ታይቷል።

ሠንጠረዥ 62፡- በቃላትን ትምህርት ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ ከማድረግ አንፃር የመምህራን ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
17	ተግባራዊ ልምምድ በማድረግ የቃላትን ትርጉም አስተምራለሁ	2	2	2		

ተራ ቁጥር 17 ላይ ተግባራዊ ልምምድ በማድረግ የቃላትን ትርጉም አስተምራለሁ ተብሎ የሰፈረውን 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 2 መምህራን በከፍተኛ እና 2 መምህራን በመካከለኛ ደረጃ ተጠቅመዋል።

ሠንጠረዥ 63፡- በቃላትን ትምህርት ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ ከማድረግ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
17	ትርጉም ባለው ልምምድ የቃላትን ፍቺ እንማራለን።	18	9.14	36	18.95	40	21.05	96	50.53		

በተራ ቁጥር 17 ትርጉም ባለው ልምምድ የቃላትን ፍቺ እንማራለን ተብሎ የቀረበውን 18(9.14%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 36(18.95%) ተማሪዎች በከፍተኛ፣ 40(21.05%) ተማሪዎች በመካከለኛ፣ 96(50.53%) ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገበር ምላሽ ሰጥተዋል።

ተማሪዎች በቃላት ትርጉም ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ ሲባል እያንዳንዱን ተማሪ በተግባር እያሳየ እና እያደረገ እንዲማር በማድረግ ትምህርቱን ነባራዊ ማድረግን ይመለከታል። ይህንን አቀራረብ መጠቀም ተማሪዎች ትምህርቱን ከራሳቸው ህይወት ጋር በማዋሃድ እንዳይረሱት ያደርጋቸዋል። ይህን በተመለከተ በምልከታው በ4 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ መተግበሩ ሲታይ በፅሑፍ መጠይቁም 50.53% ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ መተግበሩን ገልፀዋል በተቃራኒው ደግሞ ደግሞ 5 መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩት በምላሻቸው ገልፀዋል። በመረጃዎቹ መሠረት መምህራን ማድረግ የሚገባቸውን ያክል ጥረት አላደረጉም። ምናልባት ለዚህ ምክንያቱ የተማሪዎች ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት ሳይሆን አይቀርም።

ሠንጠረዥ 64፡- ምስል ከሳች ቃላትን ከመጠቀም አንፃር በምልከታው የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም ማስተማር		1	3	1	1

ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም ማስተማርን 1 መምህር በከፍተኛ፣ 3 መምህራን በመካከለኛ፣ 1 መምህር በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ድግግሞሽ ተጠቅመዋል።

ሠንጠረዥ 65፡- ምስል ከሳች ቃላትን ከመጠቀም አንፃር ከመምህራን የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
18	ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም አስተምራለሁ	2	3	1		

በተራ ቁጥር 18 ላይ ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም አስተምራለሁ ተብሎ የተገለፀውን ደግሞ 2 መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 3 መምህራን በከፍተኛ እና 1 መምህር በመካከለኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 66፡- ምስል ከሳች ቃላትን ከመጠቀም አንፃር የተማሪዎች የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
18	ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም መምህሩ ያስተምረናል።	17	8.95	5.9	31.05	97	51.05	6	3.16	11	5.79

በተራ ቁጥር 18 ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም መምህሩ ያስተምረናል ተብሎ ለተገለፀው 17(8.95%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 59(31.05%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 97(51.05%) ተማሪዎች መካከለኛ፣ 6(3.11%) ተማሪዎች ዝቅተኛ እና 11(5.79%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ ገልፀዋል።

ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም ማቅረብ ትምህርቱ በተማሪዎች አእምሮ ውስጥ ተቀርፆ ስለሚቀር ትምህርቱን ነባራዊ ያደርገዋል። ይህንን ስልት በተመለከተ በምልከታው 3 መምህራን እና ከመጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት ከ51.05% ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ሲተገበር በ5 መምህራን ምላሽ መሠረት ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩት ተናግረዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ይህን ቃላትን ለማስታወስ የሚያግዝ የማቅረቢያ ስልት መምህራን በተገቢው መልኩ የተገበሩት ቢመስላቸውም በተግባር ግን አተገባበራቸው የሚፈለገውን ያክል ከፍተኛ አለመሆኑን ከሁለቱ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል።

ሠንጠረዥ 67፡- ለቃላት ትርጉም ተማሪዎች የራሳቸውን ብልሃት ከመጠቀም አንፃርበምልከታው የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
ተማሪዎች ለቃላት ትርጉም የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃቶችን መጠቀም			2	3	1

ተማሪዎች ለቃላት ትርጉም የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ማድረግ 2 መምህራን በመካከለኛ፣ 3 መምህራን በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ተግባራዊ አድርገውታል።

ሠንጠረዥ 68፡- ለቃላት ትርጉም ተማሪዎች የራሳቸውን ብልሃት ከመጠቀም አንፃር ከመምህራን የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
16	ቃላትን እንዳይረሱ የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃት እንዲጠቀሙ አደርጋለሁ።		2	1	3	

በተራ ቁጥር 16 የተገለፀውን ቃላትን እንዳይረሱ የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃት እንዲጠቀሙ አደርጋለሁ ተብሎ 2 መምህራን በከፍተኛ፣ 1 መምህር በመካከለኛ እና 3 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ማድረጋቸውን በምላሻቸው ገልፀዋል።

ሠንጠረዥ 69፡- ለቃላት ትርጉም ተማሪዎች የራሳቸውን ብልሃት ከመጠቀም አንፃር ከተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
19	ቃላትን እንዳንረሳ የራሳችንን የማስታወስ ስልት እንጠቀማለን	28	14.74	12.4	65.26			34	17.89	4	2.11

ቃላትን እንዳንረሳ የራሳችንን የማስታወስ ስልት እንጠቀማለን የሚለውን 28(14.74%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 124(65.26%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 34(17.89%) ተማሪዎች ዝቅተኛ እና 4(2.11%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

ተማሪዎች ለቃላት ትርጉም የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃቶችን መጠቀም እንዲችሉ መምህራን ከፍተኛውን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል። ይህ ስልት ተማሪዎችን

ከራሳቸው ልምድ አንፃር የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀም እንዲያስታውሱ በማድረግ ማለማመድ የትምህርቱን አይረሴነት ያጠናክረዋል። ይሁን እንጅ መምህራን ይህንን ስልት አዘውትረው ተግባራዊ እንደማያደርጉት በምልከታው 4 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩት ሲታይ ከፅሑፍ መጠይቆችም 3 መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩት ገልፀዋል። ይሁን እንጂ ከ80% ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚተገብሩት ነው። ስለዚህ ከመምህራን ምላሽና ከምልከታው በተገኘ መረጃ መሠረት ይህንን ስልት መምህራን በአግባቡ እንደማይተገብሩት ለመገንዘብ ተችሏል።

ሠንጠረዥ 70፡- የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ከማስተማር አንፃር በምልከታ የተገኘ መረጃ

የምልከታ መስፈርት	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
	5	4	3	2	1
የቃላትን ትርጉም በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገሙ ማስተማር			2	3	1

የቃላትን ትርጉም በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገሙ ማስተማርን ደግሞ 2 መምህራን በመካከለኛ፣ 3 መምህራን በዝቅተኛ እና 1 መምህር በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ በምልከታው ተረጋግጧል።

ሠንጠረዥ 71፡- የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ከማስተማር አንፃር ከመምህራን የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
19	የቃላትን ትርጉም እንዳይረሱ በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገምኩ አስተምራለሁ	1	3	1	1	19

በተራ ቁጥር 19 የቃላትን ትርጉም እንዳይረሱ በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገምኩ አስተምራለሁ ተብሎ የተጠቀሰውንም 1 መምህር በጣም ከፍተኛ 3 መምህራን ከፍተኛ፣ 1 መምህር መካከለኛ እና 1 መምህር ዝቅተኛ እንደሆነ በምላሻቸው አረጋግጠዋል።

ሠንጠረዥ 72:- የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ከማስተማር አንፃር ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መካከለኛ		ዝቅተኛ		በጣም ዝቅተኛ	
		5		4		3		2		1	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
20	የቃላትን ትርጉም እንዳንረሳ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ እንማራለን።	3	1.8	104	54.74	19	10	46	24.21	18	9.47

በተራ ቁጥር 20 የቃላትን ትርጉም እንዳንረሳ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ እንማራለን ተብሎ የሰፈረውን ደግሞ 3(1.58%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 104(54.74%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ 19(10%) ተማሪዎች መካከለኛ፣ 46(24.21%) ተማሪዎች ዝቅተኛ እና 18(9.47%) ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ ለመሆኑ ምላሽ ሰጥተዋል።

የቃላትን ትርጉም በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገሙ ማስተማር ተማሪዎች ትምህርቱን እንዳይረሱት ከማድረግ አንፃር ሚናው የላቀ ነው። 4 መምህራን እና ከ55.54 ተማሪዎች አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት በምላሻቸው ይግለፁ እንጅ በምልከታው የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ግን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚተገበር በ4 መምህራን ላይ ታይቷል። ከመጠይቆቹ በተገኘው መረጃ መሠረት የማቅረቢያ ስልቱን መምህራን በከፍተኛ ደረጃ የሚያቀርቡት ቢመስላቸውም በምልከታው አቀራረቡ በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

ተማሪዎች ቃላትን እንዲያስታውሱ ከማድረግ አንፃር ትርጉም ያለው ልምምድ ተማሪዎች እንዲያደርጉ ማድረግ፣ ምስል ከሳች ቃላትን መጠቀም፣ ተማሪዎች የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃት እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ማቅረብ የሚሉት ተጠቃሽ ስልቶች ናቸው። ከእነዚህ ስልቶች መካከል በዝቅተኛ ደረጃ የተተገበሩት ተማሪዎች ትርጉም ያለው ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ፣ ተማሪዎች የማስታወስ ብልሃት እንዲጠቀሙ ማድረግ እና የቃላትን ትርጉም ደጋግሞ ማስተማር የሚሉት ናቸው። በመካከለኛ ደረጃ የተተገበረው ደግሞ አንድ ስልት ብቻ ሲሆን ይህም ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም ማሰተማርን ነው። ስለዚህ መምህራን ቃላትን እንዲያስታውሱ ከማድረግ አንፃር የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሃሳቦች

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ውጤት ማጠቃለያ እና ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የመፍትሄ ሃሳብ የተሰጠባቸው በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በትግራይ ክልል በሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርትን እንዴት እንደሚያቀርቡ መፈተሽ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ጥናቱ ለመመለስ ይሿቸው የተነሳው መሪ ጥያቄዎች፡-

1. መምህራን የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ያቀርባሉ?
2. መምህራን የትምህርቱን ይዘት ለማቅረቢያነት የበለጠ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች የትኞቹ ናቸው?
3. መምህራን የቃላትን ትምህርት በአግባቡ እንዳያቀርቡ በሙሉም ሆነ በከፊል የሚያደናቅፍ ሁኔታዎች አሉ? የሚሉት ናቸው።

ጥናቱ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ መረጃዎችን ሰብስቧል። ለመረጃ ምንጭነትም በክልሉ የሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። የክፍል ውስጥ ምልከታ እና የፅሑፍ መጠይቆች ከየትምህርት ቤቶቹ መምህራን እና ተማሪዎች መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግለዋል። መረጃዎችን ለመተንተንም በገለፃ ላይ የተመሠረተ አቀራረብ ጥቅም ላይ ውሏል። ከዚያም የተገኘውን ውጤት እንደሚከተለው ለማጠቃለል ተሞክሯል።

መምህራን የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ከማቅረብ አንፃር ከተሰበሰቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት፣ የቃላትን ትርጉም እንዲሁም የቃላትን ግንባታ በክፍል ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ለተማሪዎች ያቀርቡላቸዋል።

የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ለማቅረብ የማቅረቢያ ስልቶችን ከመጠቀም አንፃር ሲታይ መምህራን የተወሰኑትን በከፍተኛ ደረጃ ሲጠቀሙባቸው ቀሪዎቹን ደግሞ በዝቅተኛ

ደረጃ እንደሚጠቀሙባቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። መምህራን በከፍተኛ ደረጃ የተገበሯቸው ሥልቶች ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን፣ የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበትን፣ የቃላትን ግንባታ በመጠቀም፣ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት እና ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ሌላ ቃል ብያኔ በመስጠት ማቅረብ የሚሏቸውን ስልቶች ነው። ነገር ግን መምህራን ሌሎች የማቅረቢያ ስልቶች ትኩረት አልሰጧቸውም። እነዚህ በመምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ሲሆኑ የታዩት የማቅረቢያ ስልቶች አብረው የሚሄዱ (የሚቧደኑ) ቃላትን በመጠቀም፣ የተለያዩ አውዶችን በመጠቀም፣ ምንባብ በማዘጋጀት፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣ የተለያዩ መግለጫዎችን (ቁሦችን፣ ስዕሎችን) በመጠቀም፣ አካላዊ ምላሽን በመጠቀም፣ ለቃሉ ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት፣ ለቃሉ ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት እና ለቃሉ በትግርኛ ቋንቋ አቻ ቃል በመተርጎም ማቅረብ የሚሉት ናቸው።

ሌላው ደግሞ ተማሪዎች ቃላትን እንዳይረሱ ከማድረግ አንፃር መምህራን ምስል ከሳች ቃላትን በመካከለኛ ደረጃ ሲጠቀሙ፣ ለቃለት ትርጉም ተማሪዎች ተግባራዊ ልምምድ እንዲያደርጉ ፣ ለተማሪዎች የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃት እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንፃር፣ ትምህርቱን በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገሙ ከማስተማር አንፃር ሲታይ ግን አጠቃቀማቸው በዝቅተኛ ደረጀ ላይ ይገኛል።

የመምህራን የክፍለ ጊዜ ጫና መኖር፣ ለመምህራን የቃላት ትምህርትን በተመለከተ ልዩ ስልጠና አለመሰጠት፣ በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ማነስ እና የማቴሪያል እጥረት መኖር የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች በአግባቡ እንዳይቀርብ የሚያደናቅፉ ተለዋዋጮች መሆናቸውን ከጥናቱ ውጤት ለመገንዘብ ተችሏል።

5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የመፍትሄ ሃሳቦችን መሰንዘር አስፈላጊ ነው። በዚህም መሠረት፣

1. አብረው የሚሄዱ (የሚቧደኑ) ቃላትን በመጠቀም፣ ቃለትን በተለያዩ አውዶች በማስገባት ማስተማርን፣ ለቃሉ ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት እና ለቃሉ ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት የቃላት ትምህርትን ከማቅረብ አንፃር የመምህራን አጠቃቀም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። እነዚህ የማቅረቢያ ስልቶች ለዚህ የክፍል ደረጃ አስፈላጊና ተገቢ መሆናቸውን የተለያዩ ምሁራን ገልፀዋል። ይሁን እንጂ

መምህራን እነዚህን ስልቶች በአግባቡ እንዳይጠቀሙ ምክንያቱ የቃላት ትምህርትን በሚመለከት አጫጭር ስልጠናዎችን አለማግኘት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የሚመለከተው አካል ለመምህራን የቃላት ትምህርትን በሚመለከት በየጊዜው አጫጭር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን እንዲወስዱ ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ መልካም ነው።

2. መምህራን የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አሰደግፎ ከማቅረብ አንፃር በዝቅተኛ ደረጀ ተጠቅመውበታል። ይህ ስልት የቃላትን የተለያዩ ዘርፎችን ለተማሪዎች ከማስጨበጥ አንፃር ከፍተኛ ሚና አለው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች ከመዝገበ ቃላት የቃላትን ትምህርት እንዲማሩ በማድረግ መምህራን ላለማቅረባቸው ምክንያቱ የመዝገበ ቃላት እጥረት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላትን በበቂ ሁኔታ በመግዛት በቤተ መፅሐፍቱ እንዲቀመጡ ቢያደርጉ ጥሩ ነው።

3. የመርጃ መሣሪያዎችን በተለይ ስዕሎችን እና ቁሦችን ተጠቅሞ ቃላትን ማስተማር ትምህርቱን የበለጠ ነባራዊ ያደርገዋል። ይሁን እንጅ የመምህራን አጠቃቀም በዝቅተኛ ደረጀ ላይ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው ለመርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች እጥረት እና የመምህራን የክፍለ ጊዜ ጫና ናቸው። እናም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ለትምህርቱ ማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ማቴሪያሎችን በበቂ ሁኔታ ቢያቀርቡ፣ እንዲሁም የመምህራንን የክፍለ ጊዜ ጫና በሳምንት ከ20 ክፍለ ጊዜ እንዳይበልጥ ቢያደርጉ የተሻለ ነው።

4. መምህራን ተማሪዎች የቃላትን ትርጉም እንዳይረሱ ትምህርቱን ትርጉም ያለው (ተጨባጭ) ከማድረግ አንፃር እና በተለያዩ ጊዜያት ትምህርቱን እየደጋገሙ ማስተማርን በተመለከተ በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ አድርገዋል። የእነዚህ ስልቶች በተማሪዎች ዘንድ የቃላት ትርጉም በአእምሯቸው ተቀርፆ ይቀር ዘንድ ያላቸው አስተዋፅዖ የጎላ ነው። ነገር ግን ስልቶቹን መምህራን በአግባቡ እንዳያቀርቡ በምክንያትነት የሚጠቅሷቸው የተማሪዎች ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት እና ለአማርኛ ቋንቋ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አናሳ መሆን ናቸው። በመሆኑም የመማር ማስተማር ሂደቱ የተቀላጠፈ ይሆን ዘንድ የሚመለከታቸው ክፍሎች ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች እንዲጨመሩ እና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜም በሳምንት ከ2 ወደ 3 ከፍ እንዲል ቢያደርጉ መልካም ነው።

መዳዬ ቃላት

ሁለተኛ ቋንቋ	Second language
ማሚያ ተቃራኒ	Complementaries
ማቅረብ	Presenting
ማጠናከሪያ	Consolidation
ምስል ከሳች	Imaginary
ምጋቤ ምላሽ	Feedback
ሰርቶ ማሳያ	Demonstration
ርዕሰ ጉዳይ	Topic areas
ሰዋሰው	Grammar
ስዕላዊ ሰንጠረዥ	Pictorial schemata
ቃላት	Vocabulary
ቃላትን መምረጥ	Choosing Vocabulary
ቅርፅ	Form
ቅጥያዎች	Affixes
ብዛት	Quantity
ብያኔ	Definition
ተለዋዋጮች	Variables
ተቃራኒ ቃላት	Antinomies
ተዛማጅ ምስረታ	Relative structure
ተዛማጅ ቃላት	Synonyms
ተዛምዶአዊ ትርጉም	Meaning relationships
ተገቢነት	Appropriateness
ትርጉም	Translation
ንበት	Pronunciation
ንፅፅራዊ ተቃራኒ	Gradable antinomies
አላማ	Aim
አበሮ የሚሄዱ	Collocation

አውድ	Context
እርባታ	Derivation
እማሪያዊ ፍቺ	Denotation
ወሰን አልባ	Open system
ወሰን ያለው	Closed system
ዘላቂ ትውስታ	Long term memory
የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎች	Visual Aids
የቃላት ግንባታ	Word formation
የቅርብ ትውስታ	Short term memory
የተለመዱ ቃላት	Commonest word
የአፍ መፍቻ ቋንቋ	Mother language
የግንዛቤ ማረጋገጫ	Check understanding
ድግግሞሽ	Frequency
ገለፃ	Description
ግልባጫዊ ተቃራኒ	Conversance
ጥመራ	Coinage
ጥምር ቃል	Compound word
ፍላጎት	Need
ፍካሪያዊ	Connotation
ሕግ	Rule

ዋቢ ጽሑፎች

ማረው አለሙ እና ተስፋዬ አበራ (1993) "አማርኛ ቋንቋን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማስተማሪያ ዘዴ" (ያልታተመ) ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

ሲሳይ ተበጀ (1990) "በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሥራ ላይ ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መመሪያ መፅሐፍ ውስጥ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት"፣ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ሽመልስ በጅጋ (1993) "አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርት ትግበራ ግምገማ በኦሮሚያ ክልል 8ኛ ክፍል ናሙናነት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሑፍ ክፍል የቀረበ ሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ፅሑፍ።

ባየ ይማም (1986) የአማርኛ ሰዋሰው፣ አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ።

ትንሳኤ ብርሃኔ (1988) "የአማርኛ ቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት" የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አንበሴ በቀለ (1993) "በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና"፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

እሸቱ አጋ (1997) "በአዲስ አበባ መስተዳድር ክልል በሚገኙ ሦስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ግምገማ"፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

የሽጥላ መንግስቱ (1997) "በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ውስጥ የቃላት ትምህርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ግምገማ"፣ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ወንድወሰን አዳነ (1995) "አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የሥነ ፅሁፋዊ ይዘቶች ፋይዳ፣ አመራረጥና አደረጃጀት"፣ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የተቀረፀውትን የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶች ለማሻሻል በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ፣ ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ኢንስቲትዩት።

Alemu, H. (1994) '"High School Teachers' Attitudes Towards Teaching Vocabulary" Addis Ababa University.

Allen, V.F. (1983) Techniques in Teaching Vocabulary. Oxford: Oxford University Press.

Brandt, K. S ed, (1981) Applied Strategies for Curriculum Education. Washington: Assoication for Supervision Development.

Brown, H. (1994) Teaching by Principles: An International Approach and Language pedagogy. London: Prentice Hall.

Brown, R and McNeill, D (1966) "the Tip of the Langue Phenomenon". Journal of Verbal learning and Verbal Behaviour:35-37.

Celce Murcia, (1991) Teaching English as a second or foreign Language. Boston: Heinle Publishers.

Choi, Uhu-Kyung (1990) "Vocabulary: in English Language Teaching" in Verner (eds) Language Use Language Teaching and the Curriculum. Hong Cong; Institute of Language in Education.

Cook,V. (1991). Second Language Learning and Language Teaching. London: Edwrd Arnold.

Cumino, Margherta (1990) "The Role of Vocabulary in Foreign Language Teaching" David Hill and Susan Holden (eds.) /Effective Teaching and Learning. Modern English Publications /5-20/.

ETP (1994) "Education and Training Policy". Addis Ababa.

Grains, R and Redman, S. (1986) Working with Words: A guide to Teaching and Learning Vocabulary. Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, J (1995 8th ed) Practice of English Language Teaching. New York: Cambridge University Press.

Harmer, J. (1991). The Practice of English Language Teaching. London: Longman Group (UK) Limited.

Harmer,J. and Rosser, R. (1998) More than Words: vocabulary for upper intermediate to advanced students; Book 1. Singapore: Long man Group UK Limited.

Haycraft, J. (1991) An introduction to English language Teaching. Singapore: Long man Group UK Limited.

Kassie, Shiferaw (1995) "How ELT Teachers Cope with Large Class with Reference to Grade 10 Teachers." Addis Ababa University.

Lado, R. (1964) Language Teaching. New York: McGraw-Hill Inc.

Lang,G. and George D. H (1991). A Practical Guide to Research Methods (4th ed). New York: University of America.

Maley, A (1990) "the Word's the thing" In Hill, D. and Susan Holden (eds.) Effective Teaching and Learning. London: Modern English Publications 10-14.

Mc Carthy, M. (1990) Vocabulary: Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Nasr, R. T. (1979 4th ed) Teaching and Learning English. London: Zowe and Brydone Printers Ltd.

Nunan, D. (1988) Designing for the Communicative Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Papalia, D. A & Wendkosolds, S. (1985) Psychology. New York: McGraw Hill Book Company.

Pettigrew, J. (2006) "Teaching Vocabulary: Two Dozen Tips and Techniques." From http://people.bu.eduljpettigr/Artilces-and-presentations/vocabulary.htm.

Richards J. C. and T. Rodgers (2001) Approaches and Methods in Language Teaching. (6th edition) Delhi: Cambridge University Press.

Richards, J. (1985) The Context of Language Teaching. Cambridge: CUP.

Richards, J. and Rodgers, T. (1995) Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: CUP.

Richards, J. C. and Rodgers, T.S. (1986). Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Seal, B. (1991) "Vocabulary Learning and Teaching" in Marianne CeleceMuricia (eds.) Teaching English of Foregn Language (2nd ed.). Foreign.Boston, Heinle and Heinle Published.

Taylor, L. (1990) Teaching and Learning Vocabulary.London: Prentice Hall international (UK).

Ur, p. (1996) A course in Language Teaching Practice and Theory. Cambridge. Cambridge University Press.

Wallace, M. (1987) Practical Language Teachiong. London: Biddles Ltd.

Wallace, M. L. (1981) Vocabulary Building and Word study. New York: McGraw. Hill Book Company.

West, M. (1963) Teaching English in Difficult Circumstances. London: Longmans. Green and Cottd.

Wilkins D. A. (1972). Linguistics in Language Teaching. London: Edward Arnold (Publishers) Ltd.

Wright, Andrew (1989) Pictures for Language Learning. New York: Cambridge University Press.

አባሪዎች

አባሪ አንድ

የቃላት ትምህርት መማር ማስተማር ክንውን ምልከታ ማረጋገጫ

ቅፅ (Check list)

የትምህርት ቤቱ ስም/ኮድ/ _____

ምልከታ የተካሄደበት የክፍል ምድብ _____ ፈረቃ _____ ክ/ጊዜ _____

የመምህሩ ኮድ _____

ሰዓት _____

በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪ ቁጥር _____

ቅፁን (Check list)ን የሚሞላው ባለሙያ ሥም _____

ተ.ቁ	የምልከታ መስፈርቶች	ደረጃው ዝቅተኛ	ደረጃው ከፍተኛ	አጥጋቢ	ደረጃው ከፍተኛ	ደረጃው ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
1	በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች					
	1.1 የቃላት ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እና ንበት 1.2 የቃላት ትርጉም 1.3 የቃላት ግንባታ					
2	የቃላት ትምህርት ከማቅረቢያ ስልቶች አንፃር					
	2.1 የቃላትን ትርጉም ለተምህርት በቀረበው ቋንቋ በሌሎች ቃላት ብያኔ በመስጠት ማቅረብ 2.2 ለቃሉ ፍቺ ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት 2.3 ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት 2.4 ቃላትን የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም ማቅረብ 2.5 አካላዊ ምላሽ ዘዴን በመጠቀም ቃላትን ማስተማር 2.6 የቃላትን ትርጉም አውድ ፈጥሮ ማቅረብ 2.7 ተዛማጅ ቃላትን በመጠቀም ማቅረብ 2.8 አብረው የሚሄዱ ቃላትን በማዛመድ ማቅረብ 2.9 ቃሉ በአፍ መፍቻቸው ቋንቋ አቻ ቃል በመተርጎም ማቅረብ 2.10 ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ 2.11 ቃላትን በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አካቶ ማቅረብ 2.12 ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ 2.13 የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት ማሳየት					
3	ቃላትን እንዲያስታውሱ ከማድረግ አንፃር					
	3.1 ተማሪዎች በቃላት ትርጉም ላይ ትርጉም ያለው ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ 3.3 ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም ማስተማር ተማሪዎች 3.3 ለቃላት ትርጉም የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃቶችን መጠቀም:: 3.4 የቃላትን ትርጉም በተለያዩ ጊዜያት እየደጋገሙ ማስተማር					

አባሪ ሁለት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፍ ክፍለ ትምህርት
በሸሬ፣ በእንዳባጉና፣ በሐክፈን እና በአዲዳሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች
በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን
የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

ውድ መምህራን፦

የዚህ ፅሑፋዊ መጠይቅ ዓላማ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቃላት ትምህርት እንዴት እንደሚቀርብ የሚያመለክት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። መጠይቁ ሶስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል መጠይቁን ስለሚሞሉት መምህራን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ነው። ሁለተኛው ክፍል ስለ ቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና በአቀራረብ ወቅት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጠዎች ሁኔታ በአምስት አማራጭ መልሶች ማለትም 5 በጣም ከፍተኛ፣ 4 ከፍተኛ፣ 3 መካከለኛ፣ 2 ዝቅተኛ፣ 1 በጣም ዝቅተኛ በማለት መልስ የምትሰጡባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ሌላው በሶስተኛው ክፍል የቀረቡትጥያቄዎች ደገሞ የጥያቄዎችን የአጠያየቅ መንፈስ በመከተል መልስ የምትሰጡባቸው ሌላው ናቸው። ስለዚህ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእናንተን ትብብር ሲያገኝ በመሆኑ መጠይቁን በትክክል እንዲሞሉ በትህትና ይጠየቃሉ። መጠይቁን በመሙላት ለሚያደርጉት ትብብርም በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን።

ማሳሰቢያ፦ ሀ. መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም።

ለ. መጠይቁን ከሌላ የሥራ ባልደረባ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው።

ክፍል አንድ፦ የመምህራን የግል መረጃ መስጫ

የትምህርት ቤቱ ሥም _____

የአገልግሎት ዘመን _____

የትምህርት ደረጃ _____

የስልጠና ሁኔታ፦ ዓብይ _____

ንዑስ _____

ፆታ፦ ወንድ _____ ሴት _____

የሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ _____ ሴክሽን _____

በሳምንት ያለዎት የክፍለ ጊዜ ብዛት _____

ክፍል ሁለት:– ስለቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ የቀረቡ ጥያቄዎች

መመሪያ:– የመረጡትን መልስ ከጥያቄዎቹ ትይዩ ባለው ሰንጠረዥ ላይ የ(✓) ምልክት በማድረግ ያመልክቱ::

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	እጅግ ከፍተኛ	ከፍተኛ	አማካይ	ዝቅተኛ	እጅግ ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
1	የቃላት ትምህርትን በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ::					
2	የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት አስተምራለሁ					
3	የቃላትን ትርጉም አስተምራለሁ					
4	የቃላትን ግንባታ አስተምራለሁ					
5	ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ብያኔ በመስጠት የቃላትን ትርጉም አቀርባለሁ					
6	ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት ቃላትን አስተምራለሁ					
7	ለዋናው ቃል ትርጉም ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት አቀርባለሁ					
8	ቃላትን ለማስተማር የተለያዩ መግለጫዎችን እጠቀማለሁ					
9	አካላዊ ምላሽን በመጠቀም ቃላትን አስተምራለሁ					
10	አውድ ፈጥሬ ቃላትን በማቅረብ ትርጉምን አለማምዳለሁ					
11	ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላትን በማቅረብ ትርጉምን አለማምዳለሁ					
12	አብረው የሚሄዱ ቃላትን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት እጠቀማለሁ					
13	የቃላትን ፍቺ በአፍ መፍቻቸው በመተርጎም አቀርባለሁ					
14	የቃላትን ትምህርት በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አካትቼ አቀርባለሁ					
15	ቃላትን ተማሪዎች ከመዝገበ ላት እንዲማሩ አደርጋለሁ					
16	ቃላትን እንዳይረሱ የራሳቸውን የማስታወስ ብልሃት እንዲጠቀሙ አደርጋለሁ::					
17	ትርጉም ያለው ልምምድ በማድረግ የቃላትን ትርጉም አስተምራለሁ					

18	ምስል ካሳች ቃላትን በመጠቀም አስተምራለሁ					
19	የቃላትን ትርጉም እንዳይረሱ በተለያዩ ጊዜያአት እየደጋገምኩ አስተምራለሁ					
20	ለቃላት ትምህርት የመማሪያ መፅሐፉን እጠቀማለሁ					
21	ለቃላት ትምህርት የግል ማቴሪያል አዘጋጅቼ አስተምራለሁ					
22	የቃላት ትምህርት አቀራረብን የሚመለከት አጫጭር ስልጠናዎችን በአየጊዜው እወስዳለሁ					

መመሪያ ሁለት:– ከዚህ በታች ሁለት ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ስለዚህ የእያንዳንዱን ጥያቄ የአጠያየቅ መንፈስ በመከተል መልሳችሁን በግልፅ አስፍሩ::

1. የቃላትን ትምህርት በአግባቡ እንዳያቀርቡ የሚያደርጉ አደናቃፊ ሁኔታዎች አሉ? ካሉ በዝርዝር ይጥቀሱ _____

_____

_____

_____

2. ከቋንቋ ትምህርት አብይ እና ንዑስ ክሂሎች መካከል አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸውን ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በቅደም ተከተል ያስቀምጡ

_____ መፃፍ _____ ቃል

_____ ማንበብ _____ ሰዋሰው

_____ መናገር _____ ማዳመጥ

3. የቃላት ትምህርት አቀራረብን በሚመለከት ያለዎትን አጠቃላይ አስተያየት አጠር አድርገው ያስፍሩ::

_____

_____

_____

_____

መጠይቁን ሞልተው በመመለስዎ ከልብ የመነጨ ምስጋናየን አቀርባለሁ::

ደረበ መሉ

አባሪ ሦስት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፍ ክፍለ ትምህርት

በሽሬ፣ በእንዳባጉና፣ በሐክፈን እና በአዲዳሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚማሩ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች፡–

የዚህ ፅሑፋዊ መጠይቅ ዓላማ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቃላት ትምህርት በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚቀርብ የሚያመለክት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። መጠይቁ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ክፍል መጠይቁን ስለሚሞሉት ተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የሚገልፅ ነው። ሁለተኛው ክፍል የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብን በተመለከተ በአምስት አማራጭ መልሶች ማለትም 5 በጣም ከፍተኛ፣ 4 ከፍተኛ፣ 3 መካከለኛ፣ 2 ዝቅተኛ እና 1 በጣም ዝቅተኛ በማለት መልስ የምትሰጡባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእናንተን ትብብር ሲያገኝ በመሆኑ መጠይቁን በትክክል እንድትሞሉ በትህትና ትጠየቃላችሁ። መጠይቁን በመመላት ለሚያደርጉት ትብብርም በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን።

ማሳሰቢያ፡– ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም።

ለ. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር በመወያየት መመላት በሚሰበሰበው መረጃ ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር አያስፈልግም።

ክፍል አንድ፡– የፅሑፍ መጠይቁን ለሚሞሉ ተማሪዎች አጠቃላይ የግል መረጃ መስጫ

የትምህርት ቤቱ ስም _____

እድሜ _____

ፆታ _____

የክፍል ምድብ /ሴክሽን/ _____

ክፍል ሁለት:– ስለ ቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ የቀረቡ ጥያቄዎች

መመሪያ አንድ:– የመረጡትን መልስ ከጥያቄው ትይዩ ባለው ሠንጠረዥ የ"✓" ምልክት በማድረግ ያመልክቱ::

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	እጅግ በጣም ከፍተኛ	ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ	እጅግ በጣም ዝቅተኛ
		5	4	3	2	1
1	የቃላት ትምህርትን መምህራን ያቀርቡልናል::					
2	መምህሩ የቃላት ትምህርትን በአግባቡ ያቀርብልናል					
3	የቃላትን ሰዋሰዋዊ ቅርፅና ንበት እንማራለን:					
4	የቃላትን ግንባታ (ቅጥያ፣ ጥመራ፣ ፊሊጥ) እንማራለን					
5	የቃላትን ትርጉም እንማራለን					
6	የቃላትን ትርጉም ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ብያኔ በመስጠት ይቀርብልናል					
7	ጥልቅ ማብራሪያ በመስጠት የቃላት ትርጉም ያስተምረናል::					
8	ለዋናው ቃል ዝርዝር ምሳሌዎችን በመስጠት ያቀርብልናል					
9	አካላዊ ምላሽን በመጠቀም የቃላትን ፍቺ መምህሩ ያስተምረናል					
10	ለቃላተን ትርጉም አውድ ፈጥሮ ያስተምረናል					
11	በተመሳሳይ እና በተቃራኒ ቃላት ትርጉምን እንለማመዳለን					
12	አብረው የሚሄዱ ቃላትን ለትምህርቱ ማቅረቢያነት መምህሩ ይጠቀማል					
13	ልዩ ልዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የቃላትን ትርጉም ያቀርብልናል::					
14	የቃላት ፍቺ በትግርኛ ቃላት ተተርጉሞ ይቀርብልናል					
15	የቃላት ትምህርት በሌሎች ክሂሎች ተካቶ ይቀርብልናል					
16	ቃላትን ከመዝገበ ቃላት እንማራለን					
17	ትርጉም ባለው ልምምድ የቃላትን ፍቺ እንማራለን					
18	ምስል ከሳች ቃላትን በመጠቀም ያስተምረናል					
19	ቃላትን እንዳንረሳ የራሳችንን የማሰታወስ ስልት እንጠቀማለን					
20	የቃላትን ትርጉም እንዳንረሳ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ እንማራለን::					
21	የቃላት ትምህርትን ከመማሪያ መፅሐፋችን እንማራለን					
22	መምህራችን የግል ማቴሪያል በማዘጋጀት ቃላትን ያስተምረናል					

መመሪያ ሁለት:– የቃላት ትምህርት አሰጣጡን በሚመለከት ያላችሁን አሰተያየት በአጭሩ አስፍሩ::

.....

.....

.....

መጠይቁን ሞልተው በመመለስዎ ከልብ የመነጨ ምስጋናየን አቀርባለሁ::

ደረበ ሙሉ

የምልከታ የጊዜ ሰሌዳ

የትምህርት ቤቱ ስም	የመምህሩ ኮድ	ምልከታ የተካሄደበት ቀን	ክፍለ ጊዜ	ፈረቃ	ሌክቸረን	የተማሪው ቁጥር	የት/ት ዋና ርዕስ	የተጠቀመበት ማቴሪያል	ገፅ	የቀረበው ይዘት
	የ	4/09/99	4	ጧት	H	58	አንብቦ መረዳት	የመማሪያ መፅሐፍ	115	ፍቺ ትርጉም
		15/09/99	5	ከሰዓት	H	58	የቃለት ጥብቀት	የመማሪያ መፅሐፍ	-	ትርጉም
		16/09/99	4	ከሰዓት	H	58	ሰዋሰው	የመማሪያ መፅሐፍ	12	መዋቅር
ሸሬ ከ/2ኛ ደረጃ	ት	9/09/99	2	ጧት	M	58	ሥነ ፅሑፍ	የመማሪያ መፅሐፍ	131	ፊሊጦች
		16/09/99	2	ከሰዓት	M	58	ሰዋሰው	የመማሪያ መፅሐፍ	135	የሚቧደኑ ቃላት
		17/09/99	1	ከሰዓት	M	58	ሰዋሰው	የመማሪያ መፅሐፍ	-	የቃል ክፍሎች
	ፀ	09/09/99	1	ከሰዓት	U	56	ሰዋሰው	የግል	-	ስም
		17/09/99	3	ከሰዓት	U	56	ሰዋሰው	የግል	-	ቅፅል
		24/09/99	2	ጧት	U	56	ሰዋሰው	የግል	-	ግስ
አዲዳሮ ከ/2ኛ ደረጃ	ን	08/09/99	5	ጧት	B	67	ሰዋሰው	መማሪያ መፅሐፍ	102	ትርጉም
		15/09/99	2	ጧት	B	67	መዛፍ	መማሪያ መፅሐፍ	103	ትርጉም
		21/09/99	4	ከሰዓት	B	67	ሰዋሰው	መማሪያ መፅሐፍ	94	የቃላት ምስረታ
እንዳባጉና ከ/2ኛ ደረጃ	ድ	14/09/99	6	ጧት	F	66	ሥነ ፅሑፍ	መማሪያ መፅሐፍ	130-131	ፊሊጣዊ ንግግሮች
		17/09/99	2	ጧት	F	66	አንብቦ መረዳት	መማሪያ መፅሐፍ	135	ትርጉም
		22/09/99	4	ከሰዓት	F	66	ሰዋሰው	መማሪያ መፅሐፍ	135	መዋቅር
ሐከፈን ከ/2ኛ ደረጃ	ም	10/09/99	5	ከሰዓት	G	68	ሥነ ፅሑፍ	መማሪያ መፅሐፍ	130	ፊሊጦች
		16/09/99	1	ጧት	G	68	ሰዋሰው	የግል	-	አያያዥ እና ገላጭ ቃላት
		23/09/99	1	ጧት	G	68	አንብቦ መረዳት	መማሪያ መፅሐፍ	134	ትርጉም

አባሪ አምስት

ቀረፃ አንድ

የመምህራ ኮድ	ም
የት/ቤቱ ስም	ሐክፈን 2ኛ ደረጃ
ምልከታ የተካሄደበት ቀን	16/09/99
ፈረቃ	ጧት
ክፍለ ጊዜ	ጧት 1
ሴክሽን	9ኛ ጂ
የማቴሪያል ሁኔታ	በግል የተዘጋጀ
የትምህርት ርዕስ	አያያዥ እና ገላጭ ቃላት

ልክ 2፡10 ጧት አጥኚው ከሶስት የምልከታ ረዳቶች ጋር፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ እና የቪዲዮ ቀረፃው በ9ኛ ጂ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል። ከዚያም የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ጥቁር ሰሌዳውን ካፀዳ በኋላ አያያዥ ቃላት እና ገላጭ ቃላት ብሎ ሰሌዳው ላይ ፃፈ። ከዚያም ስለ አያያዥ ቃላት የተወሰነ ገለፃ ካደረገ በኋላ በግሉ ያዘጋጀውን ምንባብ እንደሚያነብላቸው እና ተማሪዎችም በጥሞና አዳምጠው አያያዥ ቃላት እንዲያወጡ አዘዘ።

መምህሩ ምንባቡን አነበበ። ምንባቡን ካነበበ በኋላ ተማሪዎች ከምንባቡ ያዳመጧቸውን አያያዥ ቃላት እንዲናገሩ አዘዘ። ተማሪዎችም እጃቸውን እያወጡ አያያዥ ቃላትን ዘረዘሩ። ከተዘረዘሯቸው ቃላትም መካከል ነገር ግን፣ ስለዚህም፣ ግን፣ ስለሆነም የሚሉት ይገኙበታል። መምህሩ እንደገና የእነዚህ አያያዦች አገልግሎት ምን እንደሆነ አሁንም መልሦ ተማሪዎችን ጠየቃቸው። ተማሪዎችም አፍራሽን፣ ማጠናከሪያን ወዘተ. በማለተ መልስ ሰጥተዋል።

መምህሩ ከዚያም ስለ አያያዥ ቃላት በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎችን ማስታወሻ እነዲይዙ አድርጓል። በመቀጠልም መምህሩ ተማሪዎች የተማሩትን መሠረት በማድረግ የክፍል ሥራ እንዲሰሩ ሰጣቸው ከተሰጡት ጥያቄዎች መካከል አልማዝ ቤት ደረሰች ስልክ ደውላልኝ አለች፣ ጥሩ ውጤት አመጣች ሽልማት ተሰጣት የሚሉት የገኙበታል።

ትዕዛዙም ጥገኛ ምዕላድ ጨምራችሁ አረፍተ ነገርን አሟሉ የሚል ነው። ከዚያም በኋላ ተማሪዎች የክፍል ሥራውን ሰሩ፣ በክፍል ውስጥ ዕርማት ተሰጣቸው፣ ያልገባቸውንም እንዲጠይቁ ተደርጎ የዕለቱ ትምህርት ተቋጨ።

ቀረፃ ሁለት

የመምህሩ ኮድ	ት
የት/ቤቱ ሥም	ሽሬ ከ12ኛ ደረጃ
ምልከታ የተካሄደበት ቀን	16/09/99
ፊረቃ	ከሰዓት
ክፍለ ጊዜ	2
ሴክሽን	9ኛ ኤም
የትምህርት ርዕስ	የቃላት ክፍሎች
የማቶሪያል ዓይነት	በግል የተዘጋጀ

ልክ ሰዓት 7:20 ላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ፣ ምልከታ አድራጊዎች እና ቪዲዮ ቀራፂው 9ኛ ኤም ክፍል ተገኝተዋል። መምህሩም ለተማሪዎች ሰላምታ ከሰጠ እና ጥቁር ሰሌዳውን ካፀዳ በኋላ የቃላት ክፍሎች የሚል ርዕስ ፃፈ። ከዚያም ስለ ቃላት ምንነት በርካታ ተማሪዎች እንዲናገሩ ካደረገ በኋላ ትክክለኛውን የቃል ብያኔ በመስጠት እንደገና ለብያኔው ማብራሪያ ሰጥቷል። ለዚህም የተዘበራረቁ ሆሄያትን በመስጠት ቃላትን እንዲመሰርቱ አድርጓል። እነዚህ ሆሄያትም ና፣ መ፣ ኪ ናቸው። ተማሪዎች መኪና የሚለውን ቃል ከመሰረቱ በኋላ መምህሩ ቃል የሆሄ ስብስብ የሚሆነው ሆሄያት በስርዓት ከተደረደሩ እንደሆነ ገለፃ አድርጓል።

በመቀጠልም መምህሩ የቃል ክፍሎችን ተማሪዎችን በመጠየቅ እና በማስተካከል ስም፣ ቅፅል፣ ግስ፣ ተውሳከ ግስ እና መስተዋድድ መሆናቸውን አንድ ባንድ አስረድቷል። ከዚያም የተለያዩ ቃላትን በመስጠት በቃል ክፍላቸው እንዲያዛምዱ ትዕዛዝ ሰጠ። ከተሰጡት ቃላት መካከል ትልቅ፣ ሰው፣ መምህር፣ ተናገረ የሚሉትን በሌላ ወገን ከተዘረዘሩት ስም፣ ቅፅል፣ ግስ፣ ተውሳከ ግስ እና መስተዋድድ ጋር እንዲያዛምዱ ተደርጓል። ተማሪዎችም የተዘዙትን በደብራቸው ከሰሩ በኋላ ለአስተማሪያቸው

አሳርመዋል። በመጨረሻም መምህሩ ርማቱን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከሰጠ በኋላ ያልገባቸውን በመጠየቅና ለጠየቁት ምላሽ በመስጠት ትምህርቱ ተቋጭቷል።

ቀረፃ ሦስት

የመምህሩ ኮድ	የ
የት/ቤቱ ሥም	ሽሬ ከ2ኛ ደረጃ
ምልከተ የተካሄደበት ቀን	16/09/99
ፊረቃ	ከሰዓት
ክፍለ ጊዜ	4
ሴክሽን	9ኛ ኤች
የትምህርት ርዕስ	ቅጥያ ምዕላድ
የማቶሪያል ዓይነት	የመማሪያ መፅሐፍ እና የግል ማቴሪያል

ከሰዓት 9፡01 ሰዓት ላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህሯ፣ ምልከታ አድራጊዎች እና ቪዲዮ ቀራፂው 9ኛ ኤች ክፍል በ4ኛው ክፍለ ጊዜ ተገኝተዋል። በመቀጠል መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ ካቀረበች በኋላ የመማሪያ መፅሐፋቸውን እና ደብተራቸውን እንዲያወጡ ከአዘዘች በኋላ ጥቁር ሰሌዳውን አፅድታ ቅጥያ ምዕላድ በሚል ርዕስ ሥር ኖት በመፃፍ ተማሪዎች እንዲፅፉ አዘዘች። በኖት መልክ ያፃፈቻቸው ንዑስ ርዕሰችም ቅድመ ግንድ፣ ውስጠ ግንድ እና ድህረ ግንድ ቅጥያ የሚሉትን ነው።

አስተማዋ በመቀጠል ስለቅድመ ግንድ፣ ውስጠ ግንድ እና ድህረ ግንድ ቅጥያ ከተማሪዎች ጋር በጥያቄና መልስ ማብራሪያ ሰጥታለች። ለምሳሌ «ሰበርኩላት» የሚለውን ቃል ሰበር-ኩ-ላት በማለት ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን አሳይታለች። በመጨረሻም የክፍል ሥራ በመሥጠት እና በማረም ከዚያም ያልገባቸውን በመጠየቅ የዕለቱን ትምህርት ለማጠቃለል ሞክራለች። የክፍል ሥራው የጥያቄዎች ትዕዛዝ የሚከተሉትን ምዕላዶች በተገቢ ቦታቸው እያስገባችሁ የአረፍተ ነገሮችን ሃሰብ አሟሉ የሚል ነበር። ከጥያቄዎችም መካከል _____ አንተ _____ መጣ ካሣ _____ አየሁት የሚል ሲሆን መልሶቹም ወደ፣ ስ፣ን በቅደም ተከተል እንደሚገቡ ርማት የተሰጠባቸው ናቸው።

ቀረፃ አራት

የመምህሩ ኮድ	ድ
የት/ቤቱ ሥም	እንደበጉና 2ኛ ደረጃ
ምልከታ የተካሄደበት ቀን	17/09/99
ፊረቃ	ጧት
ክፍለ ጊዜ	2
ሴክሽን 9ኛ	ኤፍ
የትምህርት ርዕስ	የቃል ክፍል
የማቴሪያል ዓይነት	የተማረው መማሪያ መፅሐፍ
የትምህርት ይዘት	አያያዥ እና ገላጭ ቃላት

በሰዓት 2፡42 ጧት አጥኚው እና የምልከታ ረዳቱ፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ እና የቪዲዮ ቀረፃው በ9ኛ ኤፍ ክፍል ተገኝተዋል። በቀጠልም መምህሩ ጥቁር ሰሌዳውን ካፀዳ በኋላ ተማሪዎች መፅሐፍና ደብተራቸውን እንዲያወጡ አዘዘ፤ ተማሪዎችም ትዕዛዙን ከፈፀሙ በኋላ መምህሩ የቃል ክፍል የሚል ርዕስ ዓፈና ተማሪዎች የመፃፋቸውን ገፅ 135 እንዲያወጡ አዘዘ። ከዚያም በገፅ 135 ያለውን መልመጃ ምሳሌ በማሳየት እና የቃል ክፍሎችን እነማን እንደሆኑ ከተማሪዎች ጋር ከተወያየ በኋላ በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ አዘዘ።

ጥያቄው የሚለው "በምሣሌው መሠረት የተሰመረባቸውን ቃላት ከተመሳሳይ የቃል ክፍል በተመረጡ አባባሎች ተኩ" ነበር። ምሳሌው እንደ ፈለገች፣ ስለፈለገች፣ ከፈለገች የሚል ነው። ከጥያቄዎች መካከል ደግሞ ውበታ ፈነዳ፣ ወደ አዘቅት የሚሉ ናቸው። እነዚህን የተሰመረባቸውን የቃል ክፍላቸውን እንዲፅፉ እና ከዚያም በሌሎች ተመሳሳይ ቃላት እንዲተኳቸው በማዘዝ መምህሩ የተማሪዎችን አሰራር እየዞረ ሲያረጋግጥ ቆይቶ ለጥያቄዎቹ ርማት ሰጥቷል።

በመጨረሻም ለተማሪዎች ሁለት ሁለት የራሳቸውን ቃላት በማዘጋጀት እና አንዱን በማስመር ለእነዚህ ቃላት በተመሳሳይ ፍቺ እንዲተኩ የቤት ሥራ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት አጠናቋል።

ቀረፃ አምስት

የመምህሩ ኮድ	0
የት/ቤቱ ሥም	ሽሬ ከ2ኛ ደረጃ ት/ቤት
ምልከታ የተካሄደበት ቀን	17/09/99
ፊረቃ	ከሰዓት
ክ/ጊዜ	3
ሴክሽን	9ኛ ዩ
የትምህርት ርዕስ	ቃል እና የቃል ክፍሎች፣ የትምህርት ይዘት ቅፅል
የማቴሪያል ዓይነት	በግል የተዘጋጀ

ልክ ሰዓት 8፡02 ላይ አጥኚው ከሁለት ረዳቶች ጋር፣ ቪዲዮ ቀራፂው እና የአማርኛ ቋንቋ መምህሯ በ9ኛ ዩ ክፍል ተገኝተዋል። ከዚያም መምህሯ ጥቁር ሰሌዳውን ካፀዳች በኋላ "ቃልና የቃል ክፍሎች" በማለት በርዕስነት ከፃፈች በኋላ በሥሩ ቅፅል የሚል ይዘትን በመፃፍ የማስተማር ስራዋን ጀመረች።

በመጀመሪያ መምህሯ ተማሪዎች ወረቀት እና እስክሪብቶ በማውጣት የስድብ ዓይነቶችን እንዲፅፉ ትዕዛዝ ሰጠች። ተማሪዎችም ለተወሰኑ ደቂቃዎች የታዘዙትን ፃፉ። እንደገና መምህሯ የማሞገሻ ቃላተን እንዲፅፉ ትዕዛዝ ሰጠች። ተማሪዎቹ አሁንም ይህንን ፈፀሙ። ከዚያም መምህሯ ተማሪዎች ቡድን እንዲመሠርቱ አደረገች። ተማሪዎች የፃፏቸውን ቃላት እርስ በርስ ተቀያይረው በቡድን እንዲወያዩባቸው አደረገች። በመጨረሻም ተማሪዎች የፃፏቸውን ቃላት እኛቸውን እያወጡ በእየርዕሳቸው ሥር በመዘርዘር ለመምህሯ ተናገሩ። መምህሯም ቃላትን ከፃፉ በኋላ የተዘረዘሩትን ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ምላሻቸውን ሰጡ።

<u>የስድብ</u>	<u>የማሞገሻ</u>
ደደብ	ጎበዝ
ጅል	ቆንጆ

የሚሉት ይገኙበታል።

በመጨረሻም መምህሯ ቅዕሎችን ነባር እና ውልድ ቅዕል በማለት በምሳሌ ካብራራች በኂላ ለተማሪዎች የቤት ሥራ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት አጠናቃለች።

ቀረፃ ስድስት

የመምህሩ ኮድ	ን
የት/ቤቱ ሥም	አዲዳሮ 2ኛ ደረጃ
ምልከታ የተካሄደበት ቀን	21/09/99
ፊረቃ	ከሰዓት
ክፍለ ጊዜ	4
ሴክሽን	9ኛ ቢ.
የትምህርት ርዕስ	የቃላት ምስረታ
የማቶሪያል ዓይነት	የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ

ከሰዓት 8፡42 ላይ ሁላችንም ማለትም የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ፣ ምልከታ አድራጊዎች እና የቪዲዮ ቀራፂው በ9ኛ ቢ. ክፍል በአራተኛው ክፍለ ጊዜ ተገኝተናል። መምህሩም ተማሪዎችን መፅሐፋቸውን ገፅ 94 ላይ እንዲያወጡ ካደረገ በኂላ የቅዕል እና የስም አመሠራረትን በአጭሩ ገለፃ አደረገ። በመቀጠልም የቃል ክፍሎችን አንድ ባንድ በማንሳት ጠቅለል ያለ ገለፃ አደረገ ተማሪዎችንም በጥያቄና መልስ አሳተፈ።

መምህሩ በተማሪዎች መፅሐፍ በገፅ 94 ያለውን መልመጃ ምሳሌ በመስጠት የክፍል ሥራ እንዲሰሩት አዘዘ። ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኂላ የተማሪዎችን ሥራ መምህሩ እየዞረ ካረመ በኂላ ከተማሪዎች ጋር በጋራ ለጥያቄዎቹ ርማት ሰጠ። የጥያቄው ትዕዛዝ የተሰመረባቸውን ቃላት ቅርፅ ቀይሩ የሚል ሲሆን ለምሳሌ፦ የታሪክ ስፍራ ታሪካዊ ስፍራ በማለት ስምን ወደ ቅዕል ሲቀይሩ ታይተዋል። አሁንም መምህሩ በመፅሐፋቸው በዚሁ ገፅ ያለውን መልመጃ ምሳሌ በመሥጠት እንዲሰሩ አዘዘ እና እርማት ሰጡ። የጥያቄዎች ትዕዛዝም የተሰመረባቸውን ቃላት ቅርፅ ቀይሩ የሚል ሲሆን የተሰመረባቸው ቃላት ግሶች ናቸው የሚቀየሩት ደግሞ ወደ ቅዕል ነበር። ከጥያቄዎች ማካከልም - ቅጠል <u>ለቀመ</u> - ምስል <u>ቀረፀ</u>
- ንብረት <u>ዘረፈ</u> - እንጨት <u>ሰበረ</u> የሚሉት ይገኙበታል።

በመጨረሻም መምህሩ ተማሪዎችን ያልገባቸው ካለ በመጠየቅ ለጥያቄዎቹም ምላሽ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት አጠናቋል።

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ፊርማዬን ያስቀመጥኩኝ የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ፅሑፎች ምንጭ በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ደረበ ሙሉ

ፊርማ _____

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ

የማስረከቢያ ቀን ነሐሴ ፯ - ፲፱፻፺ ዓ/ም